ፍኖተ
# ነፃነት
ፍኖተ ነፃነት ማክሰኞ ጥር 22 ቀን 2004 ዓ.ም. ዋጋ 6:00
2ኛ ዓመት ቅጽ.2 ቁ.27
የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል!



## የኢህአዴግ ባለሥልጣናት በሥልጣናቸው ለሚመጣ እንኳን ለሰው ልጅ ለፈጣሪም አይመቹም

6

አቶ ደምሴ መንግስቱ



# መናገር በሚገባችሁ ጊዜ ዝም አላችሁ
## ዝም ማለት ሲገባችሁ ትናገራላችሁ

የገዥው ፓርቲ የሚያደርገው ሁሉ ትክክልም ይሁን አይሁን ከእውነተኛ ፍርድ አኳያ ሳይሆን ከአሉታዊ ጥቅም አኳያ ስለሚያዩት ሕዝብ ሲበደል ፍርድ ሲጓደል አይተው እንዳላዩ ይሆናሉ፡፡ ሥርዓቱ ሲወድቅ ግን አብረው እንደሚወድቁ ከእነርሱ በፊት በእነርሱ መንገድ ይሄዱ ከነበሩት ከወደቁት መማር አይችሉም፡፡

13

## የከተማ ቦታ ሊዝ አዋጅ ለሕዝበ ውሳኔ እንዲቀርብ መድረክ ጠየቀ

ብዙአየሁ ወንድሙ

በቅርቡ የወጣው የከተማ ቦታ የሊዝ አዋጅ ሕዝብ ተወያይቶ እንዲወስንበት ለህዝብ ውሳኔ መቅረብ ይገባዋል ሲል የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ /መድረክ/ ጠየቀ፡፡ መድረክ ይህንን የጠየቀው ጥር 17 ቀን 2004 ዓ.ም በጽ/ቤቱ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ነው፡፡ በመግለጫው ላይ እንደተገለፀው "አዋጁ የፓርላማውን የአሰራር ደንብ ሳይጠብቅ የወጣ ከመሆኑም በላይ የዜጐችን መብትና ጥቅም የገፈፈ ነው" ተብሎአል፡፡

በመግለጫው ላይ ለተነሱት ጥያቄዎች የመድረክ ሥራ አስፈጻሚዎች በጋራ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ዶ/ር መረራ ጉዲና እንደተናገሩት "አዋጁ ዜጐች የኢህአዴግን እጅ እንዲያዩ የሚያደርግ ነው፡፡ በፊውዳሉ ሥርዓት ዘመን ባለርስቱ ጭሰኛውን "ጣሪያህን ነቅለህ ሂድ" ይል ነበር፡፡ ዛሬም ኢህአዴግ ያወጣው

ወደ 11 ዞሯል

### ቶማስ ቦኒ ያዪ የህብረቱ ሊቀመንበር ሆነው ተመረጡ፤ አዲሱ
## "የቻይና ስጦታ" ህንፃም ተመረቀ

ብስራት ወ/ሚካኤል

የአፍሪካ ህብረት 18ኛው መደበኛ ጉባዔ ከጥር 14-21 ቀን 2004 ዓ.ም የተከናወነ ቢሆንም የሀገሮቹ መሪዎች ሰፊ ውይይትና ምክክር ያደረጉት ግን በዋነኛነት ጥር 20-21 ቀን 2004 ዓ.ም በአዲሱ የአፍሪካ ህብረት ህንፃ ትልቁ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ነበር፡፡

ከጥር 14-19 ቀን 2004 ዓ.ም የህብረቱ አምባሳደሮችና ሚኒስትሮች አህጉሪቱን ይመለከታል ያሉትን አጀንዳ ይዘው በመቅረብ በቀድሞው የህብረቱ ህንፃ አዳራሽ ምክክር ካደረጉ በኋላ ለመሪዎቹ አቅርበዋል፡፡

18ኛው የህብረቱን ጉባዔ ለየት ከሚያደርጉት መካከልም ሙሉ በሙሉ በቻይና መንግስትና ህዝብ ድጋፍ በ200 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለአፍሪካ "የቻይና ስጦታ" የተሰራው አዲሱ ህንፃ 99.9 ሜትር ከፍታ ያለው ሲሆን የመሰብሰቢያ አዳራሹ 2,500 ሰው የሚይዘውን ጨምሮ የተለያዩ መለስተኛ አዳራሾችና የጋዜጣዊ መግለጫ ጉባኤ አዳራሾችና ለተለያየ አገልግሎት የሚውሉ ሌሎች አዳራሾችን ይዟል፡፡ የአፍሪካ ህብረት 1,300 ቋሚ ሰራተኞች እንዳሉት፤ ከዚህ በፊት የሰራተኛ ቢሮ እና የመሰብሰቢያ አዳራሽ እጥረት እንዳለ የተገለፀ ሲሆን ከዚህ ጉባዔ በኋላ ግን 700 ሰራተኞች ወደ አዲሱ ህንፃ ቢሮ ሲገቡ ቀሪዎቹ 600 ሠራተኞች ግን በቀድሞው የሕብረቱ ቢሮ ሥራዎቻቸውን እንደሚያከናውኑ ተጠቁሟል፡፡ አዲሱ ህንፃ ያረፈበት ቦታ 50 ሺህ ስኩዌር ሜትር ሲሆን ይህም ከኢትዮጵያ መንግስት በነፃ የተበረከተ ቦታ እንደሆነ እና 1,200 ቻይናዊያንና ኢትዮጵያዊያን በህንፃው ስራ ላይ መሳተፋቸው ተጠቁሟል፡፡

ከዋናው የህብረቱ ጉባዔ በፊት የህብረቱ በይነ መንግስታት የልማት ትብብር (NEPAD) ጥር 19 ቀን 2004 ዓ.ም ስለ አህጉሪቱ ወቅታዊ የልማት አጀንዳ ላይ መክረዋል፡፡ በወቅቱም በአህጉሪቱ ስላሉ አጐራባች ሀገሮች የንግድ ትስስርና የመሠረተ ልማት አውታር ዝርጋታ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡

ከህብረቱ መሪዎች ጉባኤ በፊት በህንፃው ምረቃ ስነ-ሥርዓት ላይ የቻይና መንግስት ተወካይ የቻይና ህዝብ የፖለቲካ ምክክር ምክር ቤት ሊቀመንበር የሆኑት ዣ ኪንግሊን "ይህ ህንፃ ከቻይና መንግስት በቻይና ህዝብ ስም የተበረከተ ስጦታ ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው ቻይና ለአፍሪካ ያላትን አጋርነት የሚያረጋግጥና ወደፊትም የሁለቱም የትብብር ግንኙነት የሚያጠናክር መሠረት ነው፡፡" ሲሉ ንግግር አድርገዋል፡፡ የኢትዮጵያና የጅቡቲ መንግስታትም ለህንፃው የሚውሉ ግብዓቶችን ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ላደረጉት ትብብርም ተወካዩ አመስግነዋል፡፡

ወደ 11 ዞሯል

## በውስጥ ገፅ

አምባገነንነትና ዝግመት፣ የኢትዮጵያ እና የበርማ ንፅፅር
2-3
ጊዜ ጌታ ጊዜ ከፋይ
9
የመብት ጥሰት እየተፈፀመ መሆኑን ሰመጉ አስታወቀ
13

## የአዲስ አበባ ሕዝብ ሆይ! መሬትህን አታስነካ!

14

# አምባገነንነትና ዝግመቱ፣ የኢትዮጵያ እና የበርማ ንፅፅር



ፕሮፌሰር መሳይ ከበደ

ከበርማ ተምሳሌታዊት የተቃዋሚ መሪ ሳን ሱ ቺ ከእስር መለቀቅ ጀምሮ፣ የሀገርቷ የፖለቲካ አቅጣጫ በፖለቲካ ተዛቢዎችና ተንታኞች ዘንድ ከፍተኛ የመወያያ አጀንዳ ሆኗል፡፡ የሃገሪቱ ወታደራዊ መሪዎች ወደ ዴሞክራሲያዊነት የመሸጋገር አዝማሚያ ከሳዩ ወዲህ ሂላሪ ክሊንተን በርማን (ማይናማር) በመጎብኘት ከመሪዎቿ ጋር ተወያይተዋል፡፡

ሀገሪቱ ለአስርት ዓመታት በወታደራዊ አምባገነን ስር ከመሆኗም በላይ ወታደራዊ መሪዎቹ የገቡትን ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ቃል ስያዘገዩት ነበር፡፡ ሆኖም አሁን ከፍተኛ ፖለቲካዊ ለውጥና ወደ የዴሞክራሲያዊ መንግሥትነት ሽግግር የሚወስደውን መንገድ ይዘዋል፡፡ በሌላ በኩል በ1997 ዓ.ም ብልጭ ብሎ የጠፋው የነፃና ፍትሃዊ ምርጫ አጋጣሚ ቢፈጠርም፣ በተፈጠረው የኋሊዮሽ ጉዞ ኢትዮጵያ ወደ ጨቋኝ እና አምባገነናዊ መንግሥት ስርዓት እየገባች ነው፡፡ በ2002ቱ ምርጫ ስርዓቱ 99.6% የፓርላማ መቀመጫ ማሸነፉን ማወጁም ጥሩ ማስረጃ ነዉ፡፡ የትንተናዬ አላማ ሁለቱን ሀገራት በማወዳደር ለምን ፅንፍ (ተቀራኒ) አቅጣጫ እንደያዙ እንዲሁም የኢትዮጵያን የኋሊዮሽ ጉዞ ምልክቶች" ተቃዋሚዎች ያሏቸውን የፖለቲካ አማራጮች እንዲሁም የገዥው ፓርቲን ለመዳሰስ ነው፡፡

## ብዙዎቹ ተመሳሳይነቶች

ፖምንና ብርቱካንን ማነፃፀር እንዳይመስልብኝ እንጂ ሁለቱ ሀገራት ማነፃፀር የሚቻል መሆኑ በማሳየት መጀመር አለብኝ፡፡ በርግጥ ዋነኛው መከራከሪያ ሆኖ የሚቀርብብኝ የኢትዮጵያ ስርዓት የህዝባዊ መንግሥትነት መገለጫዎች ያሉት ሆኖ የበርማው ደግሞ ወታደራዊ አገዛዝ ከመሆኑም በላይ በጊዜው ተቀባይነት የነበረውን ህዝባዊ መንግሥት በ1959 እ.ኤ.አ በመፈንቅለ መንግሥት አስወግዶ የመጣ መሆኑ ነው፡፡ ልዩነቱን ብቀበልም ግልፅ (open) ወታደራዊ አገዛዞች ወታደራዊ ልሂቃንን በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ሲገለገሉባቸዉ ሌሎቹ ደግሞ ወታደራዊ ገዥዎችን ወደ ህዝባዊ ፖለቲከኝነት ይቀይራሉ፡፡ በዚህ መካከል ወታደራዊ ልሂቃን ከህዝባዊ ልሂቃን ጋር የጠበቀ ቅንጅት የሚፈጥሩበት አግባብም አለ፡፡ የኔ ክርክር የ|ለኛው አግባብ ለኢትዮጵያም ይሰራል የሚል ነው፡፡ በመሆኑም ያለ ጥርጥር፣ የህወሓትን ታሪክ እንደ ሽማቂ ድርጅት ያየን እንደሆን" የመለስ መንግስት ለወታደራዊ ሰዎች ከሚያደርገው አክብሮት የሞላበት አያያዝ ጋር ተዳምሮ በህዝባዊ (civilan) መንግሥትና የመጨቆኛ መሣሪያው መካከል 'ህጋዊ' ትብብር ፈጥሯል፡፡ ስርዓቱ በአብዛኛው ኢትዮጵያውያን ዘንድ ተቀባይነት ማጣቱ ቀጣይነቱን በወታደራዊና የፖሊስ ሀይላት ላይ ብቻ የተንጠለጠለ አድርጎታል፡፡

በተጨማሪም ምንም እንኳ በርማና ኢትዮጵያ የተለያዩ አህጉራት ውስጥ የሚመደቡ ቢሆኑም ብዙ አስደንጋጭ ተመሳሳይነቶች አሏቸው፡፡ በጥቂቱ ለመጀመር ልክ እንደ በርማ ሁሉ ኢትዮጵያም በህዝባዊ መንግሥት ላይ የተደረገውን መፈንቅለ መንግሥት ተከትሎ" ለጨቋኝ ወታደራዊ አገዛዝ ከመዳረጓም በላይ ወታደራዊ አገዛዙ በሁለቱም ሀገራት ሶሻሊስታዊ ፖሊሲን ነበር የተዘረጋው$ ደርግ ሀገራዊ ብሔርተኝነቱን የሶሻሊስት አጀንዳ መነገጃ እንደዳረገው ሁሉ የበርማው ወታደራዊ መንግሥትም በ1974 እ.ኤ.አ የበርማ ሶሻሊስታዊ ሪፐብልክ ህብረት አውጆ ነበር፡፡

በዚህ የተነሳም በሁለቱም ሀገራት የታወጀውን የማምረቻ ስልተ ምርት ውርስ ተከትሎ የኢኮኖሚው ብልሹ አስተዳደር ወደ ሙስናና ተጠያቂነት ማጣት ተሸጋግሮ ነበር፡፡ በተጨማሪም ሀገራቱ ሶሻልዝምን በመተው ቀኝ ኋላ ዞር ሲሉ የመንግሥት የልማት ተቋማትን ወደ ግል ይዞታ የማዞሩ ሂደት ሁሉን ነገር በገዥው ፓርቲ ሰዎች (የቀድሞ ጓደቻቸው እጅ) እንዲከማች መንገድ ሰጠ፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ የመንግሥት ንብረትን ወደ ግል የማዞሩ ሂደት (privatization) የንብረቱን ባለቤትነት በሙስና አካሄድ ወደ አንዱ የህወሓት ቅርንጫፍ ቡድን ማሸጋገር እንደሆነ ሁሉ በበርማም ወደ ጀኔራሎች ወይም የቀድሞ ጓዶቻቸው ንብረትነት መቀየር ነበር፡፡

ገንዘብ የሚገኝባቸውን ዘርፎች አጠቃሎ በመያዝ (ሞኖፖላይዝ በማድረግ) እና ጤናማ ፉክክርን በመከልከላቸው የተነሳ የሁለቱም ሀገራት ኢኮኖሚ ተጨባጭ ውጤት ያለማሳየቱ አያስገርምም፡፡

ሌላውና ግልፁ ተመሳሳይነት ሁለቱም ሀገራት በጎሳ ፀብ እና (የሽማቂዎች ጥቃት የተነሳ መጎዳታቸውና አሁንም ቢሆን በዚሁ ችግር እየማቀቁ መገኘታቸው ነው፡፡ እንደ በርማ ሁሉ ኢትዮጵያም የብዙ ብሔሮች ሀገር እና የልዕለ ብሔሩን ቡድን ለማጥፋት በከፍተኛ ጥላቻ የተነሳሱ ነፍጥ አንጋቾች ታሪክ የምታስነብብ ናት፡፡ በበርማ የብሄር ብድኖች የበርማውያንን (Burmans) የበላይነት ይቃወማሉ፤ 60% የሚሆኑቱ በርማውያን ሲሆኑ በርማውነት (Burmanization) በተባለ ፖሊሲ አናሳዎቹ ቡድኖች በኢኮኖሚና ባህላዊ ጉዳዮች ወደ ዳር ተገፍተዋል፡፡ በኢትዮጵያ ያለው የብሄር ቡድኖች ቅራኔ የአማራ የበላይነትና አማራዊነት (Amharization) የሚለው ፖሊሲ እንደሆነ እናውቃለን፡፡ በአማፂ ብሔርተኞቹ አይን በሁለቱም ሀገራት የሚገኙት ማዕከላዊ መንግስታት ብሄራዊ አንድነትን የመከላከል ሀላፊነት የሚወጡት ጠንካራ ወታደራዊ ሀይል በመገንባት ነው፡፡

የብሔር ግጭት እና ውጤቱን ካየን ሁለቱ ሀገራት ሰፊ ልዩነቶች አሏቸው፡፡ ከበርማ እውነታ በተቃራኒ በኢትዮጵያ የነበረዉ የአማራ የበላይነት የብዙሃን ቁጥር አይሆንም፤ የኦሮሞ ብሔር ከአማራ እኩል እንደሆ ይወሳልና፡፡ ይህ ታዲያ የዛሬውን የትግራዎች የበላይነት ኢትዮጵያን በግድ ወዳልተለየ የአናሳዎች ቡድን የበላይነት እንደሚወሰድ መግለፅ ሳያስፈልግ ማለቴ ነው፡፡ ከምንም በላይ በበርማ የሚገኘው ወታደራዊ ሀይል የብሄር ሽማቂዎችን መቆጣጠር ሲችል የኢትዮጲያዎቹ ግን ወታደራዊ ሀይሉን በማሸነፍ ገርስሰዉታል፡፡ የዚህ ሁሉ ግልፅ ውጤት የኢትዮጵያ ወታደራዊ ሐይል ማጣት እና በሽማቂ ልሂቃን መተካት እንዲሁም የኤርትራ ነፃ ሀገር መሆን ነው፡፡ ነገር ግን ከላይ እንደተገለፀው፣ እነዚህን የመሳሰሉ ልዩነቶች የህወሓት አገዛዝ የአንደኛው ወታደራዊ ሀይል በሌላ ወታደራዊ ሀይል መተካት መሆኑን አያስተባብልም፡፡

በባህሪ ደረጃ በሁለቱም ሀገራት ያሉት ስርዓቶች ለምርጫ ሽንፈት የሚያሳዩት ባህሪ እጅጉን ተመሳሳይ ነው፡፡ ሁለቱም የፖለቲካ ስነ ምህዳሩን በትንሹም ቢሆን በማስፋታቸው ጉራ ቢነዙም መልሰው ለመከርቸም እጅግ ትንሽ ፈተና/ፉክክር ትበቃቸዋለች፡፡ በ1990 እ.ኤ.አ የበርማ ወታደራዊ አገዛዝ ለረዥም ጊዜ ቃል ሲገባለት የነበረውን ነፃ ምርጫ እንደሚያከናውን አስታወቀ፡፡ በውጤቱም በሳን ሱ ቺ የሚመራው National league for democracy ከፍተኛ ውጤት (land slide) በማስመዝገብ አሸነፈ፡፡ የወታደራዊው መንግሥት አለቆች መልስ አይነተኛ /የተለመደ ነበር! ስልጣኑን ለአሸናፊዉ ፓርቲ ለመስጠት ካለመፍቀዳቸውም በላይ ሳን ሱ ቺ እና ሌሎች አመራሮችን በቁም (በቤት ውስጥ) እስረኝነት ማቆየት ነበርና፡፡

የፖለቲካ ስነ ምህዳሩን የማስፋት ሂደት እንደገና በመጀመር በበርማ በ2003 እ.ኤ.አ ወታደራዊ አገዛዙ ሰባት ደረጃዎች ያሉት ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እና ነፃ ምርጫ የሚወስድ አቅጣጫ ጠቋሚ ዕቅድ ይፋ አድረጎ ነበር፡፡ በ2010 ቃል የተገባው ምርጫ ቢደረግም ነፃና ፍትሃዊ አልነበረም፡፡ ማጭበርበርና መሰሪነት በሰፊው የተስተዋሉበት ከመሆኑም ብሶ የሳንሱቺ National League for Democracy ፓርቲ እንዳይሳተፍ ከመታገዱም በላይ ሳን ሱ ቺራሷ እና ሌሎች መሪዎች ለቤት እስረኝነት ተዳረጉ፡፡ ከዚህ በኋላ ወታደራዊው ገዥ ቡድን የተወከለበት Union Solidarity and Development Party በ80% ድምፅ ሙሉ በሙሉ ማሸነፉን አወጀ፡፡

በኢትዮጵያም ተመሳሳይ አፅመ ታሪክ እናስታውሳለን፡፡ በመጠኑም ቢሆን ነፃና ፍትሃዊ በነበረው የ2005ቱ ምርጫ ተቃዋሚዎች ትልቅ አሸናፊነት ተቀዳጅተው ነበር፡፡ የሕወሓት ግብረ መልስ ውጤቱን መሰረዝና ዋና ዋና የተቃዋሚ ቡድን አመራሮችን ማሰር፣ እና ተቃውሞዎችን በሀይል መበተን ነበር፡፡ ይህም ከፍተኛ አፈና በማስከተል እና የ2010ን ምርጫ ከነፃነት እና ፍትሃዊነት በማፋታት ዳግም ተረጋገጠ፡፡ ስንት የተባለለት ምርጫ የተካሄደው በማስፈራሪያ፣ አፈና እና ገቺ ህጎች ታጅቦ ነበር፡፡ ተቃዋሚዎችና የውጭ ታዛቢዎች ስለ መጭበርበሩ እና በእጩዎች ላይ ስለደረሰው ማስፈራሪያና ዛቻ/ ንዝነዛ ቢናገሩም ገዥው ፓርቲ ያለ ምንም ማፈር ምርጫውን በ99.6% ማሸነፉን አወጀ፡፡

ሊተኮርበት የሚገባው ሌላው ጉዳይ፣ በሁለት አገሮች እየጨመረ የመጣው አፋኝ ፖሊሲ በሀገራቱ የታቃውሞ ሀይሎች ላይ ያለው ተፅዕኖ ተመሳሳይ መሆኑ ነው፡፡ በሁለቱም ሀገራት የሚገኙ የተቃውሞ ቡድኖች ገዢ ልሂቃኑን ወይ ለድርድር ለማቅረብ አሊያም ጨቋኝ ፖሊሲያቸውን እንዲያላሉ ማስገደድ አልቻሉም፡፡ በዚህ የተነሳ ገሚሶቹ ተቃዋሚዎች ወደ ትጥቅ ትግል እየተሳቡ ሲሆን ገሚሶቹ ደግሞ የህዝባዊ ተቃውሞ መነሳትን መጠባበቅን መርጠዋል፡፡ አቅመ ቢስነት National League for Democracyን ለሁለት ለመከፈል ችሏል! ገሚሶቹ አባላት ከምርጫ ራሳቸውን ላለማግለልና ከገዢው ፓርቲ ጋርም ለመስራት ወስነዋልና፡፡ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ቡድኖች ሁኔታ ከዚህ ለየት የሚል ቢሆንም ቅሉ በአገዛዙ ላይ የለውጥ ጫና ማሳደር ባለመቻላቸው የተነሳ መከፋፈል እና የስትራቴጂ ዳግም አሰሳ ማድረግ ግድ ብሏቸዋል፡፡

## ዋና ዋና ልዩነቶች

ልዩነቶችንበተመለከተትልቁአንዷከምዕራብ ጋር ባላቸው ግንኙነት ነው፡፡ ከ1996 ጀምሮ በርማ የአለም ባንክ እና የአለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትን ጨምሮ በምዕራባውያን ማዕቀብ ስር ናት፡፡ ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ቢኖርም በምስራቅ አፍሪካ ብቸኛ የተረጋጋ መንግሥት ያላትና እና የፀረ ሽብርተኝነት ጦርነት አጋር በመሆንዋ ምዕራባውያን ኢትዮጵያን በኢኮኖሚ ለመቅጣት አልፈቀዱም፡፡ ሆኖም ልዩነቱ የጎላ የሚያደርገው በበርማ ላይ የተጣለው አለም አቀፍ ማዕቀብ ከተግባራዊነት የራቀ በመሆኑ ነው፡፡ ላለመተግበሩ ከሚነሱት ምክንያቶች አንዱ ደግሞ የሁለቱ ጎረቤት ሀገራት— ህንድ እና ቻይና እንዲሁም የደቡብ ምስራቅ ኤዢያ ሀገራት ህብረት የኢኮኖሚ ማዕቀቡን እና ከቀጠናዉ ፖለቲካ የማግለሉን ሀላፊነት ለመተግበር ፍቃደኛ ያለመሆናቸዉ ነው፡፡

የሁለቱን የአገዛዝ ልዩነት የሚያሰፋው" የበርማዉ ወታደራዊ አገዛዝ ኢ-ዴሞክራሲያዊ መሆኑን ማመኑና እንደ መፍትሄም በ2003 ደረጃ በደረጃ ወደ ዴሞክራሲያዊ መንግሥትነት ለማደግ የነደፈው ዕቅድ (rood map) ነው፤ ምንም እንኳ ብዙ ታዛቢዎች ቀርፋፋና ተጨባጭነት የሌለው ነው ሲሉ ቢተቹትም ቅሉ፡፡ በተቃራኒው የኢህአዴግ/ህወሓት አገዛዝ መሰረታዊ የዴሞክራሲያዊነት ባህሪያት ባይኖሩትም ላለማመን ፍፁም የቆረጠ ከመሆኑም በላይ ህወሓት ወደ መንግሥት ስልጣን ከመጣ ጀምሮ ምንም የሽግግር ዝግጅቶች ባለ ማድረጉ ዴሞክራሲ የሚያብብበትን ዕድል አልተፈጠረም፡፡

የዚህ ዓይነት አስተሳሰብ ወደ አልተለመደና ለመረዳትም ሆነ ለማስረዳት አስቸጋሪ የሆነ አስተሳሰብ ወደ መያዝ ያመራል፡፡ በዚህ አስተሳሰብ መሠረት አገዛዙ በተቃዋሚዎች ላይ የሚወስደውን ርምጃ የሚተረጉመው ተቃዋሚዎቹ ጸረ ዴሞክራሲ ናቸው በሚል ሳይሆን ዴሞክራሲያዊ የሆነውን ሥርዓት ኢ-ዴሞክራሲያዊ ከሆኑ ኃይሎች መከላከል በሚል ነው፡፡

ለኢትዮጵያው አገዛዝ የማያቋርጥ የማጭበርበር እና የሽግግር ሂደት አደናቃፊነት ከላይ ያየነው ሁናቴ እንደ ምክንያት የሚነሳ ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ ፖለቲካው ቅርቃር /dead lock/ ውስጥ በመግባቱ ብዙ ኢትዮጵያውያን በአገዛዙ ዝግመታዊ ለውጥ ላይ ተስፋ በመቁረጣቸው አንድም በግዴለሽነት (passivity) መመታት አሊያም የአመፅ ምንጮችን መጠባበቅ ሆነ፡፡ እንዲህ ያለው ወደፊት የማያስኬድ ዝግ ሁኔታ የሠላማዊ ትግል አራማጅ ተቃዋሚዎችን

**ሊተኮርበት የሚገባው ሌላው ጉዳይ፣ በሁለት አገሮች እየጨመረ የመጣው አፋኝ ፖሊሲ በሀገራቱ የታቃውሞ ሀይሎች ላይ ያለው ተፅዕኖ ተመሳሳይ መሆኑ ነው፡፡ በሁለቱም ሀገራት የሚገኙ የተቃውሞ ቡድኖች ገዢ ልሂቃኑን ወይ ለድርድር ለማቅረብ አሊያም ጨቋኝ ፖሊሲያቸውን እንዲያላሉ ማስገደድ አልቻሉም፡፡ በዚህ የተነሳ ገሚሶቹ ተቃዋሚዎች ወደ ትጥቅ ትግል እየተሳቡ ሲሆን ገሚሶቹ ደግሞ የህዝባዊ ተቃውሞ መነሳትን መጠባበቅን መርጠዋል**

## ዳሰሳ

እንደሚያጥላላ ሁሉ ለኢትዮጵያም ሆነ ሥልጣን ለጨበጡ ኃይሎች ከተሰፋ በስተቀር የሚያስገኝላቸው የተጨበጠ ነገር

### የበርማ የለውጥ ተነሳሽነት ምክንያቶች

በርማ ወደ ሽግግር ሂደት የገባችበትን ሁኔታ ለመረዳት ወታደራዊ ቡድኑ ዝገመታዊ የዴሞክራሲያዊነት አካሄድ የመረጠበትን ምክንያት ማወቅ ያሻል፡፡ የፖለቲካ ስነ ምህዳሩን የማስፋቱ ውሳኔ ከተቃዋሚዎች ጫና ያለመመንጨቱን አመላክቻለሁ፡፡ ታዲያ ለረዥም ዘመናት ራሱን ያደላደለና አገዛዙን ለመከላከል የቻለን አምባገነን መንግሥት የፖለቲካ ምህዳሩን ለመክፈት ምን አስገደደው? ይልቅ እዚህ ላይ የፖለቲካ ተንታኞች በፖለቲካዊ ለውጡ አቅጣጫ ላይ ያላቸው አመለካከት እንደሚለያይ መጠቆም ያሻል፡፡

ብዙዎች ታዛቢዎች የታቀደው ዴሞክራሲያዊነት የማታለያ ዘዴና በህዝባዊ መንግሥት ስም ወታደራዊ አገዛዙን ለማስቀጠል የታለመ ነው ይላሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ሂደቱ ቀርፋፋና ወጥ ባይሆንም ቅሉ ለዴሞክራሲያዊነት የሚያነሳሱ አስገዳጅ ምክንያቶች ስለመኖራቸው ይከራከራሉ፡፡ አንደኛው አስገዳጅ ነጥብ በርማ የምትገኝበት ቦታ ነው፤ የሚቆም የማይመስል ኢኮኖሚያዊ እድገት ያለበት ቀጠና! በርማ የዚህ ሽምጣጭ ዕድገት ተቋዳሽ ያለመሆኗን መገንዘብ ለወታደራዊው ቡድን የለውጥ ፍላጎት በቂ መነሳሻ ነው፡፡

ካስተዋሏቸው ጉዳዮች አንዱ አምባገነናዊ ስርዓት ነፃና ፍትሃዊ ተወዳዳሪነትን በመግደል የመንግሥት ንብረትን ለግላቸው የሚያውሉ እና በሙስና የተቀየዱ ቡድኖችን በማበራከት የኢኮኖሚ ዕድገቱን እንደሚገታ ነው፡፡ ፈጣን ለውጥ ያለው የገበያ ኢኮኖሚ ስርዓት እንዲኖር የተገለሉና የተማሩ ሰዎች ልምዳቸውን" የብልፅግና ህልማቸውን እና ማህበረሰባዊ የለዉጥ ናፍቆታቸዉን በኢኮኖሚው ስርዓት ውስጥ ያስገቡ ዘንድ የፖለቲካ ስርዓቱ የተቆለፈ መሆን አይጠበቅበትም፡፡ በሌላ አግባብ ለወታደራዊው ቡድን የፖለቲካ ስነ ምህዳሩን ማስፋት ከአለም አቀፍ ጫና የሚመነጭ ሳይሆን የኢኮኖሚ እድገት በፖለቲካዊ ለውጥ ላይ ጥገኛ መሆኑን ስለተረዳ ነው፡፡

ሌላው ተያያዥ የፖለቲካ ለውጥ ተነሳሽነት" በሚያመጡት ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ልክ በምዕራባውያንና አለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት የተጫነባቸውን የኢኮኖሚ ማዕቀብ ለማስነሳት ይረዳቸው ዘንድ ነው፡፡ ማትለም ወታደራዊ ቡድኑ ሀገሪቷን በተለየ የኢኮኖሚ አቅጣጫ ለመውሰድ እስከወሰነ ድረስ የአለም አቀፉ ማዕቀብ ቀስ በቀስ ስለምነሳላቸዉ የሀገሪቷ አዲሱ አቅጣጫ እዉን ይሆናል ማለት ነው፡፡

ሌላው የፖለቲካ ስነ ምህዳሩን የማስፋቱ ሂደት ሳቢ እንዲሆን ያደረገው በመንግስት የተያዙ ተቋማትን ወደ ግል በማስተላለፉ ሂደት ብዙ የጦሩ ከፍተኛ መኮንኖች/ጄኔራሎች ተሳታፊ መሆናቸው ነው፡፡ የመንግስትን ንብርት ሙሰኛ በሆነ መልኩ ወደ የበላይ መኮንኖች በማስተላለፉ ሂደት የተፈጠረው ወታደራዊ ነጋዴ" ጤነኛ የሆነ የግል ንብረት የማፍራት ሂደትን እንዲያበረታታ ያልተጠበቀ ውጤት አስከተለ፡፡ ጡረታ የወጡም ሆኑ ያልወጡት ጄነራሎች ቡድን፣ ያላቸውን ኃይልና ተፅዕኖ ፈጣሪነት በመጠቀም የግል ንብረት የማከማቸቱ ሂደትን የሚያግዙ ሁኔታዎችን ለማፍጠ ተንቀሳቀሱ$ በሌላ መልኩ አብዛኛዎቹ የግል ንብረት ያፈሩ ጄኔራሎች ፍላጎታቸው ቀስ በቀስ ከፖለቲካ ስልጣን ይልቅ የግል ድርጅቶቻቸውን ወደ ማስተዳደር አዘነበለ፡፡

ታዛቢዎች ሌላው የፖለቲካ ለውጡን ያጧጧፈው ምክንያት በወታደሩ ውስጥ የተፈጠረው የትውልድ ግጭት ነው ይላሉ፡፡ አምባገነናዊ ስርዓቱን የገነቡት የቀድሞ የበላይ መኮንኖች በዕድሜ እየገፉ ሲመጡ፣ ወጣት መኮንኖቹ ሊተኳቸው ቋመጡ፡፡ የትውልድ ግጭትን በማራቅ የወታደሩን አንድነት መጠበቅ

## ከላይ ያነሳውን ውጤት ለማግኘት፣ በዴሞክራሲያዊነት ሂደቱ ላይ ገደብ በመጣል ወታደራዊ ሀይሉ ዛሬም የፖለቲካ ከፍታ መወጣጫውን ከእጁ እንዳይወጣ ማድረግ ነው፤ ይህ ነው መገለልን የሚያቆመው፡፡ በ2008 የወጣው ህገ መንግሥትም 25% የፓርላማውን መቀመጫ እና ከመከላከያና ከደህንነት ጉዳዮች ጋር የሚገናኙ የመንግሥት ስልጣኖችን ለወታደራዊው አባላት በመተው ይህንኑ ከወነ . . .

የሚቻለው ደግሞ ወደ ህዝባዊ መንግሥትነት በመሸጋገር ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ የወታደሩም፣ እያረጁ የመጡት እና ጡረታ የወጡ ያሉ የበላይ መኮንኖችም ፍላጎት እየተጠበቀ ነው ማለት ነው፡፡ ዴሞክራሲያዊ ሂደቱን ወታደሩ ካነሳሳውና ከመራው የሚፈጠረው ህዝባዊ መንግሥትን መልካም ወዳጅነት ማፍራት ይችላል፡፡

በርማውያን ነፃ የገበያ ስርዓት ያለ ፖለቲካዊ ለውጥ እንደማይመጣ በማገንዘባቸው መሆኑ ለኢትዮጵያው ገዢ ቡድን መልካም ትምህርት ነዉ፡፡ የመለስ መንግሥት የስልጣን ቆይታ ጨቋኝ የሆኑ የመንግሥት ሀይሎችን በመጠቀም አቅሙ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይህ አቅም መለስ የመጨቆኛ መሳሪያውን /ወታደሩን/ ቁሳዊ ፍላጎት በማሟላት እና ለዘብ አርጎ በመያዝ በኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች የተነሳ ከህዝቡ የሚገጥማቸውን ተቃዉሞ በሀይል እንዲከላከሉ ያግዛል፡፡ ሁለቱ ሁኔታዎች ተከታታይ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት ከመፈለግ አያልፉም፡፡

አቶ መለስ ይህንን በሚገባ ይገነዘባሉ፤ ልማታዊ መንግሥት ለሚለው አስተሳሰብ ሊሰጡት ከሚሞክሩት የወረት ትኩረት እንደሚታየው፡፡ አዲስ ፎርቹንን ለመቅደም "አብዮታዊ ዴሞክራቶች ዴሞክራሲን ወዲያ በማድረግ ቅቡልነታቸው በሚያመጡት ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ላይ ያደርጋሉ፡፡"

የአቶ መለስ ልማታዊ መንግሥትን የማምጣት ህልም አንድ እውነታን መጋፈጥ አለበት፡፡ ይኸም ታማኞቻቸው የግል ጥቅም የባለውለታ ነት ስሜት ታማኝነት፣ ፍርሃትና የሞራ ጉትጎታ ብቻውን ኢትዮጵያን በልማት ጎዳና እንድትራመድ ያደርጋት ቀጣይነት ያለው ግፊት ሊያመጣ የማይችል መሆኑ ነው፡፡ቀጣይነት ያለው የምርታማነት ፍላጎት በደንበኝነት፣ በቀድሞ ጓደኝነት፣ እና በብሔር ቡድናዊነት የሚደረግን አድልኦ ለማቆም መጋፈጥ አለበት፡፡ ማለትም የንግዱ ማህበረሰብ ለነፃ ገበያ ፉክክር ራሱን ማዘጋጀት አለበት፡፡ ህዝባዊ አመፅ ለማስቀረት የኢኮኖሚ ዕድገት ግድ በመሆኑ በተዘዋዋሪ ሕወሓት በበላይነት ለያዘው መንግሥት መቆየት የፖለቲካ ማሻሻያ ማድረግ ግዴታ ይሆናል ማለት ነው፡፡

መለስ የፖለቲካ ስነ ምህዳሩን ለማስፋት የማይፈልገው፣ የቻይናው አይነት ያለ ፖለቲካዊ ነፃነት የሚመጣ የኢኮኖሚ ብልፅግና ሞዴል በአዕምሮው በመቀረፁ እንደሆነ እገምታለሁ፡፡ ነገር ግን ይህ አይነቱ የቻይናውያን ሞዴል በኢትዮጵያውያን መዓድ ላይ አልቀረበም፡፡ ኢትዮጵያ ሁሉንም አይነት ግጭቶች የተጫነች ሀገር ናት፤ በተለይ ሕወሓት ራሱ ያቀጣጠለው የብሄር አሉታዊ ቅንቅን፡፡ እጅግ የተስፋፋው የተለያዩ ብሔሮችን የሚወክሉ ልሂቃን ቅንቅን ኢትዮጵያን የጠበቀ ተመሳሳይነት ከሚያሳየው የቻይና ልሂቃን ተፈጥሮ የራቀ ያደርገዋል፡፡ አንዱ የማኦኢዝም የመደብ ጦርነት ውጤት ብዙሃ ልሂቃንን ማጥፋትና አንድ አይነት የአመራር መዋቅር መፍጠር ነበር፡፡ የኢትዮጵያን ሁኔታ ልዩ የሚያደርገው ልሂቃኖች በተቀናቃኝ ፍላጎት ላይ በተመሠረተ የማንነት ፖለቲካ መጠመዳቸው ነው፡፡

በኢትዮጵያ እየተፈጠሩ ያሉት ልሂቃን ተመሳሳይነት ከሚንፀባረቅበት የቻይናውያን የልሂቃን ሁኔታ ጋር በሩቁ እንኳ የሚያመሳስለው የለም፡፡ የቻይናው አይነት ባህሪ ያለው የፖለቲካ መደብ" የወታደራዊ ልሂቅ እና የቢሮክራሲው ለአስርት ዓመታት በጥብቅ ዲሲፕሊን" አንድነትና ምሉዕ በኩላሄነት ያለው የፖለቲካ ፓርቲ በኢትዮጵያ አይገኝም፡፡ ዳግም ኢህአዴግን ዉሰዱ፤ የተለያየ ፍላጎት ያላቸዉ ቡድኖች ህብረት ከመሆኑም በላይ የግንባሩ አንድነት አደላዳይ የሆነው ህወሓት በ1993 ዓ.ም ተፈረካክሷል፡፡ በውጤቱም ለአሜን ባዮች፣ አድርባዮችና ደራሽ ጥቅመኞች (የአጥቢ ዕድለኞችን) በር ከፈተ፡፡ በፖለቲካ ኢኮኖሚ እና ቢሮክራሲያዊ ልሂቅነት ለመታጨትም ከርዕዮተ አለማዊ ቆራጥነትና ተፎካካሪነት ይልቅ ለመለስና በዙሪያው ላሉ ቡድኖች ታማኝና ሎሌ መሆን ዋነኛ መስፈርት ሆኖ አረፈው፡፡ የምናየው ሁሉ ከገዢው ጎሳ ጋር በህገ ወጥ የፖለቲካ ጥላ በመከለል ለግለሰባዊ ብልፅግና የቆመ ሆነ፡፡ ስለዚህ ሙሰኞች፣ ችሎታ አልባና የራስ ጥቅም አሳዳጆች መላው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሥርዓቱን በበከሉበት ሁኔታ የኢኮኖሚ ልማት የመጣል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው፡፡

### የሽግግሩ ሂደት

የፖለቲካ ስነ ምህዳር ማስፋቱ የበርማን ኢኮኖሚ ዕድገት ቢያፋጥነውም እንኳ ወታደሩ በህዝብ ለተመረጠ አካል ስልጣን ለማስረከብ ይፈልጋል ማለት ግን አይደለም፡፡ እንደተባለው የዴሞክራሲያዊነት ሂደቱ የረዥም ጊዜ ፍላጎታቸውን የሚጠብቅ እና ለወደፊትም ለተወሰነ ጊዜ ከእጃቸው የማይወጣ መሆኑን ማረጋገጥ ይፈልጋሉ፡፡ አለበለዚያማ የብልፅግናቸው ምንጭ ሙስና መሆኑን እያወቅንና ለቀጣይ አገዛዛቸውም አስጊ (ፈታኝ) ነገር እንደሚገጥማቸው ካልገመቱ ስለምን ነገሮችን ለማመቻቸት ይሞክራሉ? ለነሱ የዴሞክራሲያዊ ሂደቱ ውድቀታቸውን ሳይሆን አዲስ በሚፈጠረው ስርዓት ውስጥም እንዲካተቱና ለቀድሞ ቦታቸውም ቢሆን ዋስትና እንዲሰጣቸው ይፈልጋሉ፡፡

ከላይ ያነሳውን ውጤት ለማግኘት፣ በዴሞክራሲያዊነት ሂደቱ ላይ ገደብ በመጣል ወታደራዊ ሀይሉ ዛሬም የፖለቲካ ከፍታ መወጣጫውን ከእጁ እንዳይወጣ ማድረግ ነው፤ ይህ ነው መገለልን የሚያቆመው፡፡ በ2008 የወጣው ህገ መንግሥትም 25% የፓርላማውን መቀመጫ እና ከመከላከያና ከደህንነት ጉዳዮች ጋር የሚገናኙ የመንግሥት ስልጣኖችን ለወታደራዊው አባላት በመተው ይህንኑ ከወነ፡፡ በተጨማሪም ህገ መንግሥቱ በወታደሩ ወሰን ውስጥ ለሚገኝ ጉዳይ ሙሉ ነፃነትን አጎናጽፎታል፡፡ ልክ እነሱንም የህገ-መንግሥቱ ደህንነቱና ሀገራዊ አንድነት ተከላካይ እንዳደረጋቸው ሁሉ፡፡

አሁንም ግዙፍ ስልጣን በጁ በመያዙ የፖለቲካ ስነ ምህዳሩን ማስፋት ነፃና ፍትሃዊ ፉክክርን ከማበረታታት ዘልሎ አያሰጋቸውም ቢባል ስህተትነት የለውም፡፡ ከህወሓት /ኢህአዴግ አገዛዝ ጋር ቢወዳደር ግልፅነትን ከማስፈንና ድብቅነትን ከመመንገል በቀር በመለስ መንግሥት ውስጥ እንደሚታየው የዜጎችን ዴሞክራሲያዊ መብቶች በመቀየድ የራስን ህግ መንግሥት ወደ መካድ አያመራም፡፡ ከምንም በላይ የበርማውያኑ ህገ መንግሥት ዴሞክራሲያዊነቱን በሂደት የማረጋገጥ ዕድል ሲኖረው የህወሓት/ኢህአዴግ አተያይ ግን በህገ መንግሥት የተሰጠውን መብቶች በመገደብ የፖለቲካ ዕድገቱን መግታትና ለኢትዮጵያዊያንም ከአመፅ በቀር አማራጭ የሚያሳጣ ነው፡፡

ሌሎቹ የኤሺያ ሀገሮች ወደ መድበል ፓርቲ ስርዓት ያደጉት ከአስርት ዓመታት የወታደራዊ ወይም ህዝባዊ አምባገነን መንግሥታት ተነስተውመሆኑን ካየን የዚህ ወታደራዊ ቡድን የሽግግር ሂደት ያለውን ሥርዓት የማስጠበቂያ ስልት ከመሆን አይዘልም፡፡

እነዚህ አጠቃላይ ሀገራት ዝግ ባለና እየጨመረ በሚሄድ ማሻሻያ ጀምረው ነው ትልቅ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማሻሻያ የሚፈልግ ባለመካከለኛ (ገቢ) መደብ ለመፍጠር የቻሉት፡፡

ምንም እንኳ ወታደራዊው ቡድን ብዙ ገደቦችን ቢያስቀምጥም የበርማ የተቃውሞ ሀይሎች "አሁኑኑ ሙሉ ዴሞክራሲ ካልሰፈነ አንገቴ ይቆረጥ" የሚለውን አቋም በመተው የሽግግር ጊዜ (እርከን) አስፈላጊነትን በማመን በ2010 ወደ ምርጫ ገብተዋል፡፡ ከእስር በታፈታች ማግስት ሻን ሱቺ የሽግግር ጊዜ አስፈላጊነትን ስታገል እንዲህ በማለት ገልፃ ነበር፤ "ወታደሩ ሲወድቅ ማየት አልፈልግም፤ ወታደሩ ወደ ሙያዊና እውነተኛ የአርበኝነት ሰገነት ከፍ ከፍ ብሎ ማየት እፈልጋለሁ፡፡" ወታደሩ ዴሞክራሲያዊነቱን ከማገዝ ይልቅ የራሱን ስልጣ ወደ ማደላደሉ እንደሚያደላ ብናስብም የፖለቲካ ስርዓቱ ክፍት መሆን እና የተቃዋሚዎች ተሳትፎ ቀስ በቀስ የወታደሩንና የሀገሪቱን ፍላጎት ወደ ማስታረቅ መሄዱ የማይካድ ይሆናል፡፡

በርማ ከፀነሰችው እውነታ በተቃራኒ በ97ቱ ምርጫ ሽንፈት የተነሳ የህወሓት /ኢህአዴግ አገዛዝ የጣለው የዴሞክራሲያዊ መብቶች ገደብ የፖለቲካ ቅርቃር ከመፍጠሩም በተጨማሪ የሀገሪቷንም ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ህይወት ከመሸርሸር አይዘልም፡፡ ከአዙሪቱ ለመውጣት የፖለቲካ ስነ ምህዳሩን ከመክፈት የተሻለ አማራጭ የለም፡፡ የበርማ ወታደራዊ ገዢዎችም አሸናፊ ተቃዋሚዎችን በተመሳሳይ ሁኔታ ከበተኑ በኋላ የፖለቲካ ስነ ምህዳሩን ወደ መክፈቱ ነበር የተመለሱት፡፡ የሕወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ መገንዘብ ያለበት ነገር ቢኖር የዴሞክራሲያዊ መብቶች ላይ ገደብ መጣል ለኢኮኖሚያዊ አስተዳደር ጤና ማጣት ቦይ ቀዳጅ በመሆኑ ከራሳቸው የረዥም ጊዜ ፍላጎትም ጋር መጋጨቱን መጣረሱን ነው፡፡

የፖለቲካ ስነ ምህዳሩን መክፈት አንድ አገዛዝ ስልጣኑን ሙሉ በሙሉ እንዳያጣ ለማሳመን የሚቀርብ መከራከያም ነው፡፡ ጉዳዩ መሆን ያለበት የፖለቲካ ስነ ምህዳሩን በመክፈት ሙሉ በሙሉ ከመገለል አደጋ ዋስትና ለማግኘት መጣርም ነው፡፡ በበርማ ያለው ወታደርም በትክክል ይህን ነው ያቀደው፡፡ በተመሳሳይ ሰዓት፣ የሕወሓት/ኢህአዴግ አመራርም የበላይነቱን ተቃዋሚዎችን ለማፈን ከሚጠቀምበት የሚሆነውን የሚመርጥበት ጊዜ ቢሆነው ይቀላል፡፡ አሪፉ የስልጣን አጠቃቀም ማፈኛ ማድረግ አይደለም፤ የቁንፅል ቡድኑ ጥቅሞችን ከብሔራዊ ጥቅሞች ጋር በማስታረቅ የረዥም ጊዜ ውጤት የሚያስገኘውን የፖለቲካ የለውጥ ሂደቶችን መተግባር እንጂ፡፡ ይህ ጥቅሞችን የማስታረቅ መጨረሻ የወቅቱን አገዛዝ እዚያው ባለበት የሚያልፈው ከሆነ፣ የሁሉንም ፍላጎት /ጥቅም የሚያስከብር መፍትሄ ማበጀት እስከቻለ ድረስ ነገሮች ከቁጥጥር ውጭ ወጥተው ለያዝ ገራዥ እስኪያስቸግሩ መጠበቁ ለምን ያስፈልጋል?

ተቃዋሚዎችም ሆኑ ገዢው ፓርቲ ግቦቻቸው ሊተገበሩ በሚችሉ ሁኔታዎች ላይ መመሥረት አለባቸው፡፡ ይህ አለማድረግ መፍትሄ የሌባቸው ችግሮችን ማንሳት ነው የሚሆነው፡፡ የሚፈቱ ችግሮች የሚባሉት በውስጥ ታዋቂነት በውስጣቸው አስቀድሞ መፍትሄአቸውን የያዙ ችግሮች ማለት ነው፡፡

የራሳቸውን መፍትሄ በውስጣቸው ያልያዙ ዕቅዶችን ማስቀመጥ አውዳሚ ወደሆነ ተምኔታዊነት መግባት ይሆናል፡፡ ይህም እንደሚሆን በ1967 ዘውዳዊው ሥርዓት ከወደቀ በኋላ የኢትዮጵያ ግራ ዘመም ኃይሎች በፈጸሟቸው ስህተቶችና በደረሰባቸው ውድቀት በግልጽ ታይቷል፡፡ የአቶ መለስ መንግሥት የኢትዮጵያውያንን ሥር የሰደዱ ቅሬታዎችንና የተቃዋሚ ፓርቲዎች ተግዳሮቶችን ሊያፍን አይችልም፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ የሠላማዊ ትግል ስልት የሚከተሉ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ገዢውን ፓርቲ ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ እንዲያካሂድ ሊያስገድዱት አይችሉም፡፡ በዚህ ሁኔታ የተሻለ ነገር ከማግኘትም የተነሳ ያለው አማራጭ የሁሉንም ፍላጎት እንደሁኔታው ግምት ውስጥ ያካተተ አማካይ መንገድ መከተል ነው፡፡

## ርዕሰ አንቀፅ

# ፈጣን እድገት ለማምጣት መሬትን መውረስ አያስፈልግም ! !

ኢህአዴግ እንደሚለው በኢኮኖሚው መስክ ዋነኛ ዓላማዎቹ ሁለት ናቸው፡፡ አንደኛው "በሁሉም የአገራችን ክፍሎች ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ማምጣትና ይህንኑ ያለማቋረጥ ማስቀጠል" ሲሆን ሁለተኛው ዓላማው ደግሞ "ብዙሃኑን ሕዝብ የእድገቱ ተጠቃሚ ማድረግ ነው"፤አላደረገውም እንጂ የሊዝ አዋጁም የወጣው እነዚህን ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ ነው፡፡ ፈጣን እድገት ለማምጣትና አብዛኛውን ሕዝብ በእውን ተጠቃሚ ለማድረግ መሬትን መውረስ አያስፈልግም፡፡ መሬት ሳይወረስ ፈጣን እድገት ማምጣት ይቻላል፡፡ ይህም በዓለም ላይ በግልጽ ታይቷል፡፡ ለምሳሌ ብራዚልና ሕንድ ፈጣን እድገት የሚያመጡ አገሮች ናቸው፡፡ መሬትን ግን አልወረሱም፡፡ አሜሪካ ከዓለም ኃያሉን ኢኮኖሚ ገንብታለች፡፡ መሬትን ግን አልወረሰችም፡፡

ዓለም ከተፈጠረ፣የሰው ልጅም በዚህ ዓለም ላይ መኖር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ መሬት የተያዘውና በጥቅም ላይ የዋለው በግልና በማህበር ነው፡፡ መንግሥት የሚባል ነገር ከተፈጠረም በኋላ በግል ወይም በማሕበር ያልተያዘውን መሬት የሚያዝበት የኸው አካል /መንግሥት/ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜም እንደ ሰሜን ኮሪያና ቻይና ባሉ ጥቂት የኮሚውኒስት አገሮች በስተቀር በተቀረው ዓለም መሬት የተያዘው በግል፣በማህበርና ከዚህ ውጭ የሆነው ደግሞ በመንግሥት ነው፡፡

ፈጣን እድገትን በማምጣት ስም መሬትን መውረስ የሰነፎች መንገድ ነው፡፡ ፈጣን፣ አስተማማኝና ዘላቂ እድገት የሚመጣው ከሁሉ በፊት ነፃነትን በማስፈንና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በመመሥረት ነው፡፡ ነፃነትና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በሌለበት ሁኔታ የሕዝብን ሕይወት ትርጉም ባለው መልክ የሚለውጥ አስተማማኝና ዘላቂ እድገትም ሆነ ልማት ማምጣት አይቻልም፡፡

ፈጣን እድገት የሚመጣው መሬትን በመውረስ ሳይሆን ክህሎትን የሚያስጨብጥና ምርታማነትን የሚያሳድግ ጥራት ያለው ትምህርት በመስጠት፣ፍትሐዊነትን በማስፈን፣ሕዝብን በማክበር፣ለፍትሐዊ ፍላጐቱ በመገዛትና አጋር በማድረግ፣በጥናት ላይ የተመሠረቱ ፖሊሲዎችን በመቀየስና በትጋት ተግባራዊ በማድረግ ነው፡፡ በዓለም ላይ ያሉ ኃያላን መንግሥታት የለሙትና የበለጸጉት ይህን በማድረግ ነው፡፡ መሬትን በመውረስ አይደለም፡፡

ኢህአዴግ ፈጣን ዕድገት ለማምጣት ከፈለገ መሬትን መውረስና የሊዝ አዋጅ ማውጣት አያስፈልገውም፡፡ አመጣለሁ የሚለውን ፈጣን እድገት ለማምጣት መሬት በግል መያዙ እንቅፋት አይሆንበትም፤ምክንያቱም በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 8 በግልጽ እንደተቀመጠው መንግሥት ሕዝብን ለሚጠቅም ልማት የሚፈልገውን መሬትንም ሆነ ሌላ ንብረት በፈለገው መጠን፣በፈለገው ጊዜ፣ተገቢውን ካሣ ከፍሎ መውረስ፣ለሚፈልገው ሕዝባዊ ዓላማ ለማዋልና የፈለገውን ያህል ትምህርት ቤቶችን፣የጤና ተቋማትን፣መንገዶችን፣የቁጠባ ቤቶችን፣ወዘተ ለመገንባት እንዲችል ሙሉ ሥልጣን ሰጥቶታል፡፡ የኢህአዴግ መንግሥት ትልቁ ችግሩ ለሚወርሰው ንብረት ተገቢውን ዋጋ ለመክፈል አለመፈለጉ ነው፡፡ ሕገ-መንግሥቱ መንግሥት ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የፈለገውን መሬት የመውረስ መብት ሲሰጠው ተገቢውን ካሣ የመክፈል ግዴታም ጥሎበታል፡፡ የኢህአደግ መንግሥት በመብቱ ለመጠቀም ይተጋል፡፡ ሕገ-መንግሥታዊ ግዴታውን ለመወጣት ግን አይፈልግም፡፡ መብትና ግዴታ አይነጣጠሉም፡፡ ስለዚህ የኢህአደግ መንግሥት የመረጠው አቋራጭና የሰነፍ መንገድ መሬትን መውረስ ነው፡፡ የዚህ ዓይነት አካሄድ የጉልበተኛ መንገድ ነው፡፡ የጉልበተኛ መንገድ ሕገ-ወጥ ነው፡፡ሕገ-ወጥ መንገድ ደግሞ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፡፡ የሕዝብ ቁጣ በበረታ ጊዜ አወዳደቁ የከፋ ይሆናል፡፡ ይህ እንዳይመጣ ነው ዛሬ መንግሥት ቆም ብሎ እንዲያስብና ኃላፊነት እንዲሰማው የምንወተውተው፡፡

መሬት የከፍተኛ የሀብት ምንጭ በመሆኑ በመንግሥት እጅ እስከሆነ ድረስ መንግሥትን በምንም ተዓምር ሊወጣው ወደማይችለው የሙስና አዘቅት ውስጥ ይከተዋል፡፡ ከላይ እስከ ታች ያሉ ኃላፊዎች ሥልጣናቸውን በመጠቀም መሬትን በቀላሉ ሕገ-ወጥ የግል ሃብት ማካበቻ መሣሪያ ሊያደርጉት ይችላሉ፡፡ ይህ ሊሆን እንደሚችልም በአለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ፤በተለይ ከ1997 ሃገራዊ ምርጫ በኋላ በግልጽ ታይቷል፡፡ መሬትን በተመለከተ መንግሥት ከሙስና መላቀቅ የሚችለው መሬት በግል ተይዞ መንግሥትም አስፈላጊውን ሥርዓት እያስያዘ፣እንደማንኛውም ንብረት በገበያ ሕግ ሲመራ ብቻ ነው፡፡

መሬትን የመንግሥት ማድረግ ከመድበለ ፓርቲ የዴሞክራሲ ሥርዓት አሠራር ጋር አብሮ አይሄድም፡፡ መድበለ ፓርቲ ዴሞክራሲ የፖለቲካ ፓርቲዎች በነፃነትና በእኩልነት የሚወዳደሩበትና የሚሠሩበት ሥርዓት ነው፡፡ የሚወዳደሩበት የፖለቲካ ሜዳ /ምህዳር/ የተስተካከለና ለሁሉም በእኩልነት ምቹ መሆን አለበት፡፡ የመሬት በመንግሥት መያዝ በሥልጣን ላይ ለአለው ፓርቲ በመሬት ላይ አዛዥነቱ ተገቢ ያልሆነ፣ተቀናቃኝ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሌላቸው ግዙፍ የፖለቲካ ሥልጣን ለብቻው ይሰጠዋል፡፡ በዚህ ምክንያት በሥልጣን ላይ ያለው ፓርቲ የሚደግፉትን የመትከል፣ የሚቃወሙትን የመንቀል ኃይል ይኖረዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በሃገራችን፣በተለይ በገጠሩ፣በስፋትና በተጨባጭ እየታየ ያለው ይኸው ነው፡፡ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላትና ደጋፊዎች የሆኑ አርሶ አደሮች "ፓርቲያችሁ መሬት ይስጣችሁ፤ይኸ የኢህአደግ መንግሥት መሬት ነው" እየተባሉ ከመሬታቸው ተነቅለዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ አርሶ አደሩ ከመሬቱ እንዳይነቀል በመፍራት የፖለቲካ አቋሙን በነፃነት ለመግለጽ ይፈራል፡፡ ለገዢው ፓርቲ ፍላጎትም አድርባይ ይሆናል፡፡ "ኢህአዴግ መሬት በግል የሚያዘው በመቃብሬ ላይ ነው" የሚልበት ምክንያት ግልጽ ነው፡፡ ዕድሜውን ለማራዘም አመቺ ሁኔታ ይፈጥርለታል፡፡ በዚህ ሁኔታ መድበለ ፓርቲ ዴሞክራሲ እውን ሊሆን አይችልም፡፡

ፈጣን እድገት ከማምጣት በተጨማሪ የኢህአዴግ ሌላ ዓላማ የመሬት አጠቃቀምን ፍትሐዊ ማድረግ ነው፡፡ ይህን ሁኔታ ፍትሐዊ ለማድረግ የሚቻለው መሬትን በመውረስ ሳይሆን መሬት በያዘው ላይ ፍትሐዊ ግብር በመጣልና ከግብር በሚገኘው ገንዘብ መሬት የሌለው ሰው በትምህርት፣በጤና፣በመንገድ፣በመኖሪያ ቤት፣ በፀጥታ ጥበቃ በዳኝነት ወዘተ. አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረግ ነው፡፡ በዓለም ላይ የሚታየው የተለመደው፣ተቀባይነት ያለውና ጤናማ አሠራርም ይኸው ነው፡፡

ኢህአዴግ የሊዝ አዋጅን ለማውጣት ሲያስብ፤የሚያሰማው የፈጣን እድገት ለፈፋ እንደተጠበቀ ሆኖ ሁለት ስሌቶችን የያዘ ይመስላል፡፡ ሁለቱም ስሌቶች በምርጫ ከማሸነፍ ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ አንደኛው ስሌት ለአርሶ አደሩ የይዞታ ደብተር ስለሰጠሁት ፍላጎቱን አሟልቻለሁ፤ስለዚህ ይመርጠኛል የሚል ነው፡፡ ሁለተኛው ስሌት ደግሞ ነባር ይዞታ ያለው ከተሜ ቁጥሩ በጣም ትንሽ ነው፡፡ ስለዚህ ቢያኮርፍም በምርጫ ጊዜ የሚያደርስብኝ ጉዳት አይኖርም የሚል ነው፡፡ ሁለቱም ስሌቶች የተሳሳቱ ናቸው፡፡ አንደኛ የአርሶ አደሩ ፍላጎት አልተሟላም፡፡ የአርሶ አደሩ ፍላጎት የመሬቱ ባለቤት መሆን ነው፡፡ ግን አልሆነም፡፡ ሁለተኛ ነባር ይዞታ ያለው ከተሜ ቁጥር ኢህአዴግ ከሚያሰላው ቁጥር በላይ ከፍተኛ ነው፡፡

ከሁሉ በላይ ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክም ሆነ ባህል ከመሬት ይዞታ (ከርስት) ጋር በጥብቅ የተያያዘ ነው፡፡ አባቶቻችን የሀገር ድንበርንና የመሬት ባለቤትነታቸውን /ርስታቸውን/ ለማስከበር ዘምተዋል፡፡ መስዋዕትነትም ከፍለዋል፡፡ በደማቸው ያስከበሩትን መሬት ለትውልድ አስተላልፈዋል፡፡ ዛሬም መሬት የሌለው አብዛኛው ዜጋም ቢሆን የኢኮኖሚ አቅሙን አሳድጎ፣ትንሽ መሬት በኪራይ ሳይሆን በባለቤትነት ይዞ፣ትንሽ ጎጆ ቀልሶ ከቤት ኪራይ ለመውጣትና ልጆቹን ለማሳደግ፣መነሻ ቅርስም ሊተውላቸው ይመኛል፡፡ የኢህአዴግ መንግሥት መሬትን በመውረስ የዚህን ሁሉ ዜጋ ተስፋ ነው ያጨለመው፡፡

ኢህአዴግ የሊዝ አዋጁን ማውጣት ለምን እንዳስፈለገ ሲነግረን በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ የተቀመጠውን ተግባራዊ ለማድረግ ነው ይለናል፡፡ ይህ ንዑስ አንቀጽ መሬት የመንግሥትና የሕዝብ መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡ ሕገ-መንግሥቱ በውሳኔ ሕዝብ ባይጸድቅም፣እንዲሁም በውስጡ የማንስማማባቸው አንቀጾች ቢኖሩም እንደ አንድነት እንቀበለዋለን፤እንመራበታለን፡፡ የማንስማማባቸው አንቀጾች ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት እንዲሻሻሉ እንታገላለን፡፡ በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ አከራካሪ ከሆኑና እንዲሻሻሉ ከምንሻቸው አንቀጾች አንዱ ከላይ የተጠቀሰው አንቀጽ ነው፡፡ በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) እምነት በግል የተያዘ መሬት የዚያ ግለሰብ የግል ንብረት ነው፡፡ ይህ አቋም በርካታ ዜጎች የሚያምኑበትና የተቀበሉት አቋም ነው፡፡ እንግዲህ የሊዝ አዋጁ የተመሠረተው በዜጎች ዘንድ አከራካሪ በሆነ የሕገ-መንግሥት አንቀጽ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም አንድነት የሊዝ አዋጁ ብቻ ሳይሆን አዋጁ የተመሠረተ የሕገ-መንግሥት አንቀጽም መሻሻል አለበት ብሎ ያምናል፡፡ የሊዝ አዋጁን በተመለከተ አንድነት ሦስት አማራጮችን ያቀርባል፡፡ ሥርዓቱን ተከትሎ መሻር አለበት፣ወይም መሻሻል አለበት፣ወይም ለውሳኔ ሕዝብ (ለረፈረንደም) መቅረብ አለበት፡፡

*ጋዜጣችን "ፍኖተ-ነፃነት" ብለናታል፡፡ "ፍኖት" ማለት መንገድ ማለት ሲሆን ከነፃነት ጋር ሲጣመር "የነፃነት መንገድ" ማለት ነው!!*

## ነፃ አስተየት

# የአዲስ አበባ ነዋሪን ከ85% በላይ ያለውን ደም እንባ እያስለቀሰ ያለ

ከአቤል ሰይፉ

ባለፈው በአዲሱ የጡረታ አዋጅ ዙሪያ የላኩላችሁ መልእክትና ጥቆማዬን ባለፈው በወጣው ጋዜጣችሁ በመስተናገዱ በጣም ላመሰገን እወዳለሁ፡፡

ዛሬ የምጠቁማችሁ ጥቆማ ደግሞ ሀቀኛ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ባለማወቅ ያልተቹበት፣ ነፃ ጋዜጦችም የዘነጉትን ነው፡፡

ጉዳዩ የአዲስ አበባ ነዋሪን ከ85% በላይ ያለውን ደም እንባ እያስለቀሰ ያለ ከባድ ችግር ነው፡፡ እሱም የቤት ክራይ ዋጋ ንረት ነው፡፡ በአዲስ አበባ ውስጥ የአንድ ክፍል 3m x 3m የሆነ ቤት ዋጋ ከ1000 ብር በታች የለም፡፡ ከከተማው በረዥም ርቀት ላይ ያሉ ቦታዎች ላይ ሳይቀር ቤት ክራይ በጣም ንሯል፡፡ ለትዝብት ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 3 ከ22 ማዞሪያ ወደ ኤድናሞል በሚወሰደው መንገድ አጋማሽ ላይ 17 ጤና ጣቢያ ፊት ለፊት ቦሌ ኬክ ቤት ጀርባ በተለምዶ "ጨረቃ ሠፈር" የሚባለውን ሰፈር ጐብኙ፡፡ ሽንት ቤት የለውም፤ አምቡላንስም ሆነ እሣት አደጋ አይገባም፡፡ ኮርኒሣቸው በሰው ቁመት ልክ ሆኖ የፈራረሱ ጭቃ ቤቶች ወለላቸው አፈር የሆነ 2m x 2m የሆኑ ከ600 ብር በታች የለም፡፡ ያውም ውሃ የላቸውም፤ መብራት ቀንቀን በፍፁም መጠቀም አይቻልም፡፡

እዚሁ ሠፈር ያየሁትን ጉድ ልንገራችሁ፤ በሸምበቆ የተሠራ መጠለያ፣ በላስቲክ የተሰራ መጠለያ፣ በርግጫ ቢሉት የሚወድቅ እንደ ቤት ተቆጥሮ ከ300-350 ይከራያል፡፡ ይሄ ህዝብ ከዚህ በላይ እንዴት ይንገላታ? እንዴት ይሠቃይ? ለተቃዋሚዎችስ ከዚህ በላይ አጀንዳ ከየት ሊመጣ ነው? የከተማው ህዝብ እኮ ከ85% በላይ የዚህ ሠለባ ነው፡፡ የሚገርማችሁ እዚህ ጨረቃ ሠፈር ተከራይተው የሚኖሩት ሰዎች በመንግስት፣ በግል ድርጅት ተቀጥረው የሚሠሩ፣ የተማሩ የሚባሉት ናቸው፡፡

የብሎኬት ቤት ከ1000 ብርና ከ1200 ብር በታች እንደ ሌለ ካሣንችስና 22 መብራት ጋር ጐላጉል ታወር አካባቢ ያሉ ደላሎችን ጠይቃችሁ መረዳት ትችላላችሁ፡፡ ክብሬን ያለ አንድ የመንግስት ሰራተኛ ያውም ባለ ዲግሪ ደሞዝተኛ ደሞዙን ለብሎኬት ቤት ክራይ ሰጥቶ ይራባል፤ በግሩ ይሄዳል ወዘተ . . . ክብሬን ካለለ ጨረቃ ሠፈር ገብቶ መንገድ ላይ እየተፀዳዳ ይኖራል፡፡

በዚህ ምክንያት የሴት ቢሮ ሰራተኞች ወደ ሴተኛ አዳሪነት እየገቡ ነው፡፡ እኔ የማውቃቸው አሉ፡፡ ወንዶች ለሙስና እየተጋበዙ ነው፡፡ የፍትህ አካላት ሣይቀሩ፡፡ በተለይ ሴቶቹ ቀን ቢሮ ውሎ ማታ ሽርሙጥና ተላምደዋል፤ ህዝቡም ሲሰማ መደንገጡን ትቷል፡፡ በምግብ ደረጃ ካየነው በከተማችን ያሉት ትንንሾቹ ምግቤጾች ያርከበ ሱቅ የሚባሉት ውስጥ ትንሹ የምግብ ዋጋ 10 ብር ነው፡፡

አንድ ባለዲግሪ የመንግስት ወይም የግል ተቀጣሪ ደሞዝ ከ1500 አይዘልም፡፡ ያውም ባለዲግሪ፡፡ ቤት ክራይ 1000 ብር ምግብ ርካሽ ያርከበ ሱቅ ምሣ 10 + እራት 10 ብር= 20ብር ቁርስ ተዘሎ ማለት ነው፡፡ 20x30 ቀን 600 ብር ነው፡፡ ለምግብና ለቤት ክራይ ብቻ 1600 ብር በወር ማለት ነው፡፡

ከ1500
- 1600
-100

ስልክ አለ፡፡ ትራንስፖርት አለ፡፡ የግልንፅና አለ፡፡ ታዲያ አዲስ አበባ ውስጥ ርሀብ የለም? እየታየ ያለው አንዴ ጐዳና ላይ የወጣው ነው፡፡ ሠርቶ እየተራበ ያለውን ለምን አታዩትም? ይሄኮ ግልፅ ነው፡፡

አዲስ አበባ ውስጥ የቤተሰብ ቤት የሌለው ለነብሴ ብሎ የሚያስጠጋው የሌለው በአጠቃላይ ሠራተኛውም ተምሮ በዲግሪ ደረጃ ሀገሩን የሚያገለግለው ስርቶ እየተራበ ነው:: ይሄ ግልፅ ነው፡፡ አዲስ አበባ ውስጥ ያለተራቡት ኢሕአዴጋውያን ብቻ ናቸው፡፡

ሌላው 85% ህዝብ በችጋር አለንጋ እየተገረፈ ነው፡፡ ወተት፣ ስጋ፣ ቅቤ ከተቻለ ለአመት በአል የሚገኙ ከሆነ የቅንጦት ምግቦች ናቸው፡፡ ይሄን ሁሉ ያልኩት ትንሽ መሀከለኛ ስለሚባሉት ዜጐች ነው፡፡ ዝቅተኛው ህዝብ በቀን ስራ የሚተዳረረውን በቢሮ ውስጥ አንሰተኛ ስራ የሚሠሩ ዜጐችን አበሣ ካነሳ ነው 1000 ገፅም አይበቃም፡፡

ይሄን ከተማ ውሰጥ ያለ ረሀብ፣ ችግር መከራ ስለ አላማችሁና ስለ ፈጣሪ ብላችሁ ሠፊ ሽፋን ስጥታችሁ ሥሩበት፡፡ ታች ወረዳችሁ የህዝቡን ኑሮ እዩት፡፡

ፍኖተ -ነፃነት ጋዜጣ ሐምሌ 2003 ዓ.ም ተመሠረተ፡፡ ፍኖተ ነፃነት በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ሥር የሚታተም በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ፣ በወቅታዊ ጉዳዮችና በመዝናኛ ላይ የሚያተኩር የፓርቲው ጋዜጣ ነው፡፡

**ጋዜጣችን እንደ ፓርቲ ልሳን ብቻ ሳይሆን እንደ አንድ ሚዛናዊ የግል ጋዜጣ ሆኖ ማገልገል ይፈልጋል የማንኛዉም ሰዉ ሀሳብና አመለካከት የሚስተናገድበትና የሚንሸራሸርበት እንዲሆን እንሻለን ሰፊ የሚዲያ ሽፋን ያለዉ ኢህአዴግም በዚህ ሚዲያ አቋሙንና ፖሊሲዉን ለማቅረብ ቢፈልግ ክፍት ነዉ**

ዋና አዘጋጅ፡-
አንዳርጌ መሥፍን

አድራሻ፡-
የካ ክ/ከተማ ወረዳ 12
የቤ.ቁ አዲስ

አዘጋጆች፡-
ብዙአየሁ ወንድሙ
ብስራት ወ/ሚካኤል

አምደኞች፡- ዶ/ር ኃይሉ አርዓያ
ኢ/ር ዘለቀ ረዲ
ወንድሙ ኢብሳ
ስለሞን ስዩም
ግርማ ሞገስ
ደረጀ መላኩ
ቀለሙ ሁነኛው
በለጠ ጎሹ

ኮምፒውተር ጽሑፍ፡-
የሺ ሃብቴ
ብርቱካን መንገሻ

አከፋፋይ፡-
ነብዩ ሞገስ

አሣታሚው፡-
አንድነት ለዴሞክሲና ለፍትህ ፓርቲ(አንድነት)

አድራሻ፡- አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 07 የቤ.ቁ አዲስ

አታሚ፡- ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
አራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 07 የቤ.ቁ 984

የዝግጅት ክፍሉ

ስልክ +251 922 11 17 62
+251 913 05 69 42
+251 118-44 08 40
+251 923 11 93 74

ፖ.ሳ.ቁ፡ 4222

ኢሜይል፡- fnotenetsanet@yahoo.com
udjparty@gmail.com
andinet@andinet.org

ፋክስ ቁጥር፡- +251-111226288

# ሰላማዊ ትግል እና የጋንዲ አስተዋጽኦ



ግርማ ሞገስ
(girmamoges1@gmail.com)

ክፍል ሁለት

**ከመንግስቱ ንዋይ ሙከራም ወዲህ በተለይ የኃይለ ስላሴ መንግስት መውደቂያ ግድም የተነሳው የለውጥ አራማጅ ትውልድ መሬት ለአራሹ፣ የብሔሮች/ብሔረሰቦች እኩልነት፣ የሃይማኖት እኩልነት፣ የሰብዓዊና ዲሞክራሲ መብቶች፣ ትምህርት ላልደረሰው ይዳረስ፣ ህዝብ የመንግስት ስልጣን ባለቤት ይሁን (ህዝባዊ መንግስት ይቋቋም) የሚሉትን ጥያቄዎች አንስቶ በሰላማዊ መንገድ መታገል ቢጀምርም ከታሪካችን በወረሰው የመንግስት ሽግግር ባህላዊ ምክንያትና የማርክሲዝም አለማቀፋዊ ተጽእኖ ተደማምረው የትጥቅ ትግልን ተመራጭ የትግል ዘዴ አደረገ። በዚያን ዘመን ስለጋንዲ ሰላማዊ ትግል የሚያወራ ሰው ካለ ብርቅ ነው። ካለም የሚያወራው እየተሳቀቀ ነበር ብንል ብዙም ስህተት አይሆንም። የሚያዳምጥም የሰላማዊ ትግል ወሬው ራሱ ሳይዘገንነው አይቀርም . . .**

በጋንዲ ይመራ የነበረው ብሔራዊ ኮንግረስ ያደራጀው የሰለጠነ የሰላማዊ ትግል ሰራዊት እጅግ ግዙፍ በመሆኑ የመሪዎች መታሰር ሰላማዊ ትግሉን ሊያቆመው አልቻለም ነበር። እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ከ1930 እስከ 1931ዓ. ም ድረስ በነበረው ጊዜ ውስጥ ዓብይ ስትራተጂውን ከፍጻሜ ለማድረስ ይቻል ዘንድ በህንድ ተቃውሞና ማግባባት (Protest and Persuasion)፣ ትብብር መንፈግ (non-cooperation) እና ጣልቃ መግባት (intervention) ዘመቻዎች እንደተጀመሩ የእንግሊዝ መንግስት ጋንዲን ቢያስርም የነፃነት ሰላማዊ ትግል ቀጣይነት አልተገታም ነበር። ጋንዲን በማሰር የተጀመሩትን ዘመቻዎች ማቆም ተሳናቸው። ጋንዲን በማሰር ትግሉን ማቆም የሚችሉ ይመስላቸው በነበሩት እንግሊዞች ዘንድ ሁኔታው ግራ መጋባት እና መደናገጥ ፈጠረ። በዚያን ጊዜ በተደረገ የጅምላ አፈሳ ብቻ እንግሊዞች መቶ ሺ ያህል የሰላማዊ ትግል ተሳታፊ ዜጎችን እስር ቤት እንዳጎሩና ከመቶ ሺ እስረኞች ውስጥ 17 ሺ ያህሉ ሴቶች እንደነበሩ ጂን ሻርፕ ያመለክታል። ይህም ሆኖ ለነፃነት የሚደረገው ሰላማዊ ትግል አልቆመም።

ለነፃነትና ለዲሞክራሲ የተደረገው ሰላማዊ ትግል ነፃ አልነበረም። ሰላማዊውን ትግል ለማቆም የእንግሊዝ መንግስት እንግሊዛውያን ፖሊሶችን፣ ደህንነቶችን፣ ወታደሮችንና በብዛት አድርባይ ህንዳውያንን በመጠቀም በሰላማዊ ትግል ሰራዊት ላይ ድብደባ፣ ወከባ፣ የአካል ጉዳት፣ ግድያ፣ ቤት ፍተሻና ንብረት ዝርፊያ እንዲፈጸም አድርጓል። እንዲሁም የእንግሊዝ መንግስት ሳንሱር ደንግጎ ስብሰባዎችና የተቃውሞ ሰልፎች እንዳይደረጉ አግዷል። ይሁን እንጂ እንግሊዞች የተጀመረውን ሰላማዊ ትግል ማቆም ተሳናቸው። እንዲያውም በተቃራኒው ሰላማዊው ትግል እንግሊዞችን ወደ ድርድር እንዲመጡ አስገደደ። ምክንያቱም ከፍ ብለን ያየነው ህዝባዊ ሰላማዊ የፖለቲካ ተቃውሞ (political defiance)፣ ትብብር መንፈግ እና እምቢተኛነት (disobedience) በህንድ የተተከለውን የእንግሊዝ መንግስት እንዲሽመደመድና መደበኛ ስራውን መስራት እንዳይችል አደረገ። የእንግሊዝ ኩባንያ ከህንድ እያግበሰበሰ ወደ አገሩ የሚልከውን ለኢንዱስትሪ ጠቃሚ ጥሬ እቃዎችና ማዕድን እንደቀድሞው መላክ ተሳነው። ኩባንያው ከህንድ የሚያገኛቸው ብዙ ጥቅሞች ተቋረጡበት። እንግሊዞች ከህንድ የሚፈልጉትን ማግኘት ከተሳናቸው በህንድ መኖራቸው ትርጉም እንደሚያጣ ለመገንዘብ መካሪ አላሹም ነበር። ወራሪው እንግሊዝ የተፈጠረውን ቀውስ ከድርድር በተገኘ ስምምነት በመግታት ከህንድ የሚያገኘው ጥቅም እንዳይቋረጥ ማድረግን የተሻለ አማራጭ አድርጎ እንዲወስድ ተገደደ። ስለዚህ ጋንዲ ብሔራዊ ኮንግረስን በመወከልና በህንድ የነበረው የእንግሊዝ መንግስት እንደራሴ (Viceroy) ደግሞ ቅኝ ገዢውን መንግስት በመወከል በተደረገ ድርድር ለጊዜው ሰላም ሰፈነ።

እዚህ ላይ በድርድር የተገኘው ስምምነት ያስገኛቸውን ግኝቶች (ድሎች) ብሔራዊ ኮንግረስ በትግሉ ለማስከበር መቻሉ ወይንም አለመቻሉ ወሳኝ ጉዳይ ነው። እስከዚህ ድረስ በተደረገው ሰላማዊ ትግል የነፃነት ትግሉን አቅም እንግሊዞች በሚገባ አይተዋል። ከድርድሩ በኋላ የእንግሊዝ መንግስት ከድርድር የተገኙ ስምምነቶችን አላከብርም ቢል ብሔራዊ ኮንግረሱ አዲስ ሰላማዊ ትግል ዘመቻዎች ጠርቶ የእንግሊዝን መንግስት እንደገና ማሽመድመድ እንደሚችል እንግሊዞች በደንብ ስለሚያውቁ ከድርድር የተገኙ ስምምነቶችን ለማፍረስ አልሞከሩም። ስለዚህ ጋንዲ (ብሔራዊ ኮንግረሱ) የተደራደረው ከጥንካሬ በመነሳት እንጂ ከደካማነት ወይንም ከተሸናፊነት በመነሳት አለመሆኑ ሊሰመርበት ይገባል። ምክንያቱም በድርድር የተገኙ ስምምነቶች የመከበር እጣቸው የወደቀው በእንግሊዝ መንግስት በጎ ፈቃደኛነት እጅ ሳይሆን በሰላማዊው ትግል አቅም ላይ መሆኑ ወሳኝነት ነበረው። ይህ ባይሆን ኖሮ እንግሊዞች ጊዜ ለመግዛት ያህል ድርድር እናድርግ በማለት አጭበርባሪ ስምምነት ካደረጉ በሁዋላ አቅማቸው ሲበራታ ሰላማዊ ትግሉ ቶሎ እንዳያንሰራራ አድርገው በመምታት ትግሉ ያገኛቸውን ድሎች ሁሉ ነጥቀው ወደ ቀድሞው ጠንካራ የገዢነት ቦታቸው ሊመለሱ ይችሉ ነበር። ድርድሩ የተደረገው ግን ሰላማዊ ትግሉ ከድርድር የተገኙ ስምምነቶችን የማስከበር አቅም በነበረው ጊዜ ነበር። የድርድሩን ሁኔታ አስመልክቶ ራሱ ጋንዲ ድርድሩን ሲገልጽ፥ (1) በህንድና በኢንግሊዝ መካከል በአቻነት የተደረገ እንደነበር፣ (2) የህንድን የነፃነት ሰላማዊ ትግል ህጋዊነት የለገሰ መሆኑንና (3) የህንድ ነፃ መውጣት የማይቀር ጉዳይ መሆኑን ያረጋገጠ ነበር ማለቱን ጂን ሻርፕ የሰላማዊ ትግል ፖለቲካ ክፍል 1 ገጽ 87 ላይ ያመለክታል።

ምስጢሩ ምንድን ነው? በተለይ በአፍሪካ ከቅኝ አገዛዝ ነፃ ለመውጣት የተደረጉት አብዛኛዎቹ የትጥቅ ትግሎች ያከተሙት ከውጭ ወራሪዎች ባልተናነሱ ወይንም በከፉ በነሙጋቤ አይነቶቹ ያገር ተወላጅ የአዞ እንባ ነፃ አውጭ ጨቋኝ ገዢዎች እጅ እንደሆነ አለም የሚያውቀው ሃቅ ነው። ጋንዲ የመራው ትግል ግን የህንድን ህዝብ ከቅኝ ተገዥነት ነፃ በማውጣት ሳይወሰን ከራሱ አብራክ በወጡ አምባገነኖች እንዳይገዛና ዲሞክራሲያዊ ህንድን እንዲገነባ አድርጓል። ምስጢሩ ምንድን ነው? ምስጢሩ ሰላማዊ ትግል በተፈጥሮው ከዲሞክራሲ ጋር የተቆራኘ ስለሆነ ነው። ሰላማዊ ትግል በተፈጥሮው ዲሞክራሲያዊ ጸባይ ስላለው ህዝብን የትግልና የድል ባለቤት ስለሚያደርግ ነው።

ጋንዲ የሰላማዊ ትግልን ንድፈ አሳብ በተግባር የፈተነ የመጀመሪያው ሰው ነው። ለሰላማዊ የትግል ዘዴ እድገት ከእድሜው ውስጥ 20 እና 30 አመቶች ያህል ጊዜ በቁርጠኝነት በመክፈል በግለሰብ ደረጃ ጉልህ አስተዋጽኦ አድርጓል። የጋንዲ ትልቁ አስተዋጽኦ ለስትራተጂዎችና ለታክቲኮች ትልቅ ትኩረት መስጠት እንደሚያስፈልግ እና ብዙ ጊዜ ታክቲኮች እንጂ ስትራተጂ እንደማይቀየር በተግባር ማሳየቱ ነው። ጋንዲ በሰላማዊ ትግል እድገት ላይ ማህተሙን አሳርፎ ያለፈ የእምነት ጽናት የነበረው ታላቅ መምህርና ጀግና ሰው ነበር።

የጋንዲ ተጨማሪ አስተዋጽኦ ሰላማዊ ትግልን ከፖለቲካ ግጭቶች መፍቻነት ባሻገር ማህበራዊ ግጭቶችን ለመፍታት መተኪያ የሌለው የትግል ዘዴ መሆኑን በተግባር ማሳየቱ ነው። በዚህ ረገድ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1924-25 ጋንዲ ማህበራዊ ግጭቶችን ለመፍታት ሰላማዊ ትግልን መጠቀሙንና ይህ ርምጃው በህንድ የነበረውን አጉል አምልኮታዊ ክፍፍል ለማስወገድና የካስት ስርዓትን ለማሻሻል ጥሩ ሚና መጫወቱን ጂን ሻርፕ የሰላማዊ ትግል ፖለቲካ በሚለው መጽሐፉ ክፍል 1 ገጽ 83 ላይ ያብራራል።

ጋንዲ በ1930 ዓ.ም የምግብ ጨው ህግን በመቃወም የተደረገውን የእምቢተኛነት ሰላማዊ ትግል ዘመቻና በ1942 ዓ.ም እንግሊዞች ህንድን እንዲለቁ የሚጠይቀውን ጥሪ ተከትሎ የተደረገውን ሰላማዊ ትግል በግንባር ሆኖ በጀግንነት መርቷል። በመጨረሻ እንደ አውሮፓ አቆጠጠር ነሐሴ 14 ቀን 1947 ዓ.ም ፓኪስታን ነፃ ወጣች። ነሐሴ 15 ቀን 1947 ዓ.ም ህንድ ነፃ ወጣች። የፓኪስታንን መገንጠል ጋንዲ አይደግፍም ነበር። ይሁን እንጂ የፓኪስታን መገንጠል ትግል ጥቂቶቹ ሙስሊሞች (ፓኪስታኖች) በብዙዎቹ ሂንዱዎች ይጨቆናሉ በሚል ሽፋን ተገንጣዮች ከ1920ዎቹ ጀምሮ ሲያኪያሂዱት የነበር የመገንጠል ትግል ስለሆነ እንግሊዝ ፓኪስታን ቀድማ ነፃ እንድትወጣ አደረገ። ከነፃነት ወዲህ በጥር ወር 1948 ዓ.ም ጋንዲ ከአንድ ፋይዳ ቢስ አክራሪ ግለሰብ በተተኮሰበት ጥይት ህይወቱ አለፈች። ጋንዲ ሲሞት እድሜው 78 አመት ነበር።

ከጋንዲ ወዲህም የሰላማዊ ትግል እድገት አልቆመም። እነሆ ዛሬ በእነ ጅን ሻርፕና በሌሎች አለም አቀፍ ታዋቂነት ባላቸው ምሁራን የሚመሩ እንደ እነ አልበርት አነስታይን የሰላም ትግል ምርምር ተቋም የመሰሉ ድርጅቶች ተመስርተው የሰላም ትግል ታሪክን በማሰባሰብና ንድፈ አሳቡን በማጎልመስ ላይ ይገኛሉ። በተግባርም ከጋንዲ ወዲህ በኤሲያ፣ በምስራቅ አውሮፓ፣ በላቲን አሜሪካ የሚኖረው ህዝብ ስትራተጂያዊ ሰላማዊ ትግልን በመጠቀም ከአብራኩ የወጡ አረመኔ አምባገነን ገዢዎቹን ከትከሻው አሽቀንጥሮ እየጣለ በነፃ ምርጫዎች በመረጣቸው መሪዎቹ ራሱን የማስተዳደር የሰለጠነ የፖለቲካ ባህል ለመገንባት ችሏል። እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የአረቡ ዓለም ህዝብ በሰላማዊ ትግል ራሱን ከሚዛመዱት አረመኔ አምባገነኖች ነፃ የማውጣትና ዲሞክራሲ የመገንባት ትግል ላይ መሆኑን በአይናችን እያየን ነው።

የሰው ልጅ ግጭቱን በሰላማዊ መንገድ (Non-violent Struggle) የመፍታት ባህል ከክርስቶስ ልደት በፊት ጀምሮ ቢኖረውም ለኃይል (ለሽብርና ለጦርነት) የበለጠ አድናቆት በመስጠቱ ግን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሰላማዊ ትግል ሰፊ ግንዛቤን ሳያገኝ ቀርቷል። ሆኖም ግን ዛሬ በከፊል-ሰሃራዊ አፍሪካ (Sub-Saharan Africa) ሳይቀር ሰላማዊ ትግል የተሻለ ግንዛቤና ተቀባይነት በማግኘት ላይ ነው።

መደምደሚያ፥

የመጀመሪያዎቹ የኢትዮጵያ ምሁራን እነ ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ በኢትዮጵያ የእድገት ለውጥ ለማምጣት ከፍተኛ ምኞት እንደነበራቸውና ኢትዮጵያን እንደ ጃፓን ለማድረግ የነበራቸውን ምኞት ተፈጻሚ ለማድረግ በሰላማዊ መንገድ ያልተቋረጠ ጥረት ማድረጋቸውን ባህሩ ዘውዴ የኢትዮጵያ ታሪክ [Modern History, 1855-1991] ያመለክታል። እንዲያውም አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ባሳተመው የነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ መጽሐፍ ውስጥ ምሁሩ ብዙ ጠቃሚ ምክሮችን ያነሳና መደረግ ያለባቸው ነገሮች በጊዜ ካልተፈጸሙ ወደፊት ሊደርሱ የሚችሉ ክፉ ጊዜዎችንም በትክክል የተነበየ ሲሆን ለስልጣን የሚደረግ ጦርነትም ተችቷል።

ከዚያ ወዲህ ደግሞ ጋንዲ በህንድ የነፃነት ትግል በማድረግ ላይ ሳለ የኢጣሊያን ወረራ ተከትሎ በ1928 ዓ.ም ኃይለ ስላሴ ወደ እንግሊዝ አገር ሲሄዱ በንጉሱ አገር ጥሎ መሄድ የተቆጡት የነፃነት አርበኛው ታከለ

ወደ 9 ዞሯል

**አቶ ደምሴ መንግስቱ ጃጃት የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ /አንድነት/ ፓርቲ ሥራ አስፈጻሚና የፓርቲው የህግና ሰብአዊ መብት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ናቸው፡ ፡ ስለ ግላቸው፣ ስለ ፖለቲካ ተሳትፎአቸውና ስለወቅቱ ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጨባጭ ሁኔታ በእሳቸው እይታ ምን እንደሚመስል ባልደረባችን ብዙአየሁ ወንድሙ አነጋግሮአቸዋል፡፡**



# የኢህአዴግ ባለሥልጣናት በሥልጣናቸው ለሚመጣ እንኳን ለሰው ልጅ ለፈጣሪም አይመቹም

➢ የት ተወለዱ? የት አደጉ?

የተወለድኩት በ1962 ዓ.ም በወቅቱ አጠራር ሸዋ ጠቅላይ ግዛት በሀይቆችና ቡታጅራ አውራጃ በመለቃንና ማረቆ ወረዳ ልዩ ስሙ ሰባት ጐጐት ዶቢ በሚባል ቦታ ሲሆን በልጅነቴ አጐቴ ወደ አዲስ አበባ አምጥቶኝ መርካቶ አዲሱ ሚካኤ አካባቢ አደኩኝ፡፡

➢ የተማሩባቸውን ት/ቤትዎን ቢገልጹልኝ

በቀድሞ አጠራር ጫካው ሚካኤል አሁን አዲሱ ሚካኤል ቤተክርስትያን የቄስ ትምህርት በደጃዝማች ገነሜና በኢትዮጵያ ትቅደም ት/ቤት የ1ኛ እና የ2ኛ ደረጃ ትምህርቴን ተማርኩ፡፡ በኮተቤ መምህራን ኮሌጅ በመምህርነት ዲፕሎማ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በማታው ክፍለ ጊዜ በትምህርት አስተዳደር ዲግሪ ፕሮግራም አራተኛ ዓመት ከአልፋ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ በህግ የመጀመሪያ ዲግሪ ተመርቄአለሁ፡፡

➢ የሥራ ህይወትዎና የሥራ ልምድዎስ?

በመምህርነት በምክትል ርዕሰ መምህርነትና በዩኒት አስተባባሪነት በህዝብ በሚሲዮንና በግል ት/ቤቶች ከ18 ዓመታት በላይ አገልግያለሁ፡፡

➢ እስከ ዛሬ ድረስ በፖለቲካ ውስጥ ተሳትፈው ያውቃሉ?

ጥርሴን ነቅዬ የአደግሁበት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ወንድሞቼ በኢህአፓነት በቀይ ሽብር ቢሞቱም አሻራቸውን ጥለውብኝ አልፈዋልና፡፡ ከ1985 ዓ.ም ጀምሮ እስካሁን ድረስ በተቃዋሚ ፖለቲካ ጐራ በመሳተፍ የጉራጌ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ግንባር በምክትል ፀሀፊነት፣ በደቡብ ህብረት በማዕከላዊ ኮሚቴና በድርጅት ጉዳይ መምሪያ አባልነት፣ በቀስተ ደመና አባልነት፣ የአንድነት ፓርቲ መስራች አባልና የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ አንድነት ሰብሳቢ፣ የመህል ቀጠና ማስተባበሪያና የአዲስ አበባ አንድነት ሥራ አስፈፃሚ ምክትል ሰብሳቢነት፣ በህግና ሰብአዊ መብት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ በአባልነት፣ የአንድነት ፓርቲ 2ኛ መደበኛ ጠ/ጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴ በአባልነት አገልግያለሁ፡፡ ቢበቃኝ ይሻላል፡፡

➢ የወቅቱን የአገሪቱን የፖለቲካ ሁኔታ እንዴት ይመለከቱታል?

በህገ መንግሥቱ ላይ የተጠቀሱ የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እየተጣሱ ናቸው፡፡ ሰብአዊ መብቶች የማይገሰሱ ሰዎች በመሆናችን ብቻ በተፈጥሮ የምናገኛቸው መብቶች መሆናቸው እየታወቀ በጥበቃ ስር ያሉ ዜጐች ከትዳር ጓደኞቻቸው፣ ከቅርብ ዘመዶቻቸው፣ ከጓደኞቻቸው፣ ከሃይማኖት አማካሪዎቻቸውና ከህግ አማካሪዎቻቸው ጋር እንዳይገናኙ ገደብ እየተጣለ ነው፡፡ በፍርድ ቤት ወንጀለኝነታቸውን ተረጋግጦ ፍርድ እስከሚሰጥ ትዕግስት በማጣት እንደ ወንጀለኞች መቁጠር ተጀምሮአል፡፡ በሰሩት ወንጀል ነው ከተባለ በህግ አግባብ መጠየቅ ሲቻል ተራ ድራማ በማዘጋጀት ዜጐችን ማስጨነቅና ፍርሃት ውስጥ ለመክተት እየተሞከረ ነው፡፡ በአጠቃላይ የፖለቲካው ምህዳር እየጠበበ መምጣቱን የሚያሳይ ህጋዊና ሰላማዊ ትግልን ለማጨናገፍ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ ስለ ኢትዮጵያ ሁላችንም ኢትዮጵያውያን ያገባናል ሊያገባንም ይገባል፡፡

➢ አገራችን የፀረ-ሽብር አዋጅ ማውጣቷ ይታወቃል፡፡ አዋጁን ከሕግ ሞያዊ አንፃር እንዴት ይመለከቱታል?

ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች፣ የጦር ወንጀሎች፣ የዘር ፍጅት ሽብርተኝነት እንዲሁም የባህር ላይ ዝርፊያ ወንጀል ዓለም አቀፍ ይዘት አላቸው፡፡ የዓለም መንግሥታትና ህዝቦች ያገባቸዋል ተብሎ ይገመታል፡፡ ስለሆነም የአንድነት ፓርቲ ሽብርተኝነትና አሸባሪነትን ሙሉ በሙሉ ይቃወማል፡፡ ያወግዛል፡፡ በፕሮግራሙ ላይ በግልፅ ሰፍሮ ይገኛል፡፡ አሸባሪነት አንድ ቡድን የራሱን ዓለማና ርዕዮት ዓለምን በሌሎች ላይ በሃይል ለመጫን የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው፡፡ ሽብርተኝነት ለመዋጋት ለገዥው ፓርቲ ወይም ለመንግስት ብቻ የሚተው ጉዳይ አይደለም፡፡ የሁሉም ዜጐች አገራዊና የዜግነት ግዴታ ነው፡፡ ሆኖም ግን በሽብርተኝነት ሰበብ የመንግስት ባለሥልጣናት ዜጐችን እንዳሻቸውና በአሻቸው ጊዜ ሰብአዊ መብታቸውና ክብራቸውን በመግፈፍ ማሰቃየትና ማሰር የለባቸውም፡፡ የፀረ ሽብርተኝነት አዋጁም የራሱ የሆነ ችግሮች አሉበት፡፡ በፀረ ሽብርተኝነት ህጉ አስታኮ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት፣ አመራሮችን እና ነፃ ጋዜጠኞችን ሰዶ የማሳደድ ተግባር ይታያል፡፡ የኢህአዴግ ባለሥልጣናት የሚቀርቡላቸውን አቤቱታዎች ይሰማሉ ግን አያዳምጡም፡፡ ተግባራዊም አያደርጉም፡፡ በተለይም በቅርብ ወራት የቀረበ አንድ ቀሺም “የአኬልዳማ” ድራማ መጥቀሱ በቂ ነው፡፡

## ቆይታ



➢ በእርስዎ እይታ ልማትንና ተቃዋሚዎችን እንዴት ይገመግሟቸዋል?

ስለልማት ስናስብ የህግ የበላይነት፣ የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ነጻና ገለልተኛ የፍትህ አካልን በቅድሚያ ማሰብ አለብን፡፡ ባለሀብቱ ለማልማት እንዲችል ሀብት ለማፍራት በግል ሀብቱና ንብረቱ ላይ የማዘዝና የባለቤትነት ስሜት እንዲኖረው ህግን መሠረት አድርጎ ነው፡፡ ሰብአዊ መብቱ ክብሩ መከበር አለበት፡፡ እናም ሀገራችን በምታደርገው የልማት እንቅስቃሴ ተቃዋሚዎች ሲቃወሙ አልሰማሁም፡፡ ልማት የጋራ ጉዳያችን ነው፡፡ በልማት ስም ግን ማቆሚያ የሌለው ምዝበራን መቃወም ተገቢ ነው፡፡ ለአገር ውስጥ የምግብ ፍጆታ የማይውል ለውጭ ገበያና ለአገራቸው ብቻ ምርትን ለመላክ ወደ አገራችን በልማትና በባለ ሀብትነት ስም የሚመጡትን ህዝብ ቢቃወማቸው አያስደንቅም፡፡ ምክንያቱም የተመረተው ምርት በአገር ውስጥ ፍጆታ ቅድሚያ ሊሰጡ ይገባል፡፡

➢ በአገራችን የሙስና መንሰራፋትና የመልካም አስተዳደር እጦት አስከፊ ደረጃ ላይ ደርሷል የሚሉ አሉ፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ችግሩ ቢኖርም የተጋነነ አለመሆኑን እንዲያውም እየተሻለ እና ችግሩ እየተቀረፈ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ እርስዎስ ምን ይላሉ?

ሙስና ስር እየሰደደ መምጣቱን አይካድም፡፡ በንጉሱ ዘመን የመንግሥት ባለሥልጣናት ብዙም አይታሙም ነበር ይባላል፡፡ በደርግ ዘመን ደግሞ በመቶ ብር ደረጃ ነበር በኢህአዴግ ዘመን በሺዎችና በመቶ ሺህዎች ብቻ ሳይሆን በሚሊዮኖች ደረጃ ደርሶአል፡፡ ሙስና እንደሚታወቀው በጥሬ ገንዘብ ብቻ ሳይሆን እየተባባሰ የመጣው በመሬት በመንግስት ንብረቶችና በህዝብ ሀብቶች ላይ ነው፡፡ የመንግሥት ባለሥልጣናት አይተው እንዳላዩ ሰምተው እንዳልሰሙ ይሆናሉ፡፡ በህዝብ ብርታት በሚጋለጡበት ወቅት ከአንድ የሀላፊነት ቦታ ተነስተው ወደ ሌላ የሀላፊነት ቦታ ይዘዋወራሉ፡፡ አስገራሚና አስቂኝ ጉዳይ ነው፡፡ ይህም የመልካም አስተዳደር ዕጦት ውጤት ነው፡፡ የማያዳግም እርምጃ ሲወሰድ አይታይም፡፡ የኢህአዴግ ባለሥልጣናት ከልባቸው ሙስናን ለመዋጋት ሲከጅሉ አይስተዋሉም፡፡ ሙስናን በመዋጋት ሰበብ ሌላ ሙስና ይፈጠራል፡፡ ኢህአዴጓች እኮ ለፓርቲያቸውና ለሥልጣናቸው ሲሉ የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም፡፡ ሙስናን በመዋጋት ጊዜ ማባከን አይፈልጉም፡ ፡ ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ አይነት ነው፡፡

➢ የወቅቱ ዋና ችግር ምንድ ነው ይላሉ?

የኑሮ ውድነት፣ የህግ የበላይነት አለመከበር፣ የዜግነት ክብር ማጣት፣ የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች አለመጠበቅ፣ የዜግነት ዋስትና ማጣት፣ ሙስና መልኩን ለውጦ እየተንሰራፋ መምጣት፣ በምግብ ራስን አለመቻል፡፡ የሥራ አጥነትና የመኖሪያ ቤት ዕጦት፣ የዜጐች የግል ሀብት የማፍራት መብት ጥያቄ ውስጥ መግባት፣ በአገርና በህዝብ ስም የሚፈፀሙ ብድሮች አገርና ህዝብን ከመጉዳቱም በላይ ትውልዱ ከሚሸከመው በላይ እየሆነ መምጣቱን መጥቀስ ይቻላል፡፡ እነዚህ ችግሮች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየባሱ እየሄዱ ናቸው፡፡

➢ ጠቅለል ባለ ሁኔታ በአገራችን ያለውን የህግ የበላይነትና የሰብአዊ መብት አከባበር እንዴት ይመለከቱታል?

የህገ መንግሥት የበላይነት አለመከበር፣ ህገ መንግሥቱ "የህጐች ህግ ነው፡፡" እናም "የህጐች ሁሉ የበላይ ህግ ነው፡፡" ስለሆነም በመመሪያና በቃል በሚሰጡ ትዕዛዞች ባለሥልጣናት ከህገ መንግሥቱ የሚቃረኑ ድርጊቶች ሲፈፀሙ ይስተዋላሉ፡ ፡ የፓርላማ የበላይነት አለማክበር፤ ለአብነት ያህል የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ አዋጁ ታትሞ ወጥቶ እያለ ታክሱ የሚጣልባቸው ዓመታዊ ገቢአቸው ከ500,000 ሺህ ብር በላይ መሆኑ እየታወቀ በንግዱ ማህበረሰብና በተጠቃሚው ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ አለአግባብ እንዲጣልበት ተደርጓል፡፡ የህግ አውጪው፣ የህግ አስፈፃሚውና የዳኝነት አካላት የሚታየው የተደበላለቀ አሰራር መኖር በዚህም የመንግሥትና የኢህአዴግ (የፓርቲ) ሥራ አቀላቅሎ መሥራት፣ የህግ ትርጓሜ ለፍ/ቤት ከመስጠት ይልቅ ለፌዴሬሽን ም/ቤት መሰጠት፡፡ ይህም ፖለቲካዊ መመሪያና ትዕዛዝ አዘል ትርጓሜ ለመሰጠት እንዲያስችል የታቀደ ነው፡ ፡ ከምንም በላይ የህግ የበላይነት አለመከበር፣ በተቃዋሚ ፓርቲ አባላትና ዜጐች ላይ አድሎአዊ አሰራርን አስከትሎአል፡ ፡ በይበልጥ "ሰዎች ሁሉ በህግ ፊት እኩል ናቸው፡፡" እናም "ማንም ከህግ በላይ አይደለም፡፡" የሚባሉት መሠረታዊ የህግ የበላይነት መርሆዎችን ተሸርሽረዋል፡፡

➢ በቅርቡ ወደ ሥራ አስፈፃሚ መጥተዋል፡፡ የአንድ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ነዎት እርስዎ የሚመሩት ቋሚ ኮሚቴ ኃላፊነትና ተግባር ምንድን ነው?

የፓርቲው ስትራቴጂና የአምስት ዓመት እቅድ በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብና ፕሮግራም ላይ የተጠቀሱትን ተግባራት መሠረት በማድረግ የታቀዱ ዕቅዶች አሉ፣ በህግ የበላይነት ዙሪያ ለአባላት ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በማስመልከት ትምህርት መስጠት፣ ህገ መንግስቱን በማክበርና በማስከበር አባላት የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ማድረግ፣ አባላት የህግ የምክር አገልግሎት በሚሹበት ወቅት የህግ የምክር አገልግሎት መስጠት፣ በአባላትና በዜጐች ላይ የሚደርሱ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችና የዴሞክራሲያዊ መብት አፈናዎች መረጃዎች ማሰባሰብ፡፡ ጥሰቶቹና አፈናዎቹ እንዲቆሙ መጠየቅ፡፡ ለህዝብ፣ ለአገር አቀፍና ለዓለም አቀፍ ተቋማት ማሳወቅ፣ ማጋለጥ ይገኙበታል፡፡

➢ በአሁኑ ወቅት ያለውን የአገሪቱን የወጣቶችና የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ እንዴት ያዩታል?

የወጣቶች ተሣትፎ የሚያበረታታ ቢሆንም ይበልጥ መሥራት አለበት፡፡ በብ/ም/ቤትና በ/ሥ/አ/ኮሚቴ ደረጃ ያለው ሰብጥር በቂ ነው ማለት አይቻልም፡፡ የሴቶች ተሣትፎ ቁጥር እጅግ አናሣ ነው፡፡ የአንድነት ፓርቲ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በአገር አቀፍ ደረጃ ያለ ችግር ነው፡፡ ኢህአዴግ የመንግስት ሥልጣን ይዞ የመንግስት ሀብትና የሰው ሃይል ኖሮት እኔ እስከማውቀው ድረስ አንዲት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ብቻ ናቸው ያሉት፡ ፡ ማነፃፀር አስፈላጊ ባይሆንም በቀጣይ ሂደት በድርጅት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ የወጣቶችንና የሴቶችን ተሣትፎ የማብቃት ሥራ ትኩረት የተደረገበት መሆኑን አውቃለሁ፡፡

➢ ኢህአዴግና መንግስት ምን ማድረግ አለበት ይላሉ ?

ኢህአዴግ ማለት መንግሥት ነው፡፡ መንግሥት ማለት ኢህአዴግ ነው አደረጃጀቱም ሥራውም በጀቱም የተደባለለቀ ነው፡፡ ይህ መለየት አለበት፡፡ እንደ አገር መሪ ፓርቲና እንደ መንግስት፣ የግለሰብና የቡድን ነፃነት በተገቢው ሁኔታ ማክበርና ማስከበር፣ ሀገራችን ኢትዮጵያ የሁላችን የጋራችን መሆኗን መረዳት፣ ሀላፊነት ከግል ነፃነትና ከተጠያቂነት ጋር አጣምሮ መስራት፣ ሰዶ ከማሳደድ መቆጠብ ሆደሰፊ በመሆን በውይይትና በመግባባት ልዩነቶችን ማጥበብ፣ የገጠርና የከተማ ቦታ የግል የመንግስትና የህዝብ እንዲሆን ማድረግ ምክንያቱም የመንግስት ባለሥልጣናት መሬትን ጠፍጥፈው የሰሩት ባለመሆኑ የዜጐች የጋራ የተፈጥሮ ሀብት ስለሆነ ነው፡፡ ከኢህአዴግና ከአመራሩ ጥቅም ይልቅ የአገርና የህዝብን ጥቅም ማስቀደም፡ ፡ ህዝብን አለማዋሸት፡፡ የገቡትን ቃል አለማጠፍ፡፡ በተለይም የባድመን ለእኛ ተፈረደልንና በቀን ሦስት ጊዜ እንበላለን ውሸት ሆነው በመቅረታቸው ነው፣ ሙስናን አለማመንታት መዋጋት፡፡ ለባለሥልጣናቱ ከለላ አለመሰጠት፡፡ "የኢህአዴግ ባለሥልጣናት በሥልጣናቸው የሚመጣባቸው እንኳን ለዜጋ ቀርቶ ሊፈጣሪም አመይመቹም፡፡ ቢሆንም በረዥም ጊዜያት ሥልጣን ላይ መቆየት በስልጣን መባለግን ስለሚያስከትል አክራሪ አብዮተኞች የሆኑ ባለ ሥልጣናት በራሳቸው ፈቃድ ስልጣናቸውን ቢለቁ መልካም ነው፡፡

➢ ከተቃዋሚዎችስ ምን ይጠበቃል ይላሉ?

የሚሻሻሉ ድንጋጌዎችና ህጐች እንዳሉ ሆነው ህገ መንግሥቱንና ሌሎች ህጐችን አክብሮ መንቀሳቀስ፣ የፖለቲካ ምህዳሩ ጥርቅም ብሎ እስከሚዘጋ ድረስም ቢሆን በህጋዊና በሰላማዊ መንገድ መታገል፣ በሃይልና በጦርነት አለማመን ምክንያቱም አገርንም ዜጐችንም ስለሚጐዳ፣ የምር ተቃዋሚ የሆኑ ፓርቲዎች ቢቻል እስከ ውህደት መሄድ ካልተቻለ ደግሞ በጥምረት ወይም በግንባር ለመቀናጀት መሞከር፣ ጠንካራና የዓላማ ፅናት ያላቸውን አባላት ማፍራት፣ ከህዝብና ከደጋፊዎች ጋር በተገኘው አጋጣሚዎች ለመገናኘት መሞከር፣ ከእርስ በርስ ጥላቻና መጠላለፍ መቆጠብ፡፡

➢ ህዝብስ ምን ማድረግ አለበት?

ህገ መንግሥታዊ መብትን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን እንዲከበሩ የበኩልን ድርሻ መወጣት፣ ከፍርሃትና ከጭንቀት ራስን ነፃ ማውጣት፣ ለአገርና ለህዝብ በሚጠቅሙ ጉዳዮች ላይ አለማመንታት መሳተፍ፣ በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ ኢህአዴግን ለመተካት ቆርጦ መታገል፣ የጥቂቶች መታሰርና መሞት ብቻ ነፃነት እንደማያስገኝ ተገንዝቦ በጋራና በአንድነት የኢህአዴግን አምባገነን ሥርዓትን መለወጥ፣ በኢህአዴግ ውስጥ አክራሪ አብዮተኞች እንዳሉ ሁሉ ለዘብተኛ አብዮተኞች የሆኑ አመራሮችና አባላት መኖራቸውን በመገንዘብ ጭፍን ጥላቻን አለማሳየት፡፡

## ምርጫማ ጥሩ ነው !

ምርጫማ ጥሩ ነው ጥሩ ነው ምርጫማ
"ድምፃችን ተሰርቋል" ካላላችሁማ!!
ከቶ የት ይገኛል ምርጫን የመሰለ
ከውስጥም ከውጭም ታዛቢ ከሌለ
ተቃዋሚ ፓርቲ ጠፍቶልን ከአገሩ
ቢሆን "ፅቡቅ" ነበር ምርጫ በየወሩ!!
ምርጫኮ ጥሩ ነው ክብሩ የገነነ
የምርጫ አስፈፃሚው የራስ ሰው ከሆነ!!
እንደ ምርጫ አስደሳች የት ይገኛል እስቲ
በተለይ ከሌለ ተቃዋሚ ፓርቲ!!

"ከፀሐይ በታች" የተሰኘው
ሰለሞን ሞገስ የግጥም መድብል የተወሰደ

"ከፀሐይ በታች" የተሰኘው ሰለሞን ሞገስ የግጥም መድብል ቁጥር 2 ገበያ ላይ ዋለ፡፡ ደራሲና ጋዜጠኛ ሰለሞን ሞገስ "እውነትን ሰቀሏት" በሚለው የግጥም መድበሉና በተለያዩ ጋዜጦች ላይ ይጽፍ የነበረ ነው፡፡ በአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ላይ በሚጽፋቸው ጽሑፎቹ ደረሰብኝ ባለው ጫና መጽሐፍ ማቆሙ የሚታወቅ ነው፡፡

## "ደርቢ" ኮመዲ ፊልም ሊመረቅ ነው

በአክቴት ፒክቸርስ ኃ/የተ/የግ/ማ የተዘጋጀው በደራሲ እና በዳይሬክተር አንዱዓለም ጌታቸው የተሰራው "ደርቢ" አዲስ ፊል በዓይነቱ ለየት ያለ ልብ አንጠልጣይ የፍቅር ኮሜዲ ፊልም ጥረ 27 ቀን 2004 ዓ.ም በግልና በመንግሥት ሲኒማ ቤቶች በአዲስ አበባ ተከማ በ8፡00 በ10፡00 እና በ12፡00 ሰዓት ይመረቃል፡፡

በአምባሳደር ሲኒማ፣ በሲኒማ ኢትዮጵያ፣ በሲኒማ አምፒር፣ በሴባስቶቦል ሲኒማ፣ በሲኒማ እምቢልታ፣ በአጎና ሠራዊት ሲኒማ፣ በዮፍታሄ ሲኒማ በሰበታ ጂም ሲኒማ በአቃቂ ካፍደም ለሕዝብ እይታ ይበቃል፡፡

በልዩ ፕሮግራም በአምባሳደር ሲኒማ ቤት 8፡00 ሰዓት ሚኒስትሮች፣ አምባሳደሮች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ አርቲስቶች፣ ጋዜጠኞች፣ የኪነ-ጥበብ ቤተሰቦች፣ በተገኙበት በደመቀ ሥነ-ሥርዓት ይመረቃል፡፡ ሲል ዝግጅት ክፍሉ በላከልን መግለጫ አስታውቋል፡፡

## "ተሜው" ኮመዲ ፊልም ለዕይታ በቃ

ጥበብ ኢቲ ፊልም ፕሮዳክሽን እና ኤምቢ ዲጂታል ስቱዲዮ የተዘጋጀው በደራሲ ዮሐንስ ሙሉጌታ፣ ዳንኤል ንጉሴ፣ መልካሙ ማሞ በዳይሬክተር መልካሙ ማሞ እና ዮሐንስ ሙሉጌታ የተሰራው "ተሜው" አዲስ ፊልም በዓይነቱ ለየት ያለ ልብ አንጠልጣይ ኮሜዲ ፊልም ጥር 20 ቀን 2004 ዓ.ም በግልና በመንግሥት ሲኒማ ቤቶች በክልል ከተሞች በ8፡00 በ10፡00 እና በ12፡00 ሰዓት ተመረቋል፡
፡

በቅርብ ቀን በአዲስ አበባ ከተማ የተለያዩ ሲኒማ ቤቶች እንደሚታይና የምረቃ ሥነ ሥርዓቱም እንደሚከናወን ኤም.ቢ ዲጅታል ስቱዲዮ በላከለን መግለጫ አስታውቋል፡፡

## <<ወደ መጣሁበት>> የሚለው ፊልም <<እየሩስ>> ሆኖ መጣ!

ብሩክ ከበደ



ቃልኪዳን መጽሐፍ ደራሲ መጽሐፉን ወደ ፊልም ከቀየሩት በኋላ ካዘጋጁ ጋር በተነሳው ውዝግብ ጉዳያቸው ሰበር ችሎት የደረሰው አቶ ጌታቸው አያልቄ ባለፈው ጥቅምት 15 ቀን 2004ዓ.ም በሻሎም እስቱዲዮ በተለያዩ ሚዲያዎች የሚሰሩ ጋዜጠኞችን በመሰብሰብ እየሩስ ስለተሰኘው እና በመጪው ጥር 28 ቀን 2004 ዓ.ም በሲኒማ አምባሳደርና አምፒር ስለሚለቀቀው ፊልማቸው መግለጫ ሰተዋል፡፡

በዚህ መግለጫቸው ላይ ቀደም ሲል "ወደ መጣሁበት" የተሰኘው ፊልም አንዳንድ የቴክኒክና የታሪኩ ተከታታይ ፍሰት ተስተካክሎና ስሙንም ፊልሙ ላይ ባለችው ዋንኛ ገፀ ባህርይ "እየሩስ" ስም ተሰይሞ ለተመልካች እንደሚቀርብና ደራሲውና ፕሮዲውሰሩ አቶ ጌታቸው አያልቄ ገልፀዋል፡፡

ፊልሙንም በፋይናንስ በመደገፍ እገዛ ያደረጉት አቶ አበበ ወርቁም "እኔ ለፊልሙ ገንዘብ ሣወጣ አተርፋለሁ ብዬ ሣይሆን ምንም ይሁን ምን ለሀገራችን የፊልም ዕድገት የበኩሌን እንዳደረኩ ስለሚሰማኝ ነው" በማለት የደራሲውን ሀሳብ አጠናክረውለታል፡፡ አያይዘውም "እዚህ የተሰበሰባችሁት ጋዜጠኞች እንድታስተላልፉት የምፈልገው መልዕክት ወደ መጣሁበት ፊልም እንደገና እንከኖቹን አስተካክሎ ስሙን ለውጦ የመጣ መሆኑን ነው" ካሉ በኋላ "ፖስተሩም በአዲስ መልክ ፊልሙን አጉልቶ በሚያሳይ መልኩ እንደ ሚዘጋጅ" ተናግረዋል፡፡

ይኸው ቀደም ሲል "ወደ መጣሁበት" የተባለውና አሁን "እየሩስ" የተባለው ፊልም ላይ አብይ ላቀው፣ ሳሚ በየነ፣ አልማዝ ኃይሌና ሌሎች ተዋናዮች ይተውኑበታል፡፡ ፊልሙ 1 ሰዓት በ32 ደቂቃ የሚቆይና ሰርቶ ለመጨረስ 1 ዓመት ከ6 ወር የፈጀና አንድ ሚሊዮን ብር ወጥቶበታል፡
፡ ፊልሙን ዲያሬክት ያደረገው ስንታየሁ ሲሳይ ሲሆን እንደገና ተሻሽሎና ተስተካክሎ የተሠራው በሻሎም ስቱዲዮ ባለቤት በአቶ ጥላሁን ወ/ሰንበት ነው፡፡ በፊልሙ ላይ ለተወኑት ከፍተኛ ክፍያ የተከፈለ ሲሆን ድምፃዊቷና ተዋናይዋ አቢላቀው እስከ ሁለት መቶ ሺህ ብር እንደተከፈላት ያገኘሁት መረጃ ይጠቁማል፡፡ የፊልሙ ቀረፃም ከአዲስ አበባ ውጪ ጐጃምና ጐንደር ውስጥ ተከናውኗል፡፡

ይህው ፊልም ከመመረቁ ሁለት ቀን በፊት ጥር 26 ቀን 2004 ዓ.ም 6 ኪሎ በሚገኘው የስብሰባ ማዕከል ጥሪ የተደረገላቸው ከፍተኛ የመንግስት ባለ ሥልጣኖች፣ ዲፕሎማቶች፣ የመገናኛ ብዙሃን ሰዎችና የጥበብ ባለሙያዎች በሚገኙበት ከቀኑ 10፡00 ሰዓት ለእይታ እንደሚበቃም ታውቋል፡፡

## የሊዝ አዋጁ ለመንግስትና ለሥርዓቱ እንጂ ለዜጐች የማይመች መሆኑን ኢራፓ አስታወቀ

ብዙአየሁ ወንድሙ

"የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣው አዋጅ ለመንግስትና ለሥርዓቱ እንጂ ለህዝብ ወይም ለዜጐች የማይመች የጐን ውጋት ነው፡፡" ሲል የኢትዮጵያ ራዕይ ፓርቲ (ኢራፓ) አስታወቀ፡፡ ኢራፓ ይህንን ያስታወቀው "የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት ባለቤትነት የመንግስትና የህዝብ ወይስ የህዝብና የመንግስት??" በማለት ሰሞኑን በወጣው መግለጫ ነው፡፡ መግለጫው ላይ እንደተዘረዘረው "ህብረተሰቡ የሚሰማውና የሚደመጠው ቅሬታ የባለቤትነት መብት የመንግስትና የሕዝብ ወይስ የህዝብና የመንግስት ነው የሚሉ መሠረታዊ ጥያቄዎችን በማስነሳት ላይ ይገኛል፡፡" ይላል፡፡

መግለጫው በማያያዝም "መንግስት ህዝብን ወይም ዜጐችን አገልጋይ ስለሆነ የህዝብን የባለቤትነት መብት ክርክር ውስጥ በመክተት ህዝብን እንጂ ራሱን ማስቀደም የለበትም፡፡ ከዚህ አጭርና ግልፅ የዴሞክራሲ ጽንሰ ሀሳብና ተግባራዊነት አንፃር በሀገራችን የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ በቀለም (በጽሑፍ) እንጂ በተግባር እንዳይተረጎም "ሮም በአንድ ሌሊት አልተገነባችም" በሚል የዳተኛነትን ስሜትን ዘይቤ እያራመደና ምክንያት እየፈጠረ፤ ሰበብ አስባብ እየፈለግን እነሆ ሃያ አንደኛውን ዓመት የዴሞክራሲ ሀሁ በመቁጠር ላይ እንገኛለን፡፡" ሲል ያብራራል፡፡

ባለ ሁለት ገጽ የኢራፓ መግለጫ በመጨረሻም ሲደመድም "ስለሆነም ይህ አዋጅና በመውጣት ላይ የሚገኘው የአፈፃፀም መመሪያው የዜጎቻችንን ሕገ-መንግስታዊ ነፃነት የሚፈታተን የሀገሪቱን ኢኮኖሚ የሚጎዳ ልማትንና ዕድገትን የሚገታ የዴሞክራሲ ግንባታን ጥያቄ ላይ የሚጥል በጥቂት ሀብታሞችና ብዙሃኑ ድሃ ዜጎች መካከል ከፍተኛ የኑሮና የኢኮኖሚ ክፍተት ወይም ርቀት የሚፈጥር ማህበራዊ ችግሮችን የሚያባብስ ቤተሰባዊነትን የሚሸረሽር፣ ዛሬም ሆነ ነገ ጥያቄ የሚያስነሳ ግዙፍ የማንነትና የአለኝታነት አጀንዳ በመሆኑ ሕጉ የዜግነትና ሕዝባዊነት ይዘትና ቅርፅ እንዲኖረው አዋጁን አፈፃፀሙ እንዲፈተሽ መንግስት እድሉን ለዜጎች በመስጠት የከተማ መሬት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ ተደርጎ ከመውሰድ ይልቅ የሕዝብና የመንግስት ተብሎ ለሕዝብ ድምፅ ክብደት ተሰጥቶ በሀገሩና በንብረቱ የባለቤትነት መብት ያለአንዳች ፖለቲካዊ ተፅዕኖ እንዲረጋገጥለት አበርክተን እንጠይቃለን፡፡" ሲል ይደመድማል፡
፡

### የሰመጉ ጥሪ

የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ሰመጉ) በቀድሞው የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉበኤ /ኢሰመጉ/ የቆመው ለህግ ልዕልና፣ ለዲሞክራሲና ለሰብአዊ መብቶች መከበር ነው፡
፡ የሰመጉ አባል ይሁኑ። ዓላማውን ለማስፈጽም ይችል ዘንድ በገንዘብ ይደግፉ።

ስልክ 011 551-44089/011 551-77-04
አድራሻ ሣህለ ሥላሴ ሕንፃ 8ኛ ፎቅ ከአዲስ አበባ ስታዲየም ፊት ለፊት

## በዚህ አመለካከትህ አራት 7 ማዕከላዊ ያስፈልግሐል

በኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ፀበል የተለመደ ነው። በተለይ የአእምሮ አለመረጋጋት ወይም የመንፈስ ጭንቀት ከታየ ወደ ሕክምና ባለሞያ ከመምራት ወደ ፀበል መውሰድ የተለመደ ነው፡
፡ አንድ ሰው የባህርይ ለውጥ አሳይቷል ተብሎ ለአንድ የእምነት አባት ቢነገር ያለጥጥር እዚህ ቤተ ክርስቲያን ሁለት ሰባት ወይም ሦስት ሰባት አስጠምቁት እንደሚባል አያጠራጥርም።

በሌላ በኩል ደግሞ በቅርቡ መነጋገሪያ የሆነው "በዜጐች ላይ ሽብር የፈጠረው የሽብር ሕግ" እንደተፈራውም አፈጻጸሙም ሽብር እየነዛ ነው። በየመኖሪያ ቤቱ በየመዝናኛው መነጋገሪያ መቀለጃም ከመሆን አልተረፈም። ወደ ቀልዱ ከመሄዳችን በፊት እንደ አዋጁ አፈጻጸሙ ግልጽ ነው። አንድ በሽብር የተጠረጠረ ሰው በ48 ሰዓት ውስጥ ፍ/ቤት ቀርቦ ለምርመራ ይባልና የ28 ቀን ጊዜ ቀጠሮ ይጠየቅበታል። 28 ቀን ሲሞላ ምርመራዬን አልጨረስኩም ተብሎ ሌላ ይጠየቅበታል። በዚህ ዓይነት እስከ አራት ወር ድረስ በምርመራ ማቆየት እንደሚቻል አዋጁ ለፖሊስ ሥልጣን ይሰጣል። በዚህ የምርመራ ወቅት የሚፈፀመውን ቶርችና ኢሰብአዊ ድርጊት ከአቶ ዘሪሁን ገ/እግዚአብሔር፣ውብእሸት ታዬ፣ርዕዮት ዓለሙ ናትናኤል መኮንን ለፍ/ቤቱ ሲያስረዱ ሰምተናል። የሥርዓቱን ምንነትና የአገራችን ፖሊሶች የተገነቡበትን ስብዕናም ተረድተነዋል። ወደ ጽሑፉ ቀልድ እንመለስ።

28 ቀን ወደ ፀበል አቆጣጠር ቢቀየር አራት 7 ማለት ነው። ይህንን የተረዱ ሽማግሌዎች ሲቀላለዱ የሰማሁትን ላካፍላችሁ። ሰሞኑን በአፋር አካባቢ ስለተከሰተው ግድያ ጉዳይ ተነስቶ ሞቅ ያለ ክርክር ይደረጋል። "የሞቱት ፈረንጆች የተለያየ አገር ዜግነት ያላቸው ናቸው። የኢሳያስ መንግሥት ሠላም ነሳን። ሻዕቢያን ማጥፋት ነው። እንዴት የአገራችንን ገጽታ ያበላሽብናል። እንግዲህ የሻዕቢያን መንግሥት እስከ መጨረሻው ማጥፋት ያስፈልጋል።" በማለት አንዱ ይናገራል። "ሻዕቢያ ወይም የኢሳያሳ መንግሥት ወይም ደግሞ በኤርትራ መንግሥት የሚደገፉ ሽብርተኞች የፈጠሩት መሆኑን እንዴት እርግጠኛ ሆንክ?" በማለት አንዱ ይጠይቃል። ሌላው ደግሞ በጥያቄው በመናደድ "ከመንግሥት በላይ ማን እንዲነግርህ ትፈልጋለህ? የራስህ መንግሥት የነገረህን እንዴት ትጠራጠራለህ? ነው ከተባልክ ነው።" ጥያቄ አንሺው አሁንም ጥያቄውን አላቆመም። "ሆኖ ባይገኝስ?" ይላል፡
፡ አሁንም። መልስ ሰጪ በንዴት ድምጹን ከፍ አድርጎ "ይህ የአመለካከት ችግር ነው። አንተ ከፍተኛ የአመለካከት ችግር አለብህ" ይለዋል።

ቀጠለ ጥያቄ አቅራቢው "አትንጨርጨር ምን ያንጨረጭርሐል። አመለካከትን ምን አመጣው? መረጃ ካለህ በመረጃ አስረዳኝ፡
፡ የመጠየቅ የመረዳት የማረጋገጥ መብት አለኝ። አቋም ለመውሰድ በበቂ ማስረጃ መረዳት ይገባኛል፡
፡ ይኸ የቱሪስቶች መናኸሪያ ለምን በበቂ ጥበቃ አልተሸፈነም። ጥበቃው ለደቂቃና ለሰኮንድ ክፍተት መፈጠር ነበረበት። እንዴት? መቼ?" እያለ አጣደፈው ያኛውም መልሱን ቀጠለ። "ነግሬሀለሁ አንተ የአመለካከት ችግር አለብህ። ይሄ የአገር ክህደት ነው።" ሲል ክርክሩን ዝም ብለው ይከታተሉ የነበሩ የተከራካሪው ጓደኛ ጣታቸውን ጓደኛቸው ላይ ቀስረው "በዚህ አመለካከትህ አራት 7 ከማዕከላዊ ያስፈልግሐል" ቢሉ ሁሉም ሳቀ።

ማህበራዊ

# ጊዜ ጌታ ጊዜ ከፋይ



ውብሸት ተሾመ
sfgtb7@yahoo.com

የጐንደሩ ንጉስ የነበሩት አፄ ዳዊት መምህር ኤርምያስ የተባሉ ንጉሱ ፍትህ ለመስጠት በፈርድ መንበራቸው በሚቀመጡበት ሰዓት ታላቁን የሕግ መፅሐፍ በአትሮንስ/መፅሐፍ ማንበቢያ/ላይ ዘርግተው በግዕዝ ካነበቡ በኋላ ወደ አማርኛ መልሰው ለተከሳሹ "አንተ ሞት ይገባሐል አንተ ይህን ያህል ጊዜ ትታሰራለህ "አንተ እድሜ ልክህን ትታሰራለህ - - - እያሉ የመጨረሻውን የቅጣት ፍርድ የሚወስኑ ታላቅ ባለሥልጣ ን ነበሯቸው፡፡

እኚህን መምህር ኤርመያስን ይህንን ሥልጣናቸውን የሚያውቅ ሁሉ ይፈራቸዋል፡፡ ሲያያቸውም ያለው አክብሮት ከመጠን በላይ ነው፡፡ "ጊዜ የሾመውን ጊዜ አስኪሽረው ምን ይደረጋል" እያለ ሁሉም ለመምህር ኤርምያስ ጠብ ርግፍ ይላል፡፡

መምህር ኤርምያስም በንጉሱ የዙፋን ችሎት ፍትህ ነገሥቱን እያነበቡ ብዙ ፍርዶችን ፈረዱ፡፡ የሚታሰረውን አሰሩ የተሰማቸውን እንዳሻቸው ሥልጣኑን በመጠቀም ፈረዱ፤ አሰሩ፤ፈቱ፤ሕዝብ ሁሌም መታዘብ ልማዱ ነውና መምህር ኤርምያስን ሲያያቸው እያስጎነበሰ ጉልበት እያሳመ በልቡ ግን "ጊዜ አሉ" ሲል ቆየ- - - ቀን በሳመንት ሳመንት በወር ወርም በአመት እየተፈራረቀ ያ ሕዝቡ ያለው ጊዜ ደረሰ፤ነገሩ እንዲህ ነው - - - በሰዓቱ የነበሩ የአቡነ አውስጣጢዎስና የአቡነ ተክለ ኃይማኖት የሁለቱ ገዳማት መምህራን በሃይማኖት ጉዳይ /Doctrine/ አለመግባባት ተፈጠረና ቢወያዩም መፍትሔ ላይ መድረስ ስላልቻሉ ጉዳዩን ወደ አፄ ዳዊት ወስደው በንጉሱ ችሎት እንዲታይ አደረጉ፡፡ በዚህ ሰዓት የፍትሐ ነገስቱ ሊቅ መምህር ኤርምያስም ሥራቸው ነውና በክርክሩ ወቅት እንደወትሮው ተፈርተው እና ተከብረው ተቀምጠዋል፡፡ በንጉሱ ትዕዛዝ የሁለቱ ገዳማት መምህራን ሐሳባቸውን አቀረቡ፤ከብዙ ውይይት በኋላ ንጉሱ አፄ ዳዊት የአቡነ አውስጣጢዎስ ገዳም

በዚህ ሰዓት ንጉሱ የመምህር ኤርምያስ ትምክህትና ሁኔታ ከሳቸው የተለየ ሐሳብ መያዛቸው እጅግ አስቆጥቷቸው በአስቸኳይ ወደ እስር ቤት እንዲገቡ አዘዙ፡፡ "ጊዜ አለው" የተባለው ቀን ደረሰ፤መምህር ኤርምያስም ብዙዎችን ወደላኩበት እስር ቤት ሊያስፈቱ ሳይሆን ሊታሰሩ እየተሰገደላቸው ሳይሆን እያዳፏቸው ወሰዷቸው፡፡ ሹመትና ሽረት እርግማንና መርቃት መውጣትና መውረድ መሾምና መሻር ባለበት አለም ጊዜን ተገን አድርጎ መቆም አደጋ ነው፡፡

መምህራን ያቀረቡት ሐሳብ ልክ ነው፡፡ ብለው ሲደግፉ የፍትሐ ነገስቱ ሊቅ መምህር ኤርምያስ ደግሞ በፈፁም ትክክለኞቹ የአቡነ ተክለሃይማኖት ገዳም መምህራን ናቸው አሉ፡፡

በዚህ ሰዓት ንጉሱ የመምህር ኤርምያስ ትምክህትና ሁኔታ ከሳቸው የተለየ ሐሳብ መያዛቸው እጅግ አስቆጥቷቸው በአስቸኳይ ወደ እስር ቤት እንዲገቡ አዘዙ፡፡ "ጊዜ አለው" የተባለው ቀን ደረሰ፤መምህር ኤርምያስም ብዙዎችን ወደላኩበት እስር ቤት ሊያስፈቱ ሳይሆን ሊታሰሩ እየተሰገደላቸው ሳይሆን እያዳፏቸው ወሰዷቸው፡፡ ሹመትና ሽረት እርግማንና መርቃት መውጣትና መውረድ መሾምና መሻር ባለበት አለም ጊዜን ተገን አድርጎ መቆም አደጋ ነው፡፡

ዛሬ እንደተሳቀ በፍፁም ነገ አይሳቅም፡፡ ዛሬ እንደተለቀሰ በፍፁም ነገ አይለቀስም፤ነገ አዲስ ቀን ነውና፡፡ ዛሬ ሊያስመካው የቻለ ባለዛሬ ነገን እንደዛሬው በትምክህት አልፋለሁ ካለ ስህተት ነው፡፡ የሚያስመካ ጊዜ ሳይሆን፣ሥልጣን ሳይሆን፣ሐብት ሳይሆን፣ሰርተው የሚያልፉት ወይም የሰሩት መልካም ነገር /መልካል ሥራ/ ብቻ ነው፡፡ መምህር ኤርምያስ ወደ እስር ቤት ከወረዱ በኋላ አንድም ጠያቂ ከማይጠይቃቸው እስረኞች አንዱ ሆነው ነበር፡፡ "እግዚአብሔር ያስፈታዎ" የሚል ጠፍቶ ጭራሽ ወደ ንጉሱ ዘንድ እየቀረቡ ያልሰሩትን እንደሰሩ የሰሩትንም እያባባሱ የንጉሱን ልብ አስጨከኑባቸው፡፡ ጠያቂ አልባው የትናንቱ ፈራጅ የዛሬው እስረኛ መምህር ኤርምያስም ስሜታቸው በጣም ተጎዳ፡፡

በሀገራችን ተረት "ጊዜ አይደለም ሰው ድንጋይን ያስረጃል" ይባል የለ፤በዛሬ ሀብት ወገን ሥልጣን ዘመድ ወዳጅ መመካት የጊዜን ፀባይ ያለማወቅ ውጤት ነው፡፡ ጊዜ ሲለዋወጥ ከብዙ ነገር ጋር አብሮ ይለዋወጣል፡፡ ያሰገዱ ይሰግዳሉ፣ ያሳሰሩ የታሰራሉ፣ያስገደሉ ይሞታሉ፣ ያባረሩ ይባረራሉ፣ ያስያዙ ይያዛሉ፤የጊዜን ጉዳይ ከአንድ መምህር የሰማሁትን ላክልላችሁ በልጅነት አእምሮው የ4ኛ ክፍል ተማሪ እያለ የሒሰብ አስተማሪው ምን ያህል እንዳሰቃዩት አይረሳውም፡፡ "ማስመሪያ ጣት ውስጥ በመከተት፣በማንበርከክ፣በመግረፍ - - - የእሳቸው የት/ት ክፍለ ጊዜ ለእኔና ለተማሪዎች ስቃይ ነበር፡፡ ከብዙ ጊዜ በኋላ እኔም ዩኒቨርስቲ ገብቼ በዚሁ በሒሳብ ትምህረት ተመርቄ በጥሩ ውጤት እዛው መምህር ሆኜ ተቀጠርኩ፡፡ በክረምት የትምህርት ጊዜ ያኔ የሒሳብ መምህሬ የእኔ ተማሪ ሆነው መጡ፤እሳቸው ሲመጡ ት/ት የመያዝ አቅማቸው ተዳክሟል እንደውም ከሰዓት የት/ት ክፍለ ጊዜ አልፎ አልፎ እንቅልፍ ያስቸግራቸዋል፡፡ አሁን ምን ላድርጋቸው፤ላምበርክካቸው፣ላስወጣቸው፣ልስደባቸው - - - ይህ ከእኔ አይጠበቅም ሁሉንም ለጊዜ ሰጠሁት" አለኝ፡፡

መሽቶ በነጋ ቁጥር ማሰብ ያለብን ብዙ መሾቶባቸው የነበሩ ሁሉ እንዲነጋላቸው ነው፡፡ ነግቶም ሲመሽ በዚያ ንጋት በሆነው ሥልጣናቸው ሀብታቸው ጉልበታቸው፣ጊዜያቸው ሲኩራሩ ለነበሩ ሁሉ ምሽት፣እጦት፣እስር፣ስቃይ የእጃቸው፣የግላቸው፣የላባቸው ውጤት መሆኑን ነው፡፡ ጊዜ ጌት ነው፡፡ ብዙዎችን ሽሯል፤ሾሟል፡፡ በጊዜ መኩራራት ዋጋ ቢስ ነገር ነው፡፡ ለጊዜው ታማኝ መሆን፣በጊዜው መልካም ነገር መሥራት፣በጊዜው መጠቀም ነው፡፡ መምህር ኤርምያስ ጊዜውና ቦታው ሁሌም እሳቸውን ፍርድ ሰጪ፣ወሳኝ ፈላጭ ቆራጭ አድርጎ የሚያኖራቸው መስሏቸው ነበር፡፡ ግን በጊዜው አለመጠቀማቸው ስንት አጃቢ አንዳልተከተላቸው እስር ቤት ሲገቡ ግን ጠያቂ አጡ፡፡ ጊዜ ይከፍላል የሚባለው ለዚህ ነው፡፡ መምህሩም ሁሌ መምር የሚሆኑ ይመስላቸው ነበር፡፡ ግን ጊዜ ከፋይ ነውና መልሶ ተማሪ አደረጋቸው፡፡ ጊዜ ለማንም አይወግንም፤ቀን ጠብቆ ይከሳል፡፡ "የተገፋውን ሲያነሳው የገፋውን እሱንም ይገፋዋል፡፡ ሁሉንም ለጊዜ መተው ነው" ይላሉ የአገራችን ሰዎች፤እውነት ነው፡፡ ከፋይ ለሆነው ጊዜ ነገሮችን ሁኔታዎችን የአቅምን ያህል ጥሮና ደክሞ መፍትሔ ካጡ ለጊዜው ለዳኛው መተው መፍትሔ ነው፡፡ በአለማችን ላይ ከመሪ እስከ ተመሪ ከሊቅ እስከ ደቂቅ ከሀብታም እስከ ድሃ ከምሑር እስከ ማይም ከቤተ መንግሥት እስከ ዳሰሳ ጎጆ ከሃይማኖተኛ እስከ ኢ-አማኝ ጊዜ ያልከፈለው ማንም የለም፡፡

"ከሕሊናቸው ጋር ሆነው ለዘኑና ለተከዙ ብርሃን በርቶላቸዋል፡፡ ላሳደዱና ለበደሉ የእጅ ጌጣቸው ካቴና፣ድሎት የለመደ ገላቸው የአለጋ ሲሳይ ሆኗል፡፡ ጊዜ ጌታ ጊዜ ከፋይ ነውና፡፡ ከብዙ ሰዎች አፍ የምንሰማው አንድ ነገር አለ፡፡ ጠቢቡ ሰለሞን ስለመናገሩ ጠቅሰው "ለሁሉም ጊዜ አለው" ይላሉ እውነት ነው ጠቢቡ እንዳለው እኛም ተቀብለንና አምነን አንደምንለው "ለሁሉም ጊዜ አለው" ይሄ ንግግሩ ለተገፉ መፅናኛ ሲሆን ለባለ ጊዜዎች ደግሞ ያሉበትን ሁኔታ በጥንቃቄ እንዲጠቀሙበት የሚያስገድድ ነው፡፡ ግሩም አባባል ነው፡፡ በአንድ ሀገር ይኖር የነበረ አንድ ንጉስ አንድ የልብ ወዳጅ አማካሪ ነበረው፡፡ ይህ አማካሪው ለንጉሱ የቅርብ ባለስልጣናት ከሚሰጠው ክብር በላይ ወደ ከተማው ሲወጣ ለመንገደኛው የሚሰጠው ክብር እጅግ ከፍ ያለ ነበር፡፡ ጠብ ርግፍ ብሎ ነበር መንገደኛውን፣ገበያተኛውን፣ነዋሪውን ሠላም የሚለው፤በዚህ ሰዓት ከንጉሱ ሹማምንት መካከል አንደኛው "ስማኝማ ለእኛ ከምትሰጠው ክብር በላይ ለመንገደኛው ጠብ ርግፍ ትላለህ፤ ሹማምንቱ እኛ ከመንገደኛ ጋር ምን አለህ - - -?"፡፡ አለው ያም የንጉሱ አማካሪ ለሹሙ "ክቡር ሆይ ይህ መንገደኛ ያዘነ የተቆጣ ቀን እኛ የለንም፡፡ ይንቀናል፣ይሰድበናል፣ ይረሳናል፣ ያጠፉናል፣እኛ የተቆጣን ቀን ግን እኛው እንጠፋ ይሆናል እንጅ መንገደኛው ላይ፣ኗሪው ላይ፣ገበያተኛው ላይ፣ምንም አናመጣም፤ጊዜው ሳይከፋ ከዋናው ጋር ሠላም መሆን ይሻላል ብዬ ነው ጊዜ የከፋ ቀን ምን ማምለጫ አለን ክቡር ሆይ አለው"

ቆሞ የሚናገረው አንድ ሰው ነው አድማጩ ግን ብዙ ነው፤ነጋዴው አንድ ነው፤ገበያተኛው ብዙ ነው፤አዝማሪው አንድ ነው፤አድማጩ ብዙ ነው፤ ከአንድ ብዙ ይበልጣል መልካም መስራት ቅን መሆን ለህሊና መኖር ነገ ጊዜ ሲከፍለን የምንደሰትበት ነገር ነው፡፡ መሽቶ ሲነጋ ንጋትን በፍቅር የምንጠብቀው በትናንት ሥራችን ውሳኔያችን ለህሊና የሚሆን ሥራ ከሰራን ብቻ ነው፡፡ ያለንበትን ቦታ ሥልጣን፣ ሀብት፣ ንብረት፣ዝና - - - ለማርዘም የምንጠቀምበት ነገር ከሀሰት፣ከበደል፣ከክፋት ያልፀዳ ከሆነ ረጅም ጊዜ በድሎት መኖራችን ትክክለኞች አያስብለንም፡፡ ጊዜው ሲመጣ የእጃችንን ሲከፍለን የውርደት ቀን አይመሽም እያልን እንተርታለን፡፡ "ጊዜ ጌታ፣ጊዜ ከፋይ ስንል የእጃችንን ሳናገኝ አናልፍም ማለታችን ነው፡፡" "ሰው ሁሉ የዘራውን ያጭዳል" ተብሎ የለ፡፡ ያንኑ የዘራናትን እናጭዳለን፤ከፋይ የሆነው ጊዜ የእጃችንን ይከፍለናል፡፡ ስለዚህ ሁላችንም እጃችንን ከበደል ከክፋት እናንሳ ለምን - - -? ጊዜ ጌታ ጊዜ ከፍይ ነውና!!!

# ሰላማዊ ትግል እና የጋንዲ . . .

ወልደ ሐዋሪያትና ራሳቸውን ሩፓብሊካውያን ብለው ያደራጁት የፈረንሳይ ትምህርት ቀመሶቹ ወጣት ኢትዮጵያውያን የትግላቸውን ግብ ለነፃነትና በህዝብ የተመረጠ መንግስት (ሩፓብሊክ) መመስረት አድርገው እንደነበር ነገር ግን ከነፃነት በኋላ ዘውዳዊው የኃይለ ስላሴ መንግስት ታከለ ወልደ ሐዋርያትንና ወጣቶቹን ሩፓብሊካውያን ተራ በተራ እንደበላቸው ባህሩ ዘውዴ የኢትዮጵያ ታሪክ [Modern History, 1855-1991] በሚለው መጽሐፉ ይተርካል። የነ ታከለና የወጣቶቹ ሩፓብሊካውያን ትግል ግብ ከሞላ ጎደል ከጋንዲ ትግል ግብ ጋር ይመሳሰል ነበር ማለት ነው። ኢትዮጵያውያኑ ከወራሪው ጣሊያን ነፃ ለመውጣት ጦርነትን ሲመርጡ ሩፓብሊክ ለመመስረት የመረጡት የትግል ዘዴ መጀመሪያ ላይ ከሞላ ጎደል ሰላማዊ ነበር።

ከመንግስቱ ንዋይ ሙከራም ወዲህ በተለይ የኃይለ ስላሴ መንግስት መውደቂያ ግድም የተነሳው የለውጥ አራማጅ ትውልድ መሬት ለአራሹ፣ የብሔሮች/ብሔረሰቦች እኩልነት፣ የሃይማኖት እኩልነት፣ የሰብዓዊና ዲሞክራሲ መብቶች፣ ትምህርት ላልደረሰው ይዳረስ፣ ህዝብ የመንግስት ስልጣን ባለቤት ይሁን (ህዝባዊ መንግስት ይቋቋም) የሚሉትን ጥያቄዎች አንስቶ በሰላማዊ መንገድ መታገል ቢጀምርም ከታሪካችን በወረሰው የመንግስት ሽግግር ባህላዊ ምክንያትና የማርክሲዝም አለማቀፋዊ ተጽእኖ ተደማምረው የትጥቅ ትግልን ተመራጭ የትግል ዘዴ አደረገ። በዚያን ዘመን ስለጋንዲ ሰላማዊ ትግል የሚያወራ ሰው ካለ ብርቅ ነው። ካለም የሚያወራው እየተሳቀቀ ነበር ብንል ብዙም ስህተት አይሆንም። የሚያዳምጥም የሰላማዊ ትግል ወሬው ራሱ ሳይዘገንነው አይቀርም። የጋንዲ ሰላማዊ ትግል በዚያን ዘመን የመነኩሴዎች ትግል ተደርጎ ነበር የሚታየው። ይኸው ዛሬ የስህተቱን መንገድ ካየነውና ከተማርን በኋላ የጋንዲን ሰላማዊ የትግል ዘዴ አንስተናል። የሆነው ሆኖ የሰው ልጅ ለእድገት በሚያደርገው ያልተቋረጠ ግፊት የሚሰራውን መንገድ ከመምረጡ በፊት የማይሰራውን መንገድ የመምረጡ እድል ከፍተኛ መሆኑን በታሪካችን ሳይቀር ደግመን ደጋግመን ማየታችን የሚያስደንቅ ነው።

አንዳንዴ ምነው ያኔ ከጀመርነው ሰላማዊ ትግል ዘዴ ባልወጣን ኖሮ ብለን የምንጸጸት አንጠፋም። ያኔ ሰላማዊውን የትግል ዘዴ ተከትለን ቢሆን ኖሮ ባለፉት 37 አመቶች ውስጥ ከላይ ለተዘረዘሩት ጥያቄዎች ከተሰጡት መልሶች የተሻለ የተሟላ መልስ መስጠት በቻልን ነበር። ከዘውዳዊው መንግስት በኋላ ሁለት ተከታታይ አምባገነን መንግስታት መጥተው ፍዳችንን ባላሳዩን ነበር። ያኔ ሰላማዊ ትግል ዘዴን ባለመከተላችን ኢትዮጵያን አፍርሰናል፣ ከአምባገነን ገዢዎች ዛሬም አልተላቀቅንም፣ . . . ኪሳራ ብቻ ነው ያተረፍነው!

ያለፈው አልፏል። ስላለፈው ምንም ማድረግ አንችልም። ዛሬ ማድረግ የምንችለው በየምክንያቱ ወዲህ ወዲያ ማለታችንን ትተን አፋችንና አቅማችንን አንድ አድርገን ሰላማዊ ትግልንና የምርጫ ፖለቲካን አጣምረን በመጓዝ ያልጨረስነውን የኢትዮጵያን ህዝብ የመንግስት ስልጣን ባለቤት የማድረግ ግብ ከፍጻሜ ማድረስና ለአንዴና ለሁሌ ኢትዮጵያ ፊቷን ወደ ልማትና ስልጣኔ እንድትመልስ ማድረግ ነው። በአገር ውስጥ እና በውጭ የምንኖር አፋችንንና አቅማችንን አንድ አድርገን በአንድ እጃችን ሰላማዊ ትግልንና በሌላው እጃችን የምርጫ ፖለቲካ ትግልን ይዘን መታገል ከቻልን የቀረንን አቀበት በሁለትና በሶስት አመቶች ውስጥ አገባደን ከተራራው ጫፍ መድረስ እንችላለን። ከተራራው ጫፍ ላይ ሆነን "ነፃ ህዝቦች ነን" ማለት እንችላለን። ዛሬ አቅማችንንና አፋችንን አንድ አድርገን መታገል ካልቻልን ግን የዛሬ 30 ና 40 አመቶች ግድም ትግል የጀመረው ያ ትውልድ ከተራራው ጫፍ ሳይደርስና አዲስ ቀን ለወጣቱ ትውልድ ሳያወርስ ሊያልፍ ይችላል። በየድርጅቱ ተሸሽገን በልዩነት አይን ከመተያየት እስር ቤት ነፃ ወጥተን የኢትዮጵያን ህዝብ የመንግስት ስልጣን ባለቤት በማድረግ ሌሎች ጥያቄዎቻችን መልስ የሚያገኙበትን መንገድ ተባብረን እንክፈት።

# ህመም የጠነከረባቸውን ሳገኝ በእጅጉ ረካለሁ

ብሩክ ከበደ

በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን የሰፈነው "ገብጋባነት" የሚለው ቃል ሊገልፀው ከቶ የማይደፍረውና ከዚህ በላይ የሆነ የህዝብ፣ የመንግስት፣ የሃይማኖት ተቋማትን ንብረት ያለ ምንም ሀፍረት ከመዝረፍ ታልፎ በሀብት ጉጉት የታሰረ ህሊናን ለመሙላት ልጅ ወላጆቹን፣ ባልሚስቱን፣ አሊያም ሚስት ባሏን፣ ሠራተኛ አሠሪዎቹን ወዘተ ደግሞ የማይገኝ ህይወታቸውን እንዲያጡ ሆነዋል፡፡ በዚህም የሃይማኖት መሠረት ተነቃንቋል፡፡ ሞራል ተከስክሷል፡፡ እውቀትና ሥልጣኔ የጉም ያህል በነዋል፡፡

በዚህ በብርሀን ፍጥነት በሰፈነው ፍጹም እኔነታዊ ስሜት የህዝብ መሬት የሸቀጥ ያህል ተቆጥሮ ተቸብችቧል፤ አደገኛ በሆነ በህዝብ ገንዘብና ጤንነት ላይ ከፍተኛ ጉዳት በሚያስከትሉ ህገ ወጥ ንግዶች በርካቶች ከብረዋል፡፡ ከጥበቃ ጀምሮ እስከ ሰራተኛው የሥራ ኃላፊ ድረስ እጅ እጅ ከማየት አልፈው ይህን ያህል አምጣ እስከ ማለት በመደረሱ ሕዝቡ ከጉዳዩ ይልቅ ስንት አምጣ እባል ይሆን? የሚለው ጭንቀቱ ራስምታት እየሆነበት መቷል፡፡ ተደፍሮ የሚያውቀው ብሄራዊ ባንክ ወርቁ በብረት ተለውጧል፡፡ በአቋራጭ መበልፀግ የሚሻው ዜጋ በመብዛቱም በየመንደሩ አባይ ጠንቋይ እንደ ጫጩት እየተፈለፈለ ነው፡፡ ፎቅ ውድ መኪናዎችና ውድ ጌጣጌጦች የሁሉም ምኞት መደምደሚያ እየሆኑ ናቸው፡፡ ምን ያህል ሚሊዮኖች እንደ ሚበቃቸው በውል የማያውቁትን ንፋስ አመጣሾቹ ዜጐች በየዕለቱ የሚሊዮኖችን ቁጥር ለማሣደግ የማይክሮ ሰከንድ ያህል እንኳን አያንቀላፉም፡፡

ከሁሉ የሚያሣዝነው ደግሞ ከተራበውና ከታረዘው ሕዝብ ላይ የሚቀሙትን ገንዘብ ሀይማኖታቸው እንኳን እንዳይጠይቃቸው በትንሹ ለሰባዊ ተግባር ከመፈለግ ይልቅ እርጉዝ ሚስቶቻቸው አሜሪካ ሄደው በመውለድ አሜሪካዊ ዜግነት እንዲያገኙ ማድረግ፣ በሀብታም ሀገራት ከተሞች መኖሪያ ቤታቸውን መገንባት ጨምሮ ዕቁባቶቻቸው የተንደላቀቀ ህይወት እንዲገፉ ማድረግን ጨምሮ ተመሳሳይ ኢ-ሞራላዊ ሥራዎችንም መሥራት ይኸ ሁሉ ምግባር የሚመራው ደግሞ አንዳንድ የህብረተሰቡ ክፍሎች ርዳታ ለማግኘት "ምነው የኤድስ ሰለባ በሆንኩ" እያሉ ፈጣሪቻቸውን በሚማፀኑበት ወቅት መሆኑ ደግሞ እጅግ ሰቅጣጭ ነው፡፡ ጉልት ነጋዴዎች ላይ ግብር ለመሰብሰብ የሚተጋው አካል ረጃጅም እጆች ያላቸውና በባለ ሀብት ስም ከቀረጥ ነፃ የተለያዩ ቁሣቁሶችን እንዲያስገቡ በማድረግ ሹካና ማንኪያ ሣይቀር አስመጥተው በመቸበቸብ የውድ መኪናና ፎቅ ባለቤት በመሆን አልፈው የጊቢ ማድመቂያ ሳርና አበባ መሆኑ ቀርቶ ሌላው ሚሊዮኖችን ከደሀው ህዝብ ጉሮሮ ነጥቆ የወሰደ አውቶሞቢል መሆኑ ፀሐይ የሞቀው የአደባባይ ሚስጥር ነው፡፡ እንዲህ እያልን ብንዘረዝር የጋዜጣው ገጽ ስለማይበቃን ይሄን በዚህ ላቁምና ወደ ተነሣሁበት ልመለስ፡፡

ከላይ በጥቂቱ የጠቃቀስናቸውና ዜጐች ከተባሉ ዜጐች ያሉትን ያህል ሀገራችን ጥቂት ቢሆኑም ለወገናቸው የሚጨነቁና የሚጠበቡ ልጆቿን አላጣችም ከነሱ መሀል የዛሬው እንግዳዩ አንዱ ነው፡፡

ስሙ ቢኒያም በለጠ ይባላል፡፡ ዕድሜው 35 ነው፡፡ የሚኖረውም ሆነ ሰብአዊ አገልግሎቱን የሚሰጠው ኮተቤ ብረታ ብረት ፋብሪካ አጠገብ ገደራ ሆቴል ጀርባ በየካ ክፍለ ከተማ በወረዳ 09 ቀበሌ 22 የቤት ቁጥር 769 በሚገኘው የወላጆቹ ቤት ነው፡፡ ወላጆቹን ጨምሮ ሰባት ወንድሞቹ በሙሉ ሀገር ቤት ስለሌሉ ብቻውን ያለውን ትልቁንና ባለ በርካታ ክፍሉን ቪላ ቤት የሚያስተዳድረው እራሱ ነው፡፡

ወጣቱ ይህን በግምብ የታጠረና በግሩም ጥርብ ድንጋይና ጠጠር የታነፀውን ቪላ እያከራየ እንደልቡ እየተደሰተ አሥራሽ ምቹው ቢያስብ አሁን ባለው የቤት ኪራይ ገበያ ቢያንስ በወር 40 ሺህ ብር ያከራየዋል፡፡ ይህ ሀሳብ ግን በዚህ ወጣት አዕምሮ የተወገዘ ርኩስ ምግባር



ነው፡፡

የስነ ምግባር በድኑ ደዌ ተይዘው መንቀሣቀስ የማይችሉ፣ መፀዳዳትና መመገብ የተሣናቸው በዕድሜ የገፉ አረጋውያንና በአዕምሮ ህመም የሚሠቃዩ ወገኖችን ከተለያዩ የሀገሪቷ ክልሎች በማሰባሰብ መርዳት እንዲሁም በአካባቢው ለሚገኙ የችግረኛ ቤሰሰብ ልጆች በተመላላሽነት የምግብ፣ የልብስና የትምህርት መረጃ መሣሪያዎችን አቅሙ በፈቀደ መጠን ማቅረብ ነው፡፡ የወጣቱ አእምሮ የሚረካው በሽታ የፀናባቸውን ወገኖችን አግኝቶ ሲረዳ ብቻ ነው፡፡

"እነዚህ ወገኖች ከቶ ማን አላቸው?" ሲልም ማንኛችንም ልንመልሰው የማንችለውን ትልቅ ጥያቄ ያቀርባል፡፡ "ሜቄዶኒያ ሂማኔቴሪያን አሶሴሽን" ሲል እንደሰየመው መግቢያው በር ላይ በሰቀለው ማስታወቂያ የሚገልፀው ድርጅቱም ከበጐ አድራጐት ድርጅትና ማህበራት ኤጀንሲ ፈቃድ እንዳለው ይናገራል፡፡

ድርጅቱ የተመሠረተው ከ5 ዓመት በፊት በመንደሩ የሚገኙ ችግረኛ ልጆችን በመርዳት ነበር፡፡ በጊዜውም ወጣት ቢኒያም በለጠ አሜሪካ ሆኖ ጓደኞቹ ጥቂት ሠራተኞችን ቀጥረው ሥራውን እንዲያካሄዱ ቢያደርግም አደራውን የተቀበሉት ብዙም በሥራው ላይ ስሜት ስላልነበራቸው እንደፈለገው ሊያስኬዱለት ስላልቻሉ ከሁለት ዓመት በፊት ጓዙን ጠቅሎ ከአሜሪካ መጣ፡፡ እዚህም እንደደረሰ የአረጋውያኑን ሥራ አክሎበት ድርጅቱን መምራት ጀመረ፡፡

ሥራውን በበጐ ፍቃደኞች ማለትም በገዳም መናንያን ስለሚሸፈን ሰባት ሠራተኞች ብቻ ናቸው ተቀጣሪዎች ያሉት፡፡ ቤቱ የግል በመሆኑም የኪራይ ወጪ የለበትም፡፡ ከየትኛውም ድርጅት ሆነ ግለሰብ ምንም ዓይነት እገዛ እንደማይደረግለት የሚገልጸው ቢኒያም አእምሮ ህመምተኛ የሆኑ አረጋውያንን ለመንከባከብ ያሳሰበውም እነዚህን የተጣሉ ወገኖችን የሚረዳ ድርጅት በሀገራችን እምብዛም ስለሌለ እንደ ሆነ ይናገራል፡፡

ብቻቸውን ከሚያወሩት፣ ከሚለፈልፉትና፣ ከሚቆዝሙት እንዲሁም አልጋ ላይ ተኝተው በካቲተር (ፕላስቲክ ቱቦ) የሚፀዳዱ፣ የሚሣደቡ፣ አረጋውያንን ለተመለከተ ሰብአዊ ተግባሩ እጅግ ፈታኝ መሆኑን ለመገመት የግድ ነብይ መሆን አይጠይቅም፡፡

ወጣቱም ስማቸውን እየጠራና በፍቅር እያናገራቸው ዙሪያውን ካስጐበኘን በኋላ አንድ ቦታ ቆም ብሎ ውጪ ሰብሰብ ብለው ወደ ተቀመጡት ጣቱን እያመላከተ "እዚህ ቤት ውስጥ የምታይዋቸው አሣዛኝ አረጋውያን የተሰበሰቡት ከደብረ ዘይት፣ ደብረ ብርሃን፣ አዋሣ፣ ደብረ ሊባኖስ ሲሆን ከአዲስ አበባ ደግሞ ከዮሐንስና ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ጨምሮ ከጐዳና ያሰባስብናቸው ናቸው፡፡" በማለት ከየት እንዳመጧቸው ገለፃ ካደረገ በኋላ በማገገም ላይ ወደሚገኙት አረጋውያንና ጐልማሶች እያመላከተ "ያኛው ሳምሶን ይባላል፡፡ ሣሚ በተቀመጠበት የሚፀዳዳ፣ በሽክም የመጣ ነበር፡፡ ያቺ ደግሞ ቤተሰብ መንከባከብ ሲያቅተው አውጥቶ ከጣላት መሀል አንዷ ናት፡፡ ስሟም አበሩ ይባላል፡፡ ሀብታምም ነበረች፡፡ አበሩ ላምበረት አካባቢ ወድቃ የተገኘች ናት፡፡ እኒኛው ደግሞ" አለ፡፡ በረንዳ ላይ ተቀምጠው ልብስ የሚሰፉትን እያሣየኝ "ለ3 ወር የአልጋ ቁረኛ የነበሩና በህክምና ድነው በሙያቸው እያገለገሉን ይገኛሉ፡፡" በማለት ተርኮልኛል፡፡

ተረጂዎቹስ ምን ይላሉ? ኃ/ማርያም ወርቅነህ ይባላሉ፡፡ ጣሊያን ሲገባ የ5 ዓመት ልጅ እንደነበሩ ይናገራሉ፡፡ የትውልድ አገራቸው ፍቼ ቆላ ውስጥ ነው፡፡ ገበሬ እንደነበሩና በእግራቸው ህመም የተነሣ ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም በመምጣት መንገድ ላይ ወድቀው ሌት በቁር ቀን በሀሩር ሲጠበሱ እንደቆዩ ያስታውሳሉ፡፡ በተለይ ደግሞ "ፃድቃን የሚሰጡኝን ወሮበላው እየቀማኝ ምንም ሣልቀምስ የምውልበት ቀናት ብዙ ጊዜ ያጋጥመኛል፡፡ ከጊዜ በኋላ ደግሞ ሁለቱም ዓይኔ ማየት በማቆሙ ችግሬ የመረረ ነው" የሚሉት አቶ ኃ/ማርያም ወደ ዚህ መጠለያ ከመጡ ግን በጥሩ ሁኔታ እንደተያዙ ገልፀው ምርቃታቸውን ያዥጐደጉዳሉ፡፡

ሌላው ተረጂ አቶ ማሞ ይፍሩ ናቸው፡፡ የመጡት አዲስ አበባ ልደታ ክ/ከተማ ከቀበሌ 49 ጎዳና ላይ ነው፡፡ 1928 ዓ.ም ወሊሶ ቢወለዱም በ1948 ዓ.ም ሥራ ፍለጋ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት መንገድ ሥራ ድርጅት ውስጥ በመቀጠር በተለያዩ የሀገሪቷ ክ/ሀገሮች አውራ ጐዳና ሲቀደድ በሙያቸው አገልግለዋል፡፡

ከሠሩዋቸው ሥራዎች መሀል ከእስራኤሎች ጋር በመሆን ከአዲስ አበባ በሲዳሞ በኩል የኬኒያን መንገድ፣ "ትራፐ" ከሚባል የጀርመን ኩባንያ ጋርም ከአዲስ አበባ አሰብ መንገድ፣ ከጣሊያኖች ጋር ከአዲስ አበባ ለቀምት ጊንቢ የተዘረጉት በምሳሌነት ያስታውሳሉ፡፡ ደርግ ስልጣን ከያዘ በኋላ የውጪ ካምፓኒዎች ከሀገር በመውጣታቸው ሌላ ሥራ ላይ ተሠማርተው እንደቆዩና ከጊዜ በኋላ ግን ጉልበታቸው እየደከመ ሲሄድ ለልመና ጎዳና ለመውጣት እነደተገደዱና ምንም ቤተሰብ እንዳልመሰረቱ በሀዘን ይናገራሉ፡፡ ወደዚህ ምግባረ ሰናይ ቤት ከመጡም ዓመት ሊሆናቸው እንደተቃረበና ወጣቱም በአቅሙ አስፈላጊውን ሁሉ እንክብካቤ እንደሚያደርግላቸው ገልጸዋል፡፡

ወጣት ቢኒያም በለጠ የበጐ ምግባር ሥራውን ተዟዙሮ ካስጐበኘኝ በኋላ በውስጤ አንድ ጥያቄ ተጫረብኝ፡፡ ይህን የመሰለ ከባድ የወገን ፍቅር የህሊና ዕረፍትና የሃይማኖት ግዴታ እንዲሁ ዝም ብሎ አይመጣምና "ለዚህ መሠረት የሆነህ ምንድን ነው?" የሚል ጥያቄ አነሳሁበት፡፡ እሱም "አሁን አሜሪካ የሚኖረው አባቴ የሼል ኩባንያ የስራ ኃላፊ ነበር፡፡ እዚህ በነበረበት ወቅት በቤታችን ከ20 የሚበልጡ ነዳያኖች፣ መነኩሴዎች የኖሩ ነበር፡፡ ከነሱ ውጪ ደግሞ በአካባቢያችን የሚገኘው ማንኛውም የተቸገረ ሰው ሁሉ ቤታችን ቤቱ ነው፡፡ ይህን እያየሁ ስላደኩ ይመስለኛል ወደዚህ ተግባር የተሳብኩት፡፡ ይህ ደግሞ የኔ ብቻ ሳይሆን የመላው ቤተሰብ ስሜት ነው፡፡ በአንድ ወቅት አባቴን የሚያውቀው ጋዜጠኛና ተዋናዩ ተፈሪ አለሙ የምሰራውን ከጐበኘ በኋላ አንተም የአባትህን ተግባር ቀጠልክበት" እንዳለው ያስታውሳል፡፡

አዎ! . . . ዛሬ አስከፊው ሙስና በየትኛውም አቅጣጫ በዓይነትና በስፋት መጠኑን ጨምሮ በከፍተኛ ደረጃ ተስፋፍቶና ተሰራጭቶ የሚገኝበት አገር አንድ በጐ ስራ ሲገኝ ያንሁሉ እርኩስ ተግባር እንዴት ደፍጥጦት እንደሚታይ ይሄ በራሱ በቂ ማስረጃ ነው፡፡ የሜቄዶኒያን ሂማኔቴሬያን አሶሴሽን ድርጅትንም በቅርቡ የኪነ-ጥበብ ባለሞያዎች እንዲጐበኙት ለማድረግ እቅድ መያዙን ተቆሙን እንድጐበኝ መረጃውን የሰጠኝ ጋዜጠኛ አባተ ማንደፍሮ ገልፆልኛል፡፡



# ባልቴቷ ቤቴን ተቀማሁ እያሉ ነው

በብሩክ ከበደ

ነዋሪነታቸው በልደታ ክ/ከተማ በወረዳ 5 ቀበሌ 10/30 በቤት ቁጥር 430(ሀ) የሆነው ወ/ሮ ሙና ጀማል "ዘጠኝ ልጆቼን ያለአባት የማሣድግበትን የንግድ ቤት ተቀማሁ" ሲሉ ለጋዜጣው ዝግጅት ክፍል አቤቱታቸውን አቀረቡ፡፡

እንደ ወ/ሮ ሙና አባባል ከሆነ "ለምግብ እንጂ ለሥራ ያልደረሱ ዘጠኝ ልጆቼን የማሣድግበት የሸቀጣሸቀጥ ሱቅ አመታዊ ግብር ዘጠኝ ሺህ ብር ክፈይ ተብዬ የክፍያው መጠን አቅሜን ያላገናዘበ ነው ስል አቤቱታዬን አቀርቤና ምላሽ ባለገኘሁበት ሁኔታና አሁን በህይወት የሌለው ባለቤቴ ህክምና የተበደርኩትን ከፍተኛ ገንዘብ በሂደት እቀንሣለሁ በሚል ከሱቁ ጐን ለጫት ንግድ ያከራየሁትን ቤት ያከራይ ተከራይ መመሪያ ነው በሚል ተነጥቄያለሁ" ብለዋል፡፡

አያይዘውም "ነገሩ አግባብ እንዳልሆነና እኔም ተመላላሽ የአማኑኤል ሆስፒታል ተካሚ መሆኔና የዘጠኝ ህፃናትን አሳዳጊነቴን ገልጬ ለልደታ ክ/ከተማ ዲዛይንና ግንባታ ጽ/ቤት አመልክቼ ግለሰቡ ፎርም እንደማይሞላና አግባብ እንዳልሆነ በቀበሌው በኩል ከተገለፀልኝ በኋላ ቤቴን ተቀምቻለሁ" ይላሉ፡፡ ግለሰቧም የአማኑኤል አዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ተመላላሽ ታካሚ ለመሆናቸው ከሆስፒታሉ በካርድ ቁጥር 10916 የተመዘገቡበት ማስረጃ ያመለክታል፡፡

ይኸ በዚህ እንዳለም በአንዳንድ ቀበሌዎች በአሁኑ ጊዜ በጨረታ የሚሰጥን የንግድ ቤት ጨምሮ አዲሱን የንግድ ቤት የአከራይ ተከራይ ውል ለማስሞላት በጉቦ መልክ ከፍተኛ ገንዘብ እየተጠየቅን ነው የሚሉት ባለ ጉዳዮች ከነሱ መሀል አንድ የንግድ ቤትን ላለማግኘት 10 ሺህ ብር አምጡ የተባሉ ነጋዴ የቀበሌውን ሠራተኛ በፀረ ሙስና ማስያዛቸውን ይናገራሉ፡፡ ሌላው በትርፍነት በተወረሱ መኖሪያ ቤቶች ውስጥ የግል ቤት ያላቸው ባለ ጉዳይም ከአቅማቸው በላይ የሆነ ክፍያ ተጠይቀው ቢከፍሉም ካርታቸውን ለማግኘት መመላለሱ ቢሰለቻቸውም አንድ ጋዜጠኛን ይዘው በመሄድ ወዲያውኑ ማግኘት መቻላቸውን ይናገራሉ፡፡ እነዚህንና ሌሎች የህዝቡን ያፈጠጡ ችግሮች በቀርብ የሚከታተሉ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ ግለሰብ "የዘረፈውን ስያሜ ሙስና እያልኩ ላንቆለጳጵሰው ስለማልፈልግ ንጥቂያው በየትኛውም አገልግሎት ዘርፍ እጅግ ዘግናኝ ደረጃ መድረሱን አስረግጬ ልነግርህ እችላለሁ፡፡ እኔ ጠቅላይ ሚ/ሩ ብሆን የፀረ ሙስና ኮሚሽን የበላይ ተጠሪ የሚለውን መጠሪያ አነሣ ነበር" ብለዋል፡፡



# በእነ አንዱዓለም ክስ ላይ ብይን ተሰጠ

ብስራት ወ/ሚካኤል

“ፍርዱ ቀድሞ ከቤተመንግስት የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ አይገርመንም” አቶ አንዱዓለም አራጌ

“ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲያውቅልኝ እፈልጋለሁ፤ ነፃ ሰው ነኝ” ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ

“ፍ/ቤቱ እንኳ ነፃ ባለኝ ክስ ላይ ኢቴቪ ወንጀለኛ አድርጐ እያቀረበ ስለሆነ እርምጃ ሊወሰድ ይገባ ነበር” አቶ ክንፈሚካኤል ደበበ

በፌደራል አቃቤ ህግ በ “ሽብር” ተግባር ተጠርጥረው በፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት 3ኛ ወንጀል ችሎት ክስ በተመሰረተባቸው በነ አንዱዓለም አራጌ ላይ ፍ/ቤቱ ብይን ሰጠ፡፡

ጥር 15 ቀን 2004 ዓ.ም ለ3ኛ ጊዜ ብይን ለመስጠት ፍ/ቤቱ ለ8 ሰዓት ቀነ ቀጠሮ ሰጥቶ ቢሆንም እንደተለመደው ዘግይቶ በ8፡50 ሰዓት ላይ ችሎቱ ተሰይሞ ብይን ሰጥቷል፡፡

ተጠርጣሪዎቹ ከተመሰረተባቸው 6 ክስ ውስጥ በ1ኛው ክስ “የሽብርተኝነት ድርጊቶችን ለመፈፀም በማሴር፣ በማቀድ፣ በማነሳሳትና በመዘጋጀት ወንጀል”፣ በ2ኛው ክስ “በሽብርተኝነት ድርጅት ውስጥ በአመራርነት፣ ውሳኔ ሰጭነት፣ ሰዎች በመመልመል፣ ወንጀል”፣ በ4ኛው ክስ “በፈጸሙት ከፍ ያለ ክዳት ወንጀል” እና በ6ኛው ክስ “የሙያ ድጋፋቸውን በመስጠታቸው በፈጸሙት በዋና ወንጀል አድራጊነት ለሽብርተኝነት ድርጅት ድጋፍ መስጠት ወንጀል” የሚል ክስ ላይ እንዲከላከሉ ፍ/ቤቱ የጥፋተኝነት ብይን ሰጥቷል፡፡ በ6ኛው ክስ የተከሰሱት ጋዜጠኛ መስፍን ነጋሽ እና አብይ ተ/ማርያም ናቸው፡፡

በ3ኛው እና በ5ኛው ክስ ላይ ክስ የተመሠረተባቸው ሰዎች ራሳቸውን መከላከል ሳያስፈልጋቸው ፍ/ቤቱ ነፃ ናቸው ብሏቸዋል፡፡ በሌሉበት ጉዳያቸው የታየውና ነፃ ናችሁ በተባሉበት በ3ኛው ክስ ላይ የሚገኙት ደሳለኝ አራጌ እና ኤልያስ ሞላ ሲሆኑ ተጠርጣሪዎቹ ላይ የተጠረጠሩበትን ወንጀል የሚያሳይ በቂ ማስረጃ ባለመቅረቡ ፍ/ቤቱ ነፃ ናቸው ብሏቸዋል፡፡ በ5ኛው ክስ ላይ ግን በክስ መዝገቡ ላይ የተጠቀሱትን በሙሉ የሚመለከት ሲሆን ክሱም “በፈፀሙት በስለላ ወንጀል” የሚል ሲሆን ይህንንም ፍ/ቤቱ ውድቅ በማድረግ ተከሳሾቹን መከላከል ሳያስፈልጋቸው ነፃ ናቸው ብሏቸዋል፡፡

አቶ አንዱዓለም አራጌ በችሎቱ “በተደጋጋሚ ጠቅላይ ሚኒስትሩን በፓርላማ ጨምሮ በአዲስ ዘመን፣ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ ድርጅት ጉዳያችን ገና በፍ/ቤት እየታየ ሳለ የሚፈፀምብን በደል እንዳለ ለፍ/ቤቱ አቤቱታ ብናቀርብም ተቀባይነት ባለማግኘቱ አሁን የተፈረደብን ቀድሞ ከቤተመንግሥት ጀምሮ በመንግሥት መገናኛ ብዙኃን የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ አዲስ ስላልሆነ አይገርመንም፡፡ ነገር ግን በነዚህ ተቋማት የፍ/ቤቱ ስልጣን የተጣሰ ስለሆነ እውነት ፍ/ቤቱ ለኢትዮጵያ ህዝብና ለፍትህ የሚሰራ ከሆነ የተፈፀመብንን በደል አይቶ እርምጃ ሊወስድ ይገባ ነበር፡፡” ሲሉ ፍ/ቤቱም “ችሎት እየተዳፈርክ ነው፤ ይህ አነጋገር ሊያስቀጣህ ይችላል” ሲል ገስፃቸዋል፡፡

አቶ አንዱዓለም አራጌም “ፍ/ቤቱ ሊያስፈራራኝ አይገባም” ሲሉ ፍ/ቤቱ “ድጋሚ እንዲህ እንዳትናገር፤ ፍ/ቤቱ የራሱ የሆነ ሥርዓት አለው፣ የምትናገረው ቃል ተገቢ አይደለም፤ ቅሬታ ካለ ህግን ተከትላችሁ በአግባቡ ማቅረብ ትችላላችሁ” ብሏል፡፡

አቶ ክንፈሚካኤል በረደድ በበኩላቸው “በ5ኛው ክስ ላይ የስለላ ተግባር በመፈፀም ለአሸባሪዎችና ለኤርትራ መንግስት ተላላኪ ሆኖአል የሚል ቢቀርብብኝም ፍ/ቤቱ እራሱ በቂ ማስረጃ ባለመቅረቡ ውድቅ አድርጐታል፡፡ ነገር ግን ኢቴቪ እኔን ከኤርትራ መሪ ኢሳይያስ አፈወርቂ ጋር እያይዞ እያቀረበ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ተገንዝቦ እርምጃ ሊወስድልን ይገባ ነበር፡፡” ሲሉ ፍ/ቤቱ በበኩሉ አቤቱታቸውን ውድቅ በማድረግ “ይሄ የስብሰባ ቦታ አይደለም፣ ፍ/ቤቱ የራሱ ስርዓት አለው፣ የምትናገሩት ቃል አግባብ አይደለም” ሲል አቤቱታቸውን ውድቅ አድርጐታል፡፡

በመጨረሻም የተከሳሾችን መከላከያ ማስረጃና ምስክር ለመስማት ተከላካይ ጠበቆች “የቀረቡብንን ክሶችና ማስረጃዎች መርምረን መከላከያ ማስረጃ ማቅረብ እንድንችል ከአንድ ወር ያላነሰ ጊዜ ይሰጠን” በማለታቸው ፍ/ቤቱ ተከላካይ ጠበቆች የሰነድ ኮፒዎችን ለአቃቤ ህግ እንዲሰጡ እና ዝርዝር የሰው ማስረጃዎችን ለጽ/ቤቱ እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ ሰጥቶ የመከላከያ ማስረጃ ለማየትና ለመስማት ጠዋት የካቲት 26 እና 27 ቀን 2004 ዓ.ም ቀነ ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡

ችሎቱ እንዳበቃም ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ “እኔ ከግንቦት 7 ጋር ምንም ኣይነት ግንኙነትም ሆነ ንክኪ የለኝም፤ ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲያውቅልኝ እፈልጋለሁ፣ እኔ ከተመሰረተብኝ ክስ ነፃና ንጹህ ሰው ነኝ፡፡” ሲል በተደጋጋሚ ተደምጧል፡፡

# ቶማስ ቦኒ . . .

ከ 1 የዞረ

በወቅቱ ስለ ህንፃው አስመልክቶ የኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ ይህ ህንፃ ያረፈበት ቦታ ከዚህ በፊት አለም በቃኝ እየተባለ የሚጠራ የፌደራሉ ማረሚያ ቤት እንደነበረና ኢትዮጵያም ለአፍሪካ ህብረት መጠናከር ከምታደርገው አስተዋፅዖ አንፃር ቦታውን በነፃ በኢትዮጵያ መንግስትና ህዝብ ስም መበርከቱን ተናግረዋል፡፡ የህብረቱ ኮሚሽን ሊቀመንበር የሆኑት ዶ/ር ጂያን ፒንግ በበኩላቸው ለዚህ መሳካት አስተዋፅኦ ላደረጉት ለቻይና እና ለኢትዮጵያ መንግስት በተለይም ለቻይናው ፕሬዘዳንት ሁ ጂንታኦ እና ለኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊና ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ “ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ” ሲሉ ተደምጠዋል፡፡ ሌላው ንግግር ያደረጉት የህብረቱ የወቅቱ ሊቀመንበር እና የኢኳቶሪያል ጊኒ ፕሬዝዳንት የሆኑት ቴዎዶሮ አቢያንግ ንጉማ ምባሳጐ በህብረቱ ሀገራት፣ በመንግስታቸውና በራሳቸው ስም “ለቻይና መንግስትና ህዝብ እንዲሁም ለአፍሪካዊያን ትስስር ታሪካዊት ሀገር ለሆነችው ኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ምስጋናዬን አቀርባለሁ” ሲሉ ተደምጠዋል፡፡

በእሁዱ ጥር 20 ቀን 2004 ዓ.ም የመሪዎች ጉባዔም ህብረቱን ለቀጣይ አንድ ዓመት እንዲመሩ ኢኮኖሚስቱ የቤኒን ፕሬዘዳንት ቶማስ ቦኒ ያዪ ሊቀመንበር ሆነው ተመርጠዋል፡፡ በዕለቱም የተለየ እና አስገራሚ የሆነው ባለፈው 17ኛው የመሪዎች ጉባኤ ላይ ከተሳተፉት የህብረቱ ሀገራት መካከል የቱኒዚያ ግብፅ እና ሊቢያ መሪዎች በህዝባዊ አመፅ መሪዎቹ ተቀይረው በአዲሶቹ መሪ መወከላቸውና በምርጫ ተሸንፈው “ሥልጣኔ አልለቅም” ያሉት የኮትዲቯር መሪም ከምርጫው በኋላ በኃይል ከሥልጣናቸው ተሰናብተው በአዲስ መሪ በጉባኤው ላይ ተሳትፈው አዲሱ ተወካይም ንግግር አድርገዋል፡፡

የህብረቱ ሐሳብ ጠንሳሽና የአፍሪካ አንድነት እ.ኤ.አ በ1963 ዓ.ም መስራች በሆኑት በቀድሞው የጋና ፕሬዘዳንት ኑአሚን ኑኩሩማ መታሰቢያ ለህብረቱ አባል ሀገራት በሳይንሳዊ ምርምር ከፍተኛ አስተዋፅዖ ላበረከቱ አንድ የሒሳብ ሊቅና ለአንድ አግሮ ባዮሎጂስት ሳይንቲስቶች በጉባኤው ላይ 100 ሺህ የአሜሪካን ዶላር ሽልማት ተበርክቷል፡፡

በጉባኤው የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተጋባዥ እንግዶች በተለይም ሚኒስትሮችና አምባሳደሮች የተገኙ ሲሆን የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ ባን ኪ ሙን ህብረቱ ተጠናክሮ የተረጋጋችና በኢኮኖሚ የበለፀገች አህጉር ለማድረግ መጣር እንዳለበት እና የተባበሩት መንግስታት ድርጅትም አስፈላጊውን ድጋፍና ትብብር እንደሚያደርግ በማስገንዘብ ንግግር አድርገዋል፡፡

ዋና ፀሐፊው ከጉባኤው በኋላ በአዲሱ ህንፃ 650 ሰዎችን በሚይዘው መካከለኛ አዳራሽ ከጋዜጠኞች ጋር ጋዜጣዊ መግለጫ ጉባኤ አድርገዋል፡፡ ባን ኪ ሙን የተረጋጋች አፍሪካን ለመፍጠር አፍሪካዊያን ብርቱ ጥረት ማድረግ እንዳለባቸውና ይህም እውን እንዲሆን ከሀገሮቹ መሪዎች ጋር መነጋገራቸውና የተባበሩት መንግስታትም አስፈላጊውን ሁሉ በተለይም ህብረቱ እንዲጠናከር ድጋፍ እንደሚያደርግ ጠቁመዋል፡፡ በመግለጫውም ከተለያዩ ዓለም አቀፍ ጋዜጠኞች በርካታ ጥያቄዎች ተነስተው ዋና ፀሐፊው ሙን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከተነሱ ጥያቄዎች መካከልም የአፍሪካ ህብረት ላይ የተባበሩት መንግስታት ተፅዕኖ እየፈጠረ አይደለም ወይ? የህብረቱ አባል ሀገራትስ እንዴት በነፃነት መንቀሳቀስና በአህጉሪቱ ጉዳይ ላይ መወሰን ይችላሉ? የሚሉ ይገኙበታል፡፡

ባን ኪ ሙን በበኩላቸው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ከአፍሪካ ህብረት ጋር የሚሰራው በትብብር እንደሆነና የራሱ ነፃነት ያለው መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ነገር ግን የህብረቱ አባል ሀገራት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አባል በመሆናቸው ቀጥታ ግንኙነት ያላቸው ሲሆን የሚያደርጉትም ተሳትፎ እና የሚያበረክቱት አስተዋፅዖ እንደማንኛውም አባል ነው እንጂ ከአፍሪካ ህብረት ጋር የሚያያይዘው ነገር እንደሌለ ጠቁመዋል፡፡ ለፀሐፊው በተለይ ከፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ በተነሳው ጥያቄ፤ በያዝነው በፈረንጆች 2012 ዓ.ም በአፍሪካ በተለይም በሰሜንና ምስራቅ አፍሪካ ስላለው የፖለቲካ ኢኮኖሚ መረጋጋት ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት ምን እንጠብቅ? ለሚለው ባን ኪ ሙን “የአህጉሪቱም ሆኑ የቀጠናዎቹ ሀገሮች መሪዎች በሀገራቸው የፖለቲካ ኢኮኖሚ መረጋጋት እንዲፈጠር ቀጣይነት ያለው ልማት ማረጋገጥ፣ የዋጋ ግሽበት መናርን መቆጣጠር፣ የአካባቢ ጥበቃና የተፈጥሮ አየር መዛባትን መከላከልና አሳታፊ የሆነ ዴሞክራሲን መተግበርና ማጐልበት እንዲሁም የሰብዓዊ መብት አያያዝ ላይ ትኩረት ማድረግ እንዳለባቸው ተነጋግረናል፡፡ ይህም እንዲሳካ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ከላይ የተጠቀሱትን ማበረታታትና መደገፍ ሲሆን መሪዎቹም እንደሚተገብሩ በተነጋገርንበት ወቅት የጋራ መግባባት ላይ ደርሰናል፡፡” ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በጉባኤው የተገኙት አዲሱ የቱኒዚያ ፕሬዝዳንትን ጨምሮ የተለያዩ የህብረቱ ኮሚሽን ህጋዊ ምክር ቤት ዳይሬክተር የአፍሪካ ፍ/ቤት እና ሰብዓዊ መብት ፕሬዘዳንት ስለ ወቅታዊ ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥተዋል፡፡ በተጨማሪም የህብረቱ የተለያዩ መሪዎች በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥተዋል፡፡

የህብረቱ 18ኛው መደበኛ ጉባኤ ተሳታፊ መሪዎችም የአህጉሪቱን ቀጣይነት ያለው ልማት ማረጋገጥ፣ በሀገሮቹ መካከል ያለውን የንግድ ትስስር ማጠናከር እና የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲረጋገጡ እና ተግባራዊ እንዲሆኑ መሥራት እንደሚገባቸው መተማመን ላይ መድረሳቸውን ጠቁመዋል፡፡ የተለያዩ ስብሰባዎችም በዝግ የተካሄዱ ሲሆን ጉባኤውም በተሳካ ሁኔታ መጠናቀቁ ተገልፃዕል፡፡

ሌላው ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ዓለም አቀፉ ቀጣይነት ያለው ልማትን ለማረጋገጥ የዓለም ሀገራት መሪዎች ያደረጉት ፓናል ሪፖርት በጃኮብ ዙማ በኩል ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ፀሐፊ ባን ኪ ሙን ጥር 21 ቀን 2004 ዓ.ም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን መሰብሰቢያ አዳራሽ ርክክብ ተደርጓል፡፡ ዋና ፀሐፊውም በሪፖርቱ ዙሪያ ጋዜጣዊ መግለጫ በመስጠት ሪፖርቱን በሚቀጥለው ወር ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባዔ እንደሚያቀርቡ ገልፀዋል፡፡

# የከተማ ቦታ ሊዝ . . .

ከ 1 የዞረ

አዋጅ ጣሪያህን ነቅለህ ሂድ ለማለት የሚያስችል ነው፡፡ አሜሪካኖች ሕዝብ እንዳይደኸይ መንግሥት ይደጉማል፡፡ የኢህአደግ መንግሥት በተገላቢጦሽ ሕዝብን ለማደኸየት አጠንክሮ ይሰራል፡፡ ሕዝብ የመሬት ባለቤት እንዲሆን አንድ ትውልድ ታግሏል፡፡ መስዋዕትነትም ከፍሏል፡፡ የዛሬው መንግሥት ደግሞ ሕዝብን መሬት ለማሳጣት ይሰራል፡፡ ኢህአዴግ መሬት ለኢንቬስተሮች የሚልበት ዘመን ላይ ደርሰናል፡፡ ሥርዓቱ ሕዝብን ማድመጥ አለበት፡፡ ሥርዓቱ ለሕዝብ የቆመ አይደለም፡፡ አቶ በረከት እጃቸው ንጹህ መሆኑን በአደባባይ ለመታጠብ የሞከሩበት መጽሐፍ” ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ በሰጡት መልስ “ሕገ መንግሥቱ በመሬት ላይ ያለው አንቀጽ ሕገ-መንግሥቱ ራሱ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሻሻል አለበት ብለን እናምናለን፡፡ እኛ ሕገ-መንግሥቱን ቀዳደን የመጣል ዓላማ የለንም ለሕዝብ ለውይይት ብቻ ሳይሆን ለሪፈረንደም መቅረብ አለበት፡፡ ዜጎች የመሬት ባለቤትነት መብታቸውን መነጠቅ የለባቸውም፡፡ ኢህአዴግም ጨምሮ ማንም አካል በሽብርተኝነት ቢንቀሳቀስ እናወግዛለን፡፡ የሕዝብን መብት ለማስከበር ለምናደርገው ጥረት ሕዝብ ከጐናችን ሊሆን ይገባል፡፡ የባድሜ ጦርነት በተፈለገው እና ፍትሐዊ በሆነ ሁኔታ ቢጠናቀቅ ኖሮ ዛሬ ይህ ችግር ሊፈጥር አይችልም ነበር፡፡ በአፋር ክልልም በተፈጠረው ድርጊት በጣም እናዝናለን፡፡” ሲሉ ተናግረዋል፡፡

አቶ ገብሩ አስራት በበኩላቸው በሰጡት መልስ አሁን ሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ጦርነቱ በሚገባው መልኩ እንዲጠናቀቅ አልፈለገም፡፡ በዚህ ምክንያት “በአገራችን በተለያየ ጊዜ በርካታ አደጋዎች ይከሰታል፡፡ ሰዎች ታፍነው ይወሰዳሉ፡፡ ይገደላሉ፡፡ አሳዛኝ አደጋዎች ተፈጥሯል፡፡ የሚዲያ ሽፋን እንዳያገኙ ይደረጋል፡፡ ኢህአዴግም ትኩረት አይሰጠውም፡፡ ሰሞኑን በተፈጠረው ሁኔታ ፈረንጆች ስለአሉበት ብቻ ተደጋግሞ ሲነገር እንሰማለን፡፡ በድርጊቱ መፈፀም እናዝናለን፡፡ ሊወገዝም ይገባል፡፡” ብለዋል፡፡

ዶ/ር ሞጋ ፋሪሳ እንዳሉት “መሬትና ነፃነት አይነጣጠሉም፡፡ በጣሊያን ጦርነት ያ ሁሉ ሕይወት የጠፋው ለመሬት ተብሎ ነው፡፡ ዜጐች ከድል በኋላ የመሬት ባለቤት ሆነዋል፡፡ የተሰደደው በአገራችን ሠላምና ዴሞክራሲ ቢሰፍን ወደ አገሩ ይመለሳል፡፡ የሚመለሰው አገር አለኝ፤መሬት አለኝ ብሎ ስለሚያስብ ነው፡፡ ኢህአዴግ ይህንን መብቱን ለመግፈፍ እየሠራ ነው” ሲሉ ተናግረዋል፡፡ የመድረኩን ሙሉ መግለጫ በገጽ 15 ይመልከቱ፡፡

# ያገረሸ ቁስል ያልሻረ ጠባሳ



ከመ/ር ቀለሙ ሁነኛው

ኡኡታ . . . ልቅሶ. . . ዋይታ. . .ሙሾ. . . ደረት መድቃት. . .ኡ!. . .ኡ!. . .ኡ! ውድ ኢትዮጵያውያን ለአንድ አፍታ በውስጣችሁ በመቃተት ኡ!. . . ኡ!. . .ኡ!. . .በሉ:: በፈጠራችሁ አምላክ የሙታኑን የዋይታ ድምፅ እኛ በቁም ያለን እናሰማላቸው::

*የጋምቤላ እንቁ ፈርጥ ትውልደ አኝዋኮች*
*በጅምላ ጭፍጨፋ የግፍ ሞት ቀማሾች*
*ሥጋችሁ አፈር ሆኖ መቃብር ቢወርድም*
*የሞታችሁ ምስጢር ከቶ አይከደንም*
*እናንተን ጨፍጭፈው ዛሬን በቁም ያሉ*
*ነገ በፍርድ ፊት ሞትን ይቀምሳሉ*

ያገረሸ ቁስል ያልሻረ ጠባሳ ዓመታትን ቆጥሮ ዳግመኛ ተውሳ!!

እግዚአብሔር ነፍስ ለዘራባቸው አምሳያ ፍጡራኑን የማስታወስ፣ ድምፃቸውን የመስማት ግድ ይለዋል:: የዘመነ አዲስ ኪዳን ካህን የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣው ሞታችንን በሞቱ ሊሽር እንደሆነ የክርስትና እምነት ተከታዮች የሚስማሙበት እውነት ነው:: የምድራችን አምባገነን ገዢዎች ግን ሲገድሉ፣ ሲጨፈጭፉ ማየት የወቅቱ የአለማችን ዘግናኝ ክስተት እየሆነ መጥቷል:: የዘመነ ወታደራዊ ደርግ አምባገነኖች ወጣቱን ትውልድ በቀይ ሽብር ጨፍጭፈው ኢትዮጵያዊነትን አመከኑ:: ኢሕአፓዎችም በነጭ ሽብር ሰበብ በየመንገዱ ዳር የብዙ ዜጎችን አስከሬን አጋደሙ:: ሁለቱም ግን ጠፉ፤ የአያሌ ዜጎችን ሕይወት ቀጥፈው::

ውድ አንባቢያን እጃቸውን በሰው ክቡር ደም የታጠቡ ነፍሰ ገዳዮች ነፍሳቸው ረፍት የላትም፤ ነፍሳቸው ሰላም የላትም፤ የሰው ደም በሄዱበት ይከተላቸዋል፤ የገዛ ጥላቸው ያሳድዳቸውል፤ ደራርበው ለብሰው ይበርዳቸዋል፤ እየበሉ ይርባቸዋል፤ ተኝተው የሰላም እንቅልፍ ይነሳቸዋል፤ ዝም ባሉበት ያስለፈልፉቸዋል:: የሰው ነፍስ አጥፍቶ ተረጋግቶ መቀመጥ አይቻልምና::

የሕወሓት /ኢህአዴግ መንግሥት የእርሱን ልማታዊነት እንጂ ድክመቱንና እኩይ ምግባሩን በአደባባይ የሚዘግቡትን መገናኛ ብዙሃን ሲኮንናቸውና ሲረግማቸው እያስተዋልን ነው:: አልፎ ተርፎም ከፍተኛ ገንዘብ እየበጀተ ሲያፍናቸው፣ ጋዜጠኞችንም ከአገር ሲያሳድዳቸውና ቀሪዎቹንም እያነቀ ወህኒ ቤት ሲከታቸው እያየን ነው:: የዛሬዎቹ የቤተመንግስት መኳንንት ትናንት በሽፍትነት ዘመናቸው ዛሬ በሚያፍኗቸው (ጃም በሚያደርጓቸው) የምዕራባውያን ሚዲያዎች የደርግን አገዛዝ ኮንነዋል፤ አውግዘዋል:: በህዝብ ዘንድ ተደማጭነትን ለማግኘት ቀስቅሰዋል:: ደርግም በወቅቱ የምዕራባውያኑን ሚዲያዎች ዜናች እንዳይከታተሉ ጥብቅ ህግ አውጥቶ ሲያፍን ነበር:: የዛሬዎቹም መሪዎቻችንም የደርግን ተግባር ደገሙት:: በተለይም የአሜሪካን ድምፅ ሬዲዮ ጣቢያ (VOA) በሁለቱም መንግስታት አያሌ ተግዳሮቶች ገጥመውታል:: ይሁን እንጂ ጣቢያው ስለ አገራችን ገፅታ ሚዛናዊ የሆኑ መረጃዎችን በመስጠት ከኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ ፕሮግራሞች በበለጠ ሕዝብን እያገለገለ ይገኛል::

ቪኦኤ በ09 እና በ11/05/04 ምሽት በጋምቤላ ክልላዊ መንግሥት የተደረገውን የታህሣሥ 24/04/04 የፓርቲውን ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ግምገማና የስብሰባውን ሂደት በተመለከተ ሰፊ ዘገባ ማቅረቡ ይታወሳል:: በግምገማው ወቅት ከተነሱት ጉዳዮች መሀከል በ1996 ዓ.ም በአኝዋክ ሕዝብ ላይ የደረሰውን አስከፊ ጭፍጨፋ የተመለከተ ነበር:: የግምገማውን ሂደት ለመምራት (እንደ ክልሉ ፕሬዝዳንት አባባል ለመታዘብ) ሁለት የፌዴራል መንግስት ተወካዮች በሥፍራው ተገኝተዋል:: የክልሉ ፕሬዝዳንት አቶ ኡመድ ኡቦንግ ተወካዮቹ የስብሰባውን ሂደት ከመታዘብ የዘለለ ስልጣን የላቸውም ቢሉም ሀቁ ግን የዚህ ተቃራኒ ነው:: በስመ ፌዴራሊዝም ርዕዮተ ዓለም (Ideology) የማሳሳቻ ጭምብል አጥልቀው መላ አገሪቱን ረግጠው የሚገዙት አንድ እና አንድ አቶ መለስ ናቸው:: ያለ እሳቸው በጎ አመለካከት አቶ ኡመድ ለረጅም አመታት በስልጣን ላይ መቆየት አይችሉም ነበር:: በአገራችን እውነተኛ የፌዴራሊዝም ሥርዓት የተገነባ ቢሆን ኖሮ በ1996 ዓ.ም በግፍ የተጨፈጨፉትን 400 አኝዋኮች ያስገደሉት የፌዴራል መንግሥት መሪዎች መሆናቸውን አቶ ኡመድ በአደባባይ ባልመሰከሩ ነበር:: "እኔ የሰዎችን ስም ዝርዝር እንዳስተላልፍ በተሰጠኝ ትዕዛዝ መሠረት አስተላለፍኩኝ እንጂ ግድያውን በበላይነት ያስፈፀሙት ጠቅላይ ሚ/ሩ ናቸው::" ሲሉ በግልፅ ተናግረዋል:: እንደ ቪኦኤ ዘገባም በወቅቱ በስብሰባው ላይ ስለ ብሄርሰቡ አባላት ግድያ ለተነሳው ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ እድሜ ለቴክኖሎጂ በድምፅና በበራሪ ወረቀቶች ተባዝቶ ጋምቤላ ከተማ ውስጥ መበተኑ የህዝቡ ቁስል እንዲያገረሽ አድርጓል::

ሕወሓት /ኢህአዴግ የሥልጣን መንበሩን ከተቆናጠጠ በኋላ ስለ ቀይ ሽብር ሰለባዎች ያልቀሰቀሰበት ወቅት አልነበረም:: በጅምላ ተጨፍጭፈው በየጥሻው የተቀበሩ የብዙ ሺህ ወጣቶችን አፅም ከያለበት እየሰበሰበ የደርግን አገዛዝ አስከፊ ገፅታ ለማሳየት ተጠቅሞበታል::

የወጣቶች አፅም ከወደቀበት ተሰብስቦ እንደየ ባህሉና እምነቱ አፈር መልበሱ በበጐ ህሊና ሲታይ የሚያስመሰግን ተግባር ነው:: ክፋቱ ግን ከሀያ ዓመታት በፊት የተረሳን ሀዘን እየቀሰቀሱ ሙሾ ማስደርደሩና ለተራ የፖለቲካ ትሩፋት ማዋሉ ላይ ነው:: በቀይ ሽብር የተከሰሱ የደርግ ባለሥልጣናት ከየመንደሩ እየተለቀሙ ለፍርድ የመቅረባቸው ተገቢነት አያጠያይቅም:: መልካም ነው እንቀበለዋልን ወንጀለኞች በየትኛውም ጊዜ ለፍርድ መቅረብ ይገባቸዋል:: ያንን አስከፊ የጅምላ ጭፍጨፋ ሲኮንንና የደረቁ አጥንቶችን እያሳየ ሲያስለቅስ የነበረው ነፃ አውጭው መንግሥታችን እሱም በተራው የ400 አኝዋኮችን ሕይወት በግፍ መቅጠፉ ግን መቸም ቢሆን የሚረሳ አይደለም:: ባለመረሳቱም ጊዜውን ጠብቆ በራሱ ምክንያት ቁስሉ ነፈረቀ:: ያሁኖቹ አጥፊዎችም አንድ ቀን ደግሞ አጥፊዎች ከሕግ ፊት ሲቀርቡ እናይ ይሆናል::

**የወጣቶች አፅም ከወደቀበት ተሰብስቦ**
**እንደየ ባህሉና እምነቱ**
**አፈር መልበሱ በበጐ ህሊና ሲታይ የሚያስመሰግን ተግባር ነው፡፡**
**ክፋቱ ግን ከሀያ ዓመታት በፊት የተረሳን ሀዘን እየቀሰቀሱ ሙሾ ማስደርደሩና ለተራ የፖለቲካ ትሩፋት ማዋሉ ላይ ነው፡፡ በቀይ ሽብር የተከሰሱ የደርግ ባለሥልጣናት ከየመንደሩ እየተለቀሙ ለፍርድ የመቅረባቸው ተገቢነት አያጠያይቅም፡፡ መልካም ነው እንቀበለዋልን ወንጀለኞች በየትኛውም ጊዜ ለፍርድ መቅረብ ይገባቸዋል፡፡ ያንን አስከፊ የጅምላ ጭፍጨፋ ሲኮንንና የደረቁ አጥንቶችን**
**እያሳየ ሲያስለቅስ የነበረው ነፃ አውጭው መንግሥታችን እሱም በተራው የ400**
**አኝዋኮችን ሕይወት በግፍ መቅጠፉ ግን መቸም ቢሆን የሚረሳ አይደለም፡፡**
**ባለመረሳቱም ጊዜውን ጠብቆ በራሱ ምክንያት ቁስሉ ነፈረቀ፡፡**
**ያሁኖቹ አጥፊዎችም አንድ ቀን ደግሞ አጥፊዎች**
**ከሕግ ፊት ሲቀርቡ እናይ ይሆናል፡፡**

## ጥያቄ ለክቡር ጠቅላይ ሚ/ር መለስ ዜናዊ

ለመሆኑ እነኚህን 400 የአኝዋክ ሕዝብ ተወላጆች ማን አስጨፈጨፋቸው? ማንስ ገደላቸው?

እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ይህንን ልጠይቅዎት ግድ ይለኛል:: ይህ ጥያቄ የእኔ ወይም የጋምቤላ ህዝብ አሊያም የኢትዮጵያውያን ብቻ አይደለም፤ የመላው አለምም ጭምር ነው::

ክቡር ጠቅላይ ሚ/ር በ1997 ዓ.ም ምርጫ ቅንጅት የተሰኘ ከፉ ተቀናቃኝ በተነሳብዎት ጊዜ እርስዎና ፓርቲዎ የቅንጅት መሪዎች "ኢንተር ሀሞይ" በሚል ሲወነጅሉ አልነበረምን? ከሁከቱስ በኋላ የእርሰዎ ሠራዊት (የአግአዚ ጦር) በአዲስ አበባ አስፋልት ላይ የረፈረፏቸውን ዜጎች በቅንጅት አማካኝተው "በዘር ማጥፋት ወንጀል" ሲከሰሱ አልነበረምን? ሌሎችን ወንጀለኞች አድርገው ይሰሷቸዋል:: ራስዎትን ግን ፍፁም ንፁህ ዜጋ አድርገው እንደ ጲላጦስ እጇዎትን ሲታጠቡ ሕሊናዎትን አይቆጠቁዎትም?

አሁን ደግሞ አሸባሪ በሚል ጭንብል እርስዎ እንደፈለጉ በሚዘውሩት ፓርላማ ህግ አፅድቀው ከብዕርና ከወረቀት ያለፈ ነገር የሌላቸውን ወጣት ጋዜጠኞችንና የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮችን እስከ 18 ዓመት ለማሰር ከጫፍ ደርሰዋል:: "መንግስቴ የህዝብን ሠላም የመጠበቅ ሀላፊነት አለበት" በሚል ሰበብ አስባብ ንፁህን ዜጎችን እንደሻዎት ሲያስሩና ሂደቱን ዴሞክራሲያዊ ለማስመሰል የሚዲያ ሽፋን እንዲሰጠው እያደረጉ የ400 አኝዋኮችን ሞት ምነው ደበቁን?

አቶ መለስ ሚስጥሩ ተዳፍኖ ይቀራል ብለው አስበው ከሆነ ተሳስተዋል:: ያለነው በረቀቀ የቴክኖሎጂ ዘመን ውስጥ መሆኑን ከእርስዎ በላይ የሚያውቅ ላሳር ነው:: የመንግስትዎን ስህተት ነቅሰው በማውጣት የሚነቅፉትን ሂዩማንራይትስዎች፣ አመንስቲ ኢንተርናሽናል፣ ሲፒጄ፣ ቪኦኤ፣ የጀርመን ድምፅ ሬዲዮ፣ ኢሳት ቴሌቪዥን፣ አልጀዚራ፣ ቢቢሲ (አንዳንዴ የመንግሥትዎን ልማታዊነት ሲያወራ ግን በኢቲቪ የሚወደስ) ወዘተ የኢትዮጵያን እድገት የማይሹ እንቅፋቶች ተደርገው ይቆጠራሉ:: ስለ ጋምቤላ የመሬት ቅርምት ያወሩት ቪኦኤ የጀርመን ሬዲዮና ድርጊቱን ያወገዘው ሂዩማን ራይትስዎች በኢቲቪ ዶክመንተሪ ፊልሞች ሲወገዙ እያየን ነው:: እኛ ደግሞ ከመንግሥታችን ሚዲያዎች ይልቅ የምዕራባውያኑ ሚዲያዎችና አለም አቀፍ ሰብአዊ ድርጅቶች ትክክል ናቸው እያልን ነው:: ለምን ቢሉ መንግትዎ ለአፍታ እንኳን ስህተቱን ስለማያምን፤ በተለይም እርስዎ::

ክቡር ጠቅላይ ሚ/ር እነዚህ እትብታቸው በተቀበረበት የጋምቤላ ምድር በግፍ የተጨፈጨፉትን የአኝዋክ ህዝብ ተወላጆችን በተመለከተ የዘር ማጥፋት ወንጀል (ጄኖሳይድ) በሚል ጉዳዩ ወደ አለም አቀፍ ፍርድ ቤት (ዘሄግ) እንዲሄድና እንዲጣራ ለማድረግ በውጭ የሚገኙ የጋምቤላ ተወላጆችና አንዳንድ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በወቅቱ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ እንደነበር ይኸው መከረኛ ቪኦኤ ሲዘግብ አድምጠናል:: እርስዎም ሆኑ የመንግስትዎ ጎምቱ ባለስልጣናት የድርጊቱ ተዋንያን ካልሆናችሁ እነዚህን ንፁሀን ማን እና ለምን እንደገደላቸው በግልፅ ለህዝብዎ ለማሳወቅ ለምን ተሳንዎት? የእርስዎ ወገኖች ህዝብን በግፍ ሲገድሉ ድርጊቱ በሽብርተኝነት አያስፈርጃቸውም? ጋዜጠኞችና የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ቀለማቸውን በወረቀት ላይ አንጥበው ስለፍትህ ሲሟገቱ ግን ሁኔታው አሸባሪ ያሰኛቸዋል:: እንዴት ነው ነገሩ? ሕሊናዎትን አይቆጠቁጠዎት ይሆን?

ክቡር ጠቅላይ ሚ/ር ሰዎቹ እንዲገደሉ ትዕዛዝ የሰጡትን ባለስልጣናትና ተኩሰው የገደሏቸውን ጨካኞች ህግ ፊት አስቀርበው ተገቢውን ፍርድ እንዲያገኙ በማድረግ የሟች ቤተሰቦችን ሀዘኑን ለማቅለል መሞከር የእርስዎ ሀላፊነት ይመስለኛል:: በቀይ ሽብር የተጨፈጨፉ ዜጎችን አፅም እየሰበሰቡ እንዳላስለቀሱና ቀይ ሽብርን ያፋፋሙ ባለስልጣናትን እያደኑ ለፍርድ እንዳላቀረቡ ሁሉ በእርስዎ ንግሥና ዘመን ለተጨፈጨፉት የአኝዋክ ተወላጆች ጆሮ ዳባ ያሉት ለምንድ ነው?

ስለ ጉዳዩ የቪኦኤ ጋዜጠኞች ያናገሯቸው የጋምቤላ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኡመድ ኡቦንግ እንደሌሎች ወንጀሎች ማዕከላዊ ገብተው ተዘቅዝቀው ሳይገረፉ እንደወተወቱ እርስዎም ያውቁታል:: ቁም ነገሩ እዚህ ላይ ነው:: ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ዘወትር የሚቀስሯትን ጣትዎን ከጋዜጠኞች በተለይም ከቪኦኤና ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ፊት ላይ ያንሱና እርስዎ ከሾሟቸው የጋምቤላ መስተዳድር ካቢኔዎች ጋር ይፋጠጡ:: እነ አቶ ኡመድ ባይወተውቱ ቪኦኤም አይዘግብም፤ እኛም አንሰማም ነበር:: ይሄ በማንም ሰው ወይም ድርጅት የሚመጣና የ "ብላኔ" ዶክመንተሪ ፊልም ሊሰራበት የሚችል ጉዳይ አይደለም::

እንደ "አኬልዳማ፣ የመሬት ወረራ ወይስ ልማት፣ የሽብር አባት . . ." እንደ መሳሰሉት ውሃ የማያነሱ የኢቲቪ ፊልሞችን አይነት አይደለም:: በግፍ በተጨፈጨፉት ወገኖቻችን ዙሪያ ማየትም ሆነ ማድመጥ የምንፈልገው ሀቅን፤ ሕሊናን የሚያሸር፤ የውስጥ ስሜትን የሚፈውስን እውነትን ነው:: ማታለል፣ መሸወድ፤ ማስመሰል ከእንዲህ ይበቃል::

የቀይ ሽብር ሰለባዎችን አፅም አሳይተው እንዳስለቀሱን ሁሉ የአኝዋኮችንም የጭፍጨፋ ሂደት የሚያሳየውንም ፊልም መመልከትና ደም ማንባት እንሻለን፤ የዚያን ጊዜ ነው ሀዘናችን የሚቀለው:: ድርጊቱ ምንም እንኳን ዘግናኝና ከአኬልዳማ ፊልም በእጅጉ አሰቃቂ ቢሆንም እንደተራመደው ከ13 ዓመት ዕድሜ በታች የሚለው ተሻሽሎ ከ18 ዓመት በላይ ዕድሜ ያላቸው እንዲመለከቱት በማስታወቂያው ይነገርልን::

የተከበሩ ጠቅላይ ሚ/ር ከቅርብ አመታት በፊት በሩዋንዳ የተከሰተውን የዘር ማጥፋት ወንጀል አለም በአሰቃቂነቱ በመጀመሪያው ረድፍ ላይ ያስቀመጠው ድርጊት ነው:: ለአፍሪካውያንም አሳፋሪ የታሪክ ጠባሳን ጥሎ አልፏል:: በተራ የዘረኝነት ስሜት ከ800 ሺህ በላይ ሩዋንዳውያን በመጨፍጨፋቸው የፍርዱ ሂደት ዛሬም አልተገታም:: የዜጎችም ቁስል እንዲሁ አልሻረም:: የቁጥር ልዩነት እንጅ የኛዎቹም አኝዋኮች በግፍ መጨፍጨፍ ከሩዋንዳው አይተናነስም:: እርስዎም እንደሚያውቁት በአለም አቀፍ ህግ መሠረት ከአንድ ብሔረሰብ፣ ጐሣ ቤተሰብ ከ10 በላይ ነፍስ ማጥፋት ወንጀሉ የዘር ማጥፋት ነውና በዚህ ጉዳይ እውነቱን ማወቅ ይኖርብናል፤ እንደ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ከተቆጠርን:: ዜናው መረጃ ቢስና ምዕራባውያን በእርስዎና በመነግስትዎ ላይ ከጥላቻ በመነጨ የሚያናፍሱት ከሆነም ይህንን በሚገባ ያስረዱንና እኛም ከእርስዎ ጎን ቆመን የአገራችንን መልካም ገፅታ የሚያደፈርሱትን አብረን እናውግዛቸው::

## ይድረስ ለተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች

ቁጥራችሁ እንደ አሸን ቢፈላም ከተሰለፋችሁበት አላማና ከምታራምዱት ርዕዮት ዓለም (Ideology)ልዩነት አንፃር ሳይሆን እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊና እንደ በሳል የፖለቲካ ሰው ለጉዳዩ ትኩረት ልትሰጡት ይገባል:: እናንተም እንደ ኢህአዴግ ለተራ የፖለቲካ ትርፍ ወይም ገዥውን ፓርቲ ከህዝብ ጋር በማቃረን ከስልጣን ለማውረድ ኃጢአቱን ማብዛት በሚል ሽፋን ሳይሆን ፍፁም ሰብአዊነትን (Humanity) በተላበሰ መልኩ የወንጀሉ ተዋናዮች ለፍርድ እንዲቀርቡ ከኢህአዴግ ጋር ተቀራርባችሁ መሥራት ይጠበቅባችኋል:: ድርጊቱ ከተፈፀመ 8 ዓመታትን ቢያስቆጥርም ወንጀሉ ዘርን ማጥፋት ነውና ጊዜ አይገድለውም:: ከታሪክም እንደምንማረው የናዚ የጦር ወንጀለኞች እንኳን በህይወት ሊኖሩ ይችላሉ በሚል ዛሬም ሲታደኑ እንሰማለን::

እናም በኢትዮጵያውያን ላይ በየጊዜው በሰበብ አስባቡ የሚፈፀሙ ጭፍጨፋዎች ኢ-ሰብአዊ ድርጊቶች እንዲቆሙ መጣርና የመታገያ ዋና አርማችሁ ልታደርጉት ይገባችኋል:: ይችን ሀገር የፍትሕ አገር ማድረግ ካልቻላችሁ ነገም እናንተ ቀንቷችሁ ሥልጣን ብትጨብጡ ያው ጨፍጫፊዎች ነው የምትሆኑት፤ ደርግ ወድቆ ኢህአዴግ ቢተካም በቀይ ሽብር ጥቁር ሽብር ተተካ እንጂ ምን አተረፍን? ዛሬ ምሳ ተበልቶ ራት የማይደገምበት አገር ውስጥ ሆነን በሰላም ውጥተን በሰላም መግባት እንኳን አልቻልንም:: ባፋኞች እንዳንታፈን እንሰጋለን:: ኧረ መላ በሉ፤ ኧረ አንድነት ፍጡሩ፤ ኧረ ተመካከሩ፤ ሕዝቡ በሕሊናውም በኑሮውም እየነኮተ ነው:: ፈጣሪ አምላክ የንፁሐንን ደም ይበቀል!!

ኢኮኖሚ

# "መናገር በሚገባችሁ ጊዜ ዝም አላችሁ"
# "ዝም ማለት ሲገባችሁ ትናገራላችሁ፡፡"



ኢ/ር ዘለቀ ረዲ
mesayewa2011@gmail.com

ውድ አንባቢያን ለዛሬው ጽሁፌ መነሻ ያደረግሁት ኢትዮጵያ ሀገራችን በጣሊያን ጦር በግፍ በተወረረች ጊዜ የወቅቱ የካቶሊክ ጳጳሳት ጦሩንና የጦር መሣሪያውን ባርከው ቀድሰው ቅዱስ ጦርነት ብለው ከመላካቸው በተጨማሪ ጳጳሳቱና ቀሳውስቱ ለዚህ እነሱ የተቀደሰ ጦርነት ለሚሉት እና ኢትዮጵያን በግፍ ለተወረረችበት ጦርነት የወርቅና የብር መስቀላቸውን ሳይቀር እንዳዋጡ ያየ አንድ ሲዊድናዊ ፕሮቲስታንት ጋዜጠኛ የወቅቱን ፓፓ ወቅሶ የጻፈውን ደብዳቤ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ በአባ ጎርጎርዮስ ከተዘጋጀው መጽሐፍ ገፅ 89-91 ያለውን ብንመለከት፡- "ከብዙዎቹም መካከል ኤሊክ ሲንድሩም የሚባሉት የስዊድን ጋዜጠኛ ፓፓውን እንዴት እንደወቀሷቸው (ሲሞን ረስቲን የተረጎመውን) ከዚህ ቀጠለን እናቀርባለን፡፡"

"ቅዱስ ሆይ እኔ በሰሜን አገር የተወለድሁ አንድ ፕሮቴስታንት ነኝ፡፡ ባገራችንም በስዊድን በግንባራችን የምንደፋው፣በእልፍኛችን ሁነን ከእግዚአብሔር ከአምላካችን ጋር ስንናገር ነው እንጂ ከሰው ጋራ ብንናገር ቁመን እንነጋገራለንና በእግርዎ ላይ ወድቄ ጫማዎን ስለማልስምዎ አይቆጡብኝ፡፡ ቅዱስ ሆይ እኔ አንድ ምስኪን ኃጢአተኛ እርስዎ ግን የመድኃኒታችን ምትክ ነዎት የማይሳሳቱም ነዎት፡፡ ይሁን እንጂ እኔ እነቅፍዎታለሁ፡፡ እርስዎ የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ዋና ነዎት፡፡ ካቶሊካዊት ማለትም የሁሉ ማለት ነው፡፡ ዛሬ እንግዲህ የርስዎ ቤተ ክርስቲያን በውነት የሁሉ ቤተ ክርስቲያን ናት? እርስዎ ከሙሶሎኒ ጋር ሁነው ከሌላው ዓለም ጋር በጠብ አሉ፡፡ እርስዎና ከርስዎ በታች ያሉት ሌሎችም ጳጳሳት ኢትዮጵያ ለኢጣሊያ ቅኝ አገር እንድትሆን የሚገባ ነው ብለው ተናገሩ፡፡ ርስዎ መቼም የሐዋርያው የጴጥሮስ ተከታይ ነዎትና አይሳሳቱም፡፡ እንግዲህ ሌላው ዓለም ሁሉ ቃልዎን ሳይሰማ በኢጣሊያ ላይ "ሳንክሲዮ" ቢያደርግ መሳሳቱ ነው? ቅዱስ ሆይ፣ኢጣሊያ የፍርድ ሥራ ትሠራለች ብለው ሰብከዋል፡፡ የመሲና፣የቢረንዲቤም ጳጳሳት ወርቃቸውን ሁሉ ለጦርነቱ ከሳራ እንማደሰጡ ሰማን፡፡ እናንተ ጳጳሳት ይህንን ስታደርጉ እግዚአብሔር ከኢጣሊያ ጋር ነው የማለት ያህል ይመስለኛል፡፡ እንግዲህ ሌላው ዓለም ሁሉ የኢጣሊያን ሥራ ቢቃወም የእግዚአብሔርን ፍርድ ይቃወም ይሆን? ኢትዮጵያውያንስ አገራቸውን ሲጠብቁ በእግዚአብሔር ላይ ተነሥተው ይኸንን ርስዎ እንዳሉ ኢጣሊያ የጽድቅ ውጊያ የምትዋጋ ከሆነ ሌላውም ዓለም የህንን የጽድቅ ጦርነት ቢቃወም መቼም ከናንተ በቀር ሌላው ዓለም ሁሉ እግዚአብሔርን የካደ ይመስላል፡፡ እንግዲህ ርስዎ እንደሚሉት እግዚአብሔር አምላካችን የኢጣሊያ መንግሥት ቃሉን ሊያፈርስ መሐላውንም ሊሰብር ፈቅዷል፡፡ ርስዎ እንደሚሉት የኢትዮጵያ ሰዎች አገራቸውን ለመጠበቅ ቢሰበሰቡ፤የኢጣሊያ አይሮፕላን ጥርግ አድርጐ ቢያጠፋቸው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሥራ ነው? ሴቶችንና ሕፃናትን በቦምብ ሲያጠፉ እግዚአብሔርን እያገለገልኩ ነው ይላሉ? ይህንን ሁሉ ካሁን በፊት በመጽሐፍ ቅዱስ አላገኘንም ነበርና ርስዎ አሁን ስላስተማሩን ትልቅ ነገር ነው፡፡ ይህንን ሁሉ የምታስተምረን ቅስድቲቱ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ በዱሮ ዘመን ግን ቤተ ክርስቲያን ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር መታዘዝ ይገባል ብላ ታስተምር ነበር፡፡ ቅዱስ ሆይ፤የርስዎ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት አይደለችም፤የሁሉም አይደለችም፤እግዚአብሔር መሐላን ማፍረስ ይወዳል ብለው ቢያስተምሩን ውሸትዎ ነው ብለን እንመልስልዎታለን፡፡ ርስዎም የዓለም ሁሉ አባት ነኝ ሲሉ ሳሉ የሙሶሎኒ ባሪያ ሁነዋል፡፡ በኢጣሊያ ላይ ሥጋዊ "ሳንክሲዮ" ማድረግ የግድ ነው፡፡ ርስዎ የሚያመልኩት አምላክ ጣዖት ነው እንግዳ አምላክ አይደለም፡፡ ኢትዮጵያ/ ርስዎ ለሚያመልኩት አምላክ ጸሎት ልታሳርግ አትችልም፡፡ ሌላው ዓለም እንደዚሁ ወደ ርስዎ አምላክ ሊጸልይ አይችልም፡፡ ርስዎ ከእግዚአብሔር ይልቅ ለሰውዬው ለሙሶሎኒ የሚታዘዙ ሁነዋልና፡፡ ርስዎ መናገር በተገባዎ ጊዜ ዝም አሉ፤ዝም ማለትም በተገባዎ ጊዜ ተናገሩ፡፡ አሁንም ከሌሎች ጳጳሳት ጋር የሙሶሎኒን ጫማ ስመዋል፡፡ የዓለምን ሠላም የሚያውከውን ወንበዴውን ቢያወግዙት ኖሮ ለቤተ ክርስቲያንዎ እንዴት ያለ ጥቅም በሆነ ነበር፡፡ ምናልባትም ርስዎም በታሠሩ ነበር፡፡ ምናልባትም እንደ ዱሮ ዘመን ክርስቲያኖች ወደ ሰማዕትነት ሞት በደረሱ ነበር፡፡ ዓለምም ሁሉ ከርስዎ ጋር በሆነ ነበር፡፡ ክርስቲያን ቢሆን አረመኔም ቢሆን ሰው ሁሉ ርስዎ የእግዚአብሔር አገልጋይ እንደሆኑ በተረዳ ነበር፡፡

አሁንም በቅርብ የገና በዓል ነው፡፡ ለግፍ ጦርነት ወርቃቸውን የሰጡ ጳጳሳትም እንግዲህ ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን በምድር ላይ ሰላም ይሁን ለሰውም በጐ ፈቃድ ይሁን ብለው ሊዘምሩ ናቸው፡፡ ይኸንንም ሲዘምሩ በደረታቸው የወርቅ መስቀል ሳያደርጉ አይቀርም፤ነገር ግን በጀርባቸው ላይ የእንጨት መስቀል ቢሸከሙ ይሻል ነበር፡፡ ቅዱስ ሆይ፤ በዓሉን ያሳምርልዎ ብዬ ምኞቴን እገልጻለሁ፡፡" የህ የጭካኔ ድርጊት በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል እንደ ትልቅ ገደል ሆኖ ይኖራል፡፡

አሁን ባለንበት የሀገራችንን ሁኔታ ብንመለከት በእጅጉ የሚያሳዝን እና ሕብረተሰብም ግራ ተጋብቶ ያለበት ሰዓት ነው፡፡ ሕዝባችን አንዱን አምባገነን ከብዙ ጊዜ ሽክም በኋላ እንደምንም ሲወርድ ሌላው አምባገነንም ተንደርድሮ በጫንቃው ላይ ይቀመጥበታል፡፡ ይህንንም እንደምንም ሲያስወግድ ሌላው አምባገነን ተሽቀዳድሞ እሽኮኮ ትከሻው ላይ ይወጣበታል፡፡ በዚህም የአምባገነኖች ቀንበር በመሸከም ከአፄ ኃ/ሥላሴ የአርባ ዓመት አገዛዝ ወደ ደርግ 17 ዓመት ከደርግ ወደ ኢህአዴግ መጨረሻ የሌለው አገዛዝ ከመሸጋገር የዘለለ አንዳችም ጥቅም አላገኘም፡፡ ከአብራክ የወጡት ልጆቹ በየጊዜው የመንግሥቱ ሎሌዎች ከመሆን የዘለለ አንዳችም የሕዝብን መብት ከማስጠበቅ አኳያ የፈፀሙት አንዳችም ነገር የለም፡፡ በዚህም እንዳለመታደል ሆኖ በእያንዳንዱ ስርዓቱ ካድሬዎች ወይንም ሥራ አስፈፃሚዎች የሥርዓቱ አጐብዳጆች ብቻ ስለሆኑ ሥርዓቱ ሲወድቅ ከወደቀው ስርዓት ጋር አብረው በሰሩት ጥፋት ይወቀሳሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች የወቅቱ የሃገሪቱ ገዢው ክፍል ሕዝብን ሲበድል ዝም ይላሉ፡፡ የገዠው ፓርቲ የሚያደርገው ሁሉ ትክክልም ይሁን አይሁን ከእውነተኛ ፍርድ አኳያ ሳይሆን ከአሉታዊ ጥቅም አኳያ ስለሚያዩት ሕዝብ ሲበደል ፍርድ ሲጓደል አይተው እንዳላዩ ይሆናሉ፡፡ ሥርዓቱ ሲወድቅ ግን አብረው እንደሚወድቁ ከእነርሱ በፊት በእነርሱ መንገድ ይሄዱ ከነበሩት ከወደቁት መማር አይችሉም፡፡ ከማያልፈው ሕዝብና ሀገር ጋር ከመሆን ይልቅ በሚያልፍ ጥቅምና በወቅቱ መንግሥት ስለሚመኩ የተመኩበት ሲንገዳገድ እነርሱ ቀድመው ይወድቃሉ፡፡

በአፄ ኃ/ሥላሴም ይሁን በደርግ የገዢው ፓርቲ ሕዝብን ሲበድል የወቅቱ የሥርዓቱ ካድሬዎች ልክ አይደለህም አላሉም፡፡ በዚህም የሞቱት በታሪክ ተወቃሽ ሲሆኑ ያሉት በሞትና በእስራት እንደተቀጡ ይታወቃል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከራሱ ይልቅ ቤተሰቡ ራሱን አሳልፎ ይሰጣል፡፡ በርካታ ልጆች ወደ አረብና ሌሎች አፍሪካ ሀገራት ሲሔዱ በየመንገድ የአንበሳ የጅብና የነብር እራት የሚሆኑት እነሱ ከችግር ለማምለጥ ሳይሆን ቤተሰቦቻቸውን ለመርዳት ነው፡፡ የተረፉትም ካሰቡት ቦታ ደርሰው ሲቀጠሩ በቀጣሪዎቻቸው የሚደርስባቸውን እንግልት መረገጥና መደፈር ችለው እየሰሩ እነርሱ ልብስና ጫማ ሳይቀይሩ ተቸግረው ላሳደጓቸው ቤተሰቦቻቸው ያገኟትን ይልካሉ፡፡ በሌላ በኩል እዚሁ ሀገራችን ውስጥ በርካታ ሰዎች የመንግሥትም ይሁን የግል ሥራ ተቀጥረው እድሜያቸው ከአቅመ አዳምና ሔዋን ቢያልፍም ከቤተሰቦቻቸው ጋር ይኖራሉ፡፡ ያገኟትን አብረው ከቤተሰቦቻቸው ጋር እየተቃመሱ እናት አባቶቻቸውን እህት ወንድሞቻቸውን እየረዱ እንደሚቀመጡ ይታወቃል፡፡ ማንኛውን ኢትዮጲያዊ ከራሱ በፊት ቤተሰቡን ያስቀድማል፡፡ ቤተሰቡም ቢሆን እንግዲህ 18 ዓመት ሞልቶሃል ራስህን ቻል አይለውም፡፡ ይህ የሚያሳየው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለቤተሰቡ ያለው ፍቅር በምንም ሊለካ አለመቻሉን ነው፡፡

እናንተ የሕዝብና የመንግሥት ተወካይ ሆናችሁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከራሱ የልቅ ለቤተሰቡ እንደሚኖር እያወቃችሁ ሕዝብ ተቸግሮና ተለክቶ ለቤተሰቡ ያቆየው ቦታ ላይ እንዲህ ዓይነት አዋጅ ሲወጣ ዝም አላችሁ፡፡ ቤት ንብረት ሟቹ ለወራሽ ሲቸግረው ሽጦ ለውጦ ሊጠቀምበት የሚችለውን ሟች ለቋሚ ያዘጋጀው /ያቆየው/ ንብረት ነው፡፡ የመሸጥ የመለወጥና መብቱ ሊጠቀመበት ይገባ ነበር፡፡ ይህንን ፈፅሞ እንኳን ለአድማጩ ለእናንተ ለራሳችሁ የማይዋጥ ነገር ዋጥ ተቀበል ትሉታላችሁ፡፡ ይህ ጊዜ የእናንተ ዝም የማለት ጊዜና በቦታው ሁናችሁ መንግሥት ይህንን አይነት አፋኝ አዋጅ ሲያወጣ ያልተከራከራችሁበትን ጊዜና ሁኔታ ሲያስታውሳችሁ እየተፀፀታችሁ ዝም ልትሉ የሚገባችሁ ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ሕዝቡን በማይሆን ነገር በውሸት ለማሳመን መሞከር በእጅጉ እናንተን አሳድጐ አስተምሮ ለዚህ ያደረሰውን ቤተሰብ እንደድውያን መቁጠር ነው፡፡ አሁንም ገና አልመሸም በተስፋ መንግሥት ይህንን ጉዳይ ቆም ብሎ ያስብበት ዘንድ ተገቢ ነው ባይ ነኝ፡፡

እናንተ የሕዝብ ተወካይ መሆናችሁን ብታውቁ ኖሮ በእርግጥ የወከላችሁን ሕዝብ ፍላጐት ለማሟላት ደፋ ቀና ማለት ይገባ ነበር፡፡ ይህ አንድ የተወከለ ሰው ለወከለው ሰው የወከለውን ሰው በሚፈለገው መልኩ መሥራት ካልቻለ ወካይ ውክልናውን በፈለገው ሰዓት ማንሳት እንደሚችል ያለመገንዘብ ችግር ያለ ይመስላል፡፡ የ1997ቱ ምርጫ ብዙ ነገሮችን አመላክቶ ያለፈ ነው፡፡ ሕዝብ ብዙ ጊዜ የተለያዩ ጥያቄዎችን ጠይቆ ተገቢ መልስ ባለማግኘቱ በ1997ቱ ምርጫ ኢህአደግን ከተማ ቀመሱ ሕዝብ በሙሉ በካርድ ቀጣው፡፡ አልፈልግህም አለው፡፡ በዚያን ወቅት ኢህአዴግ ተርፎ ከሆነ የተረፈው በገጠሩ ሕዝብ ነበር፡፡

ዛሬ ግን እናንተ የሕዝብ አገልጋይ ሆናችሁ በመንግሥትና በሕዝብ መካከል አገናኝ ድልድይ ናችሁ፡፡ ድልድይ ደግሞ በሁለት የተለያዩ ክፍሎች ገደልም ይሁን ወንዝ ያላገናኘውን ሕዝብ በቀላሉ እንዲገናኙ የሚያደርግ ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓት የኢህአዴግ ካድሬ ይሁንም አይሁን የሕዝብ ውክልና ማግኘት ከሕዝብ መለየት ከሕዝብ አስተሳሰብ ውጭ መሆን ማለት አይደለም፡፡ በዚህ የተለያዩ ጊዜ ሕዝብን በሚያበሳጩ አዋጆች ተሳትፋችሁ ይህ አዋጅ በዚህ በኩል ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ይቅር ይመከርበት ብላችሁ ብትናገሩ የወከላችሁን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን እያገለገላችሁት ያለውንም ሥርዓት ከአደጋ እንደማትጠብቁት ግልፅ ነው፡፡

"ስለዚህ ውድ ተወካዮቻችን" እባካችሁ መናገር በሚገባችሁ ሰዓት ብቻ ተናገሩ ዝም ማለት በተገባችሁም ጊዜ ዝም በሉ፡፡

# የመብት ጥሰት እየተፈፀመ መሆኑን ሰመጉ አስታወቀ

በደቡብ ክልል ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰት እየተፈፀመ መሆኑን የሰብአዊ መብት ጉባዔ /ሰሙጉ/ አስታወቀ፡፡ ሰመጉ ይህንን ያሳወቀው ሰሞኑን ባወጣው 18ኛና 19ኛ መደበኛ መግለጫው ነው፡፡ በ18ኛ መግለጫው ላይ እንደሚዘረዘረው "በገዋታ ወረዳ የሚኖሩ የኦሮሞ ማህበረሰቦች በራሳቸው ቋንቋ የመማር እድል እንዲሰጣቸውና ሕዝቡ በማህበር ተደራጅቶ ለልማት የመንቀሳቀስ ጥያቄያቸውን ለሚመለከተው አካል ከወረዳ እስከ ፌዴሬሽን ም/ቤት በሠላማዊ መንገድ አቅርበው መብታቸውን ለማስከበር በመንቀሳቀሳቸው ምክንያት ብዙ በደሎችና የሰብአዊ መብት ጥሰት ደርሶባቸዋል፤እየደረሰባቸውም ይገኛል፡፡ በዶማ ቀበሌ ላይ ጳጉሜ 02 ቀን 2003 ዓ.ም የ10 ቀበሌ ሕዝብ በመጥራት ስብሰባ በተደረገበት ወቅት የወረዳው ባለሥልጣናት በገዋታ ወረዳ የሚኖር የኦሮሞ ሕዝብ ጥያቄዎች "ልክ ስላልሆነ አይፈቀድላችውም በኛ ሥር ዝቅ ብላችሁ መኖር አለባችሁ፤ያለበለዚየ እናንተ አሸባሪዎች ናችሁ" ከመባላቸው በተጨማሪ ሌሎች ማስፈራሪያ ንግግሮችን በመናገር በሕገ-መንግሥቱ የተሰጣቸውን መብት እንዳይከበርላቸው በማድረግ ተፅዕኖ አሳድረውባቸዋል፡፡

በየቀበሌው ክትትል እየተደረገባቸው ንብረታቸው የተቃጠለባቸው ከቦታቸው የተፈናቀሉ ሰዎች እንደሚገኙ ስመጉ ገልጿል፡፡ 20 ሰዎች በህገወጥ መታሰራቸውን 33 ሰዎች ንብረታቸው የተቃጠለባቸውና ከቦታቸው የተፈናቀሉ መሆኑን ያብራራል፡፡

በቁጥር 19ኛ መደበኛ መግለጫው ደግሞ "የላንቴ ቀበሌ የመሬት ዴስክ ኃላፊና የቀበሌው ሊቀመንበር ከአርባ ምንጭ ዙርያ ወረዳ የካቢኔ አባልንና የወረዳውን ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ፣የወረዳውን ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት፣ኃላፊና የወረዳውንየፖለቲካድርጅትኃላፊውን፣ከዞንና ከክልልም የሚገኙ ባለሥልጣናትንም በመጨመር በሕገ-ወጥ መንገድ መሬትን ለራሳቸው፣ለዘመዶቻቸው፣መሬት ላላቸው ገበሬዎች፣ለፖሊሶችና ለመንግሥት ሠራተኞች እንዲሁም ከሌላ ቀበሌም ለመጡ ሰዎች ያለመመሪያና ደንብ በ2002 ዓ.ም ደለድለዋል፡፡ በዚሁ ምክንያት የቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ ተሰብስቦ ሕገ-ወጥ ድርጊት እየተፈጸመ በመሆኑ የደን መጨፍጨፍ፣በጎርፍ መልክ አፈሩ ወደ አባያ ኃይቅ እየገባ ኃይቁ የገበሬዎችን መሬትና አትክልት እያጥለቀለቀ ከፍተኛ ችግር መፍጠሩን በመጥቀስ ለደ/ብ/ብ/ሕ/ ክልል ግብርና ቢሮ የተፈጥሮ ሀብትና አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን በ18/05/2003 ያመለከቱ፡፡" መሆኑን ይዘረዝራል፡፡ በዚሁ ምክንያት 33 ሰዎች በህገወጥ መንገድ የታሰሩ ሰዎች መኖራቸውን 3 ሰዎች ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሰዎችን አስረው በሌሉበት ቤታቸው መፈተሹን ይህንን ህገ-ወጥ ድርጊት በማጋለጣቸው ሁለት ሰዎች ከሥራ መፈናቀላቸውን አስታውቀዋል፡፡

# የአዲስ አበባ ሕዝብ ሆይ! መሬትህን አታስነካ!


በበለጠ ጉሹ ወ/ሚካኤል

በርእሱ ላይ የተመለከተውን መልዕክቴን ለተከበረው የአዲስ አበባ ሕዝብ ለማስተላለፍ የፈለግሁበት ጥቂት መከንያቶች አሉኝ:: አንደኛ፣በአደስ አበባ የብዙ ዓመታት ነዋሪ እንደመሆኔ፣ሕዝቡን በሚገባ አውቀዋለሁ የሚል እምነት አለኝ:: ሁለተኛ፣የአዲስ አበባ ሕዝብ በብሔረሰብ ስብጥሩም ሆነ በአመለካከቱ የመላ ኢትዮጵያን ሕዝብ ይወክላል የሚል ግምት ስለአለኝ ነው:: ሶስተኛ፣ በ2005 /መስከረም ላይ ይመስለኛል/ የአዲስ አበባ ሕዝብ የክልል ምርጫ እንደሚያካሂድ ኢህአዴግ ፕሮግራም ስለያዘለት፣ምንአልባት ለምርጫው ውሳኔ የሚያግዙ አንዳንድ ሐሳቦችን ከወዲሁ ለማካፈል እችላለሁ በማለት ነው::

የአዲስ አበባ ሕዝብ ስል፣ኢህአዴግ በሚወረውርላቸው ፍርፋሪ ተደልለው ሕሊናቸውን የሸጡትንና ሀገሪቱን የከዱትን ጥቂት ሰዎች አይመለከትም:: ይህ አናሳ የሕዝብ ስብስብ ከኢህአዴግ ጥቅም መደለያ እየወሰዱ አባላቱንና ደጋፊዎቹን፣ከመንግሥት መሬት ወስደው መኖሪያ ቤታቸውን ከሠሩ በኋላ ይህንን አከራይተው በመንግሥት ቤቶች ውስጥ በአነስተኛ ኪራይ የሚኖሩትን፣የራሳቸው መኖሪያ ቤት እያላቸው አንድና ከዚያም በላይ ኮንዶሚኒየምቤቶችንየወሰዱትን፣ያለችሎታቸው በመንግሥት መ/ቤት የሥራ ዕድል ተሰጥቶአቸው ከፍተኛ የሚባል ደመወዝ የሚበሉትን፣ሕገ-ወጥ ንግድ እንዲያካሂዱ የተፈቀደላቸውን፣ወዘተ የሚያካትት አይደለም:: እነዚህ በራሳቸው ኪራይ ሰብሳቢዎች /ቋንቋው የራሳቸው ነው/ ስለሆኑ ተጠያቂዎች እንጂ ተጠቃሚዎች አይደሉም:: በቀላሉ መገመት እንደሚቻለው ይህ የሕዝብ ስብስብ ከጠቅላላው የአደስ አበባ ሕዝብ ጋር ሲነፃፀር ቁጥሩ አናሳ ነው:: ስለዚህ እኔ የማወሳው ስለ ብዙሃኑ የአዲስ አበባ ሕዝብ ነው::

እንግዲህ፣በርእሱ እንደተመለከተው እኔ አንድ አናሳ ዜጋ ለተከበረው የአዲስ አበባ ሕዝብ ለመስጠት የምፈልገው ምክር "መሬትህን አታስነካ" የሚል ነው:: እንደሚታወቀው፣ "ሊዝ" የሚባል የባዕድ ቋንቋ ያመጣብን የኢህአዴግ መንግሥት ነው:: "ሊዝ" የእንግሊዘኛ ቃል ሲሆን፣በአማርኛ "ኪራይ" እንደማለት ነው:: በእንግሊዘኛ ሲፃፍ "lease" ተብሎ ነው:: በዚህ ተርጓሜ፣የመሬት አከራይ ኢህአዴግ ሲሆን፣ተከራይ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው:: እግዚአብሔር ያሳያችሁ አንድ ኢትዮጵያዊ ዜጋ /ወንድም ሆነ ሴት/ ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርስቲ ሳይገባ፣ሳይማር፣ሳይመራመር፣በተፈጥሮው ብቻ የአገሩ፣የመሬቱ ባለቤት መሆኑን በሚገባ ጠንቅቆ ያውቃል:: በሊዝ ገመድ መታነቁን ለመረዳት ይሳነዋል ተብሎ አይታሰብም:: የኢህአዴግ የመሬት ፖሊሲ የተገላቢጦሽ መሆኑን መረዳት ቀላል ነው:: እንዴት መንግሥት ያውም በነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ያልተመረጠ መንግሥት "የኢትዮጵያ መሬት በሙሉ የእኔ ነው፤ሕዝቡም የእኔ ተከራይና ጭሰኛ ነው" ማለት ይችላል?! እውነታው ግን ኢህአዴግ ይህን እያለን ነው::

ኢህአዴግ ራሱ በፃፈው ሕገ-መንግሥት ውስጥ፣ "መሬት የመንግሥትና የሕዝብ ነው" ይላል:: ይህ ዓረፍተ ነገር አቀማመጡ ራሱ ግድፈት አለበት:: መቅደም ያለበት "መንግሥት"ሳይሆን፣ "ሕዝብ" ነው:: እንዲያውም፣መንግሥት የሕዝብ ወኪል ስለሆነ፣ባለቤቱ ሕዝብ እያለ ወኪሉ የሚጠቀስበት ምክንያት አይኖርም:: ስለዚህ አንቀፁ መፃፍ ያለበት እንደሚከተለው ነው፤ "መሬት የሕዝብ ነው"፣አራት ነጥብ:: ወረድ ብሎ ደግሞ "መሬት አይሸጥም አይለወጥም" የሚል አንቀፅ እናገኛለን:: ይህ አንቀፅ ለምን አስፈለገ? መሬት እግዜር በነፃ የሰጠን የተፈጥሮ ሀብት ነው:: መሬት የሰው ልጅ መገልገያ እንደመሆኑ፣በፈለግነው መንገድ ልንጠቀምበት እንችላለን:: እሴት (Value) እና ዋጋ (Price) ያለው ሀብት ስለሆነ፣ዜጐች በግል ንብረትነት ሊይዙት፣ ሊሸጡት፣ ሊለውጡት፣ ሊያከራዩት፣ በወለድ አገድ ሊያሲዙት፣ሊያወርሱት ወዘተ. ይችላሉ:: የወል /የጋራ/ ንብረት አድርገንም ልንጠቀመበት እንችላለን:: የሕዝቡ ፍላጐት ከሆነም፣ከፊሉን መሬት በነፃና ፍትሐዊ መርጫ በመረጥነው መንግሥት ወኪልነት በ "ሊዝ" መልክ እንዲተዳደር ልንፈቅድ እንችላለን:: እዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን ቁምነገር መሬት በሕዝቡ ፍላጐትና ውሳኔ መሠረት በተፈለገው የይዞታ ዘዴ (በግል ንብረት፣በወል ንብረት፣በኪራይ፣ወዘተ) ልንጠቀምበት መቻላችን ነው::

ሌላ አንድ መሠረታዊ ፍሬ ነገርም አለ:: ይኼውም መሬት እግዜር በነፃ የሰጠን የተፈጥሮ ሀብት እንደመሆኑ ከመነሻው የመሬት ክፍፍል ፍትሐዊ መሆን ይገባዋል:: በረጅሙ የኢትዮጵያ ታሪክ የህን መርህ ተግባራዊ ለማድረግ የሞከረ መንግሥት የደርግ ወታደራዊ መንግሥት ነው:: የኢህአዴግ መንግሥት ግን የህንን እየቀለበሰው ነው:: የመሬት ክፍፍል ፍትሐዊ መሆን አለበት የሚለው መርህ በተለይ በከተማ በግልፅ የምንገነዘበው ነው:: የከተማ ቦታን በውክልና ማስተዳደር ያለበት በነፃና ፍትሐዊ ምርጫ የተመረጠ መንግሥት ነው:: ለምሳሌ አዲስ አበባን ብንወስድ፣የደርግ መንግሥት ያደርግ እንደነበረው፣የራሳቸው መኖሪያ ቤት የሌላቸው ነዋሪዎች አንድ የመኖሪያ ቤት ለመሥራት የሚያስፈልገውን የቦታ ድርሻቸውን በነፃ ማግኘት ይገባቸዋል:: እርግጥ ቦታ ለመቆጠብ በነፃ የሚሰጠው ቦታ የግል መኖሪያ ቤቶችን / ቪላዎችን /ለመሥራት በመሆን ፈንታ ብዙ ሰዎችን በአነስተኛ ቦታ ማኖር ለሚችሉ የጋራ መኖሪያ ሕንፃዎች (apartment buildings) ቢሆን ይመረጣል:: መሆን ያለበት ይህ ነው:: ቦታው ግን በነፃ ነው መሰጠት ያለበት:: ለጋራ የመኖሪያ ሕንፃ ግንባታ መሬት በነፃ የተሰጣቸው ዜጐች በማኅበር ተደራጅተው የራሳቸውን የቁጠባ ገንዘብ ከባንክ ከሚያገኙት ብድር ጋር በማቅናጀት የመኖሪያ ሕንፃውን ራሳቸው ያስገነባሉ:: በቃ! ሌላ ጣጣ አያስፈልግም!!

በሌላበኩል ጉዳዩን እንደ ኢህአዴግ ላለማወሳሰብ ለሁለተኛ ጊዜ ከመነግሥት ቦታ በነፃ ወይም በአንስተኛ ክፍያ ወስደው ተጨማሪ ቤት አለመሥራታቸው እየተረጋገጠ ለምሳሌ በአዲስ አበባ ከተማ የራሳቸው መኖሪያ ቤቶች ያሏቸው ነዋሪዎች ለቦታ የዞታቸውና ለቤቶቹ የባለቤትነት ካርታና ደብተር ሊሠጣቸው ይገባል:: በውርስ የተገኙና እንዲሁም በነፃ ገበያው ላይ የተገዙ የግል ቤቶች ተመሳሳይ ካርታና ደብተር ይሠጣቸዋል:: በመጀመሪያ መደረግ ያለበት ይህ ነው:: የመኖሪያ ቤት ማለት አጥር፣ግቢ፣ጣሪያ፣ግድግዳና ወለል ማለት ነው:: የዚህ ዓይነት የቦታ ካርታ ያላቸው ዜጎች ቤታቸውን ከነቦታው በጊዜው ዋጋ ሸጠው የመጠቀም መብት ሊኖራቸው ይገባል:: የኢህአዴግ መንግሥት ያወጣው የሊዝ አዋጅ ግን ባለይዞታዎች ሸጠው መጠቀም የሚችሉት በቦታው ላይ የሠፈረውን ቤት / ጣሪያና ግድግዳውን/ ብቻ ነው የሚለው፤መሬት የመንግሥት ብቻ ነው ስለሚል ኢህአዴግ ሰሞኑን ሕዝቡን እየሰበሰበ ይህን ለማስተባበል እየሞከረ ነው፤ግን አዋጁ እስካልተሻረ ድረስ የኢህአዴግን ቀላማጅ ካድሬዎች ማመን አይቻልም:: ለመሆኑ፣ኢህአዴግ ራሱ ያወጣው ሕገ-መንግሥት "መሬት የመንግሥትና የሕዝብ ነው" እያለ እንዴት ተደርጐ ነው መሬት የመንግሥት ብቻ የሚሆነው?!

ኢህአዴግ ከቦታ ሽያጭ /ሊዝ/ የማገኘውን ገንዘብ ቤት ለሌላቸው ኮንዶሚኒየም እሠራበታለሁ ይላል:: ቤት የሌላቸው ነዋሪዎች ከኢህአዴግ የሚፈልጉት የጋራ መኖሪያ ቤቶች ለመሥሪያ የሚሆን ነፃ ቦታ ነው፤ ቦታውን በነፃ ካገኙ እነሱ ራሳቸው በማሕበር ተደራጅተው የመኖሪያ ሕንፃዎቹን ይሠሯቸዋል:: እንዲያውም በኮንዶሚኒየም ግንባታ ረገድ የእስካሁኑ የኢህአዴግ መንግሥት የአፈፃፀም ሪኮርድ በጣም ዝቅተኛ ስለሆነ ይህ የቤት ግንባታ ስትራተጂ መቀየር ያለበት ይመስለኛል:: ለመሳሌ በአዲስ አበባ በስምንት ዓመታት የተሠሩት የኮንዶሚኒየም ቤቶች ብዛት ሰማኒያ ሺ (80,000) ገደማ ሲሆን በ1996 አካባቢ የተመዘገቡት የቤት ፈላጊዎች ቁጥር ከአምስት መቶ ሺ (500,000) በላይ ነበር:: ስለዚህ ኢህአዴግ "ኮንዶሚኒየም ለመሥራት ነው" የሚለው ክርክር አያዋጣውም::

ሌላው ከዚሁ ጋር የተያየዘው ጉዳይ ኢህአዴግ በከተማ ልማት ሽፋን የሚያፈርሳቸው "ደሳሳ ቤቶች" ናቸው:: ለ "ደሳሳ ቤቶቹ" በጣም ዝቅተኛ የገንዘብና የቦታ ማካካሻ እየሰጠ ቦታውን በካሬ ሜትር ለኢንቨስተር ተብዬዎች እስከ ሃያ ሺ ብር (20,000) ይሸጣል ወይም በሊዝ ያከራያል:: እኔ የምለው ደግሞ ከዚህ በጣም የተለየ ነው:: በመጀመሪየ፣ለ "ደሳሳ ቤቶቹ" ባለቤቶች የቦታ ካርታና የቤት ባለቤትነት ደብተር / ካስፈለገ/ ይሠጣቸው:: ከዚያም እነዚህ ሕጋዊ ባለንብረቶች ቦታውን ለኢንቨስተር ተብዬዎቹ በጊዜው ዋጋ ይሸጡላቸው:: የቦታው ሽያጭ ዋጋ በሙሉ ለባለቤቱቹ ይሆናል:: በዚህ ገንዘብ ሌላ የመኖሪያ ቤት ሠርተው፣በሚተርፈው ገንዘብ ደግሞ የራሳቸውን "ቢዝነስ" ያቋቁሙበታል:: ከዚህ የበለጠ ልማት አለን? ልማት የሚካሄደው በኢህአዴግ ብቻ ነው እንዴ? እንዲያውም፣ በሀገራችን ከሰማኒያ በመቶ (80%) ላነሰው የልማት ሥራ መካሄድ ያለበት በዜጐች ነው / በግል፣በቤተሰብ እና በአክስዮን ማኅበር መልክ/:: ስለዚህ ኢህአዴግ ይህም የመከራከሪያ ነጥብ አያዋጣውም::

ዋናው ችግር የኢህአዴግ መንግሥት የመሬትን ሽያጭ /ሊዝ/ አቢይ የመንግሥት በጀት ገቢ ምንጭ ለማድረግ መምከሩ ነው:: ኢህአዴግ /አሁን እንደሚያደርገው/ "መሬት ሁሉ የኔ ነው" ብሎ ለመሸጥ ከሞከረ፣በአብዛኛው በሙስና ገንዘብ ካገኙ ጥቂት ግለሰቦች በስተቀር መሬት ለመግዛት የሚችለው ማን ነው? ኢህአዴግ መሬት በሙሉ በቁጥጥሩ ሥር ስለሆነ፣ ለገበያው የሚያቀርበውን የመሬት መጠን እየገደበ፣ዋጋውን እንደሚያንረው የታወቀ ነው:: ለዚህም ነው በካሬ ሜትር እስከ ሃያ ሺ ብር የሚቸበችበው:: ታዲያ፣ሕዝቡ የት ይኑር? የት ሆኖ ያምርት? ስለዚህ፣ትክክለኛው መፍትሔ የደርግ መንግሥት ተግባራዊ ያደረገው ፖሊሲ ነው /ከሞላ-ጎደል/:: ለመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ቦታ በነፃ መስጠት፤ ለማምረቻ /ለመሥሪያ ቤት/ የሚሆን መሬት ደግሞ በነፃ ወይም በአነስተኛ ክፍያ (nominal fee/price) ማቅረብ ነው ትክክል የሚሆነው:: በሌላ በኩል መንግሥት የቤት ቀረጥ (property tax) የመሬት ታክስ (Land tax) የቤት ሽያጭ ታክስ (house Sales tax) ወዘተ የማስከፈል ሥልጣን አለው:: በነገራችን ላይ ፍትሐዊ የመሬት ክፍፍል ሶሻሊስታዊ ፖሊሲ ተደርጐ መወሰድ የለበትም:: ለካፒታሊስት ሥርዓት ግንባታ ራሱ ትክክለኛውን የመሬት ይዞታ መደላድል የሚፈጥር ነው:: ብዙ መሬት ያለውና ምንም መሬት የሌለው ሰው በነፃ ገበያ ነፃ ውድድር ሊያካሂዱ አይችሉምና! ከመነሻው (initial conditions) ይህ ካልሆነ ካፒታሊዝም ከፊውዳሊዝም በሚወርሰው የገቢና የሀብት ልዩነት ምክንያት ኢ-ፍትሐዊ መሆኑን ይቀጥላል::

በከተማ ቦታ አስተዳደር የመንግሥት ዋናው ሚና ትክክለኛ የከተማ እና የመሬት አጠቃቀም ፕላን አውጥቶ ተግባራዊ ማድረግ ነው:: ለምሳሌ፣አደስ አበባን ብንወስድ፣ከተማው አጠቃላይ (master) እና ዝርዝር ፕላን ከወጣለት በርካታ ዓመታት ተቆጥረዋል:: ግን በተለይ በዘመነ ኢህአዴግ ብዙ ግንባታዎች የሚካሄዱት የከተማውን ፕላን ተከትለው አይደለም:: በዚህ ምክንያት ብዙ የተዘበራረቁ ነገሮች እየታዩ ነው:: የኢህአዴግ ባለሥልጣኖች እርስ በእርስ ለመጠቃቀም ሲሉ፣በርካታ ግንባታዎች ከፕላን ውጪ ይሠራሉ:: በዚህ ረገድ ውስጥ- አዋቂዎች ብዙ የሚሉት ነገር ስላለ ይህንን ጉዳይ ለእነሱ ትቼ፣ወደ ተነሳሁበት ርእስ ልመለስ::

"የአዲስ አበባ ሕዝብ ሆይ! መሬትህን አታስነካ" ብዬ ነው የጀመርኩት:: አሁንም የአዲስ አበባ ሕዝብ ሆይ! በመጀመሪያ እርስ በእርስ በቅብብሎሽ ተነጋገር፤በመላ ከተማዋ የሕብረትና የትግል አንድነት ሰንሰለት (network) ፍጠር፤ ከዚያም፣ የጐረቤትህ ቤት ሲፈርስ ዝም ብለህ አትመልከት፤ "ነግ በእኔ" ብለህ ለወገንህ ድረስለት:: አጥርህን፣ግቢህን፣ጣራህን፣ግድግዳህን እና ወለልህን አታስነካ! የባለቤትነት ካርታና ደብተር ከሌለህ መጀመሪያ መንግሥትን የምትጠይቀው ይህንን ነው:: የቦታ ካርታና የቤት ባለቤትነት ደብተር /ሁለተኛውም ካስፈለገ/ ይሠጠኝ ብለህ በሕብረት ድምፅህን ከፍ አድርገህ አሰማ:: መኖሪያ ቤት የሌላችሁ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች መጠየቅ ያለባችሁ፣ "መኖሪያ ቤት የምንሠራበት ቦታ በነፃ ይሰጠን" ብላችሁ ነው:: የመንግሥት ኮንዶሚኒየሞች መቼም አይደርሷችሁም:: ኢህአዴግ ቤት ያላቸውንና የሌላቸውን ለማጋጨት ሴራ እየጐነጐነ መሆኑ ተደርሶበታል:: "ከቦታ ሽያጭ የሚገኘውን ገንዘብ ኮንዶሚኒየም እሠራበታለሁ" እያለ ነው:: ይህ ይልቅ ውሸት ነው፤ ምክንያቱም ኢህአዴግ እስካሁን የሠራቸውን ኮንዶሚኒየሞች ውጪ የሸፈነው በአብዛኛው ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሚወስደው ብድር ነው:: ወደ 11.2 ቢሊዮን ብር ወስዶ መልሶ ለመክፈል የቻለው 2.2 ቢሊዮን ብር ገደማ ብቻ ነው:: ከመሬት ሽያጭ የሚያገኘውን እንዴት እንደሚያጠፋው እግዚአብሔርና ራሱ ብቻ ናቸው የሚያውቁት!

የአዲስ አበባ ሕዝብ ሆይ ተንቀሃል! ኢህአዴግ ሳያማክርህ "አዲስ የከተማ ቦታ ሊዝ አዋጅ" ብሎ ካወጣ በኋላ፣ "የተራበ በሆዱ ይፈታል" በሚል የሞኝ ፈሊጥ፣የቤተመንግሥት ምግብ እያበላ፣"አዋጁን ከማውጣቴ በፊት ለውይይት አለማቅረቤ ክፍተት ነው፤ ለወደፊቱ ጥሩ ልምድና ተሞክሮ ይሆነኛል" እያለ እያላገጠብህ ነው:: ኢህአዴግ እንዴት እንደቀለደብህ ይበልጥ ለማወቅ ከፈለግህ የ"ፍትሕ" ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ተመስገን ደሳለኝ በጋዜጣዋ ላይ ጥር 4 2004 ዓ.ም ያቀረበውን ድንቅ ሐተታ ተመልከት:: በአንፃሩ አቶ መኩሪያ ኃይሌና አቶ ኩማ ደመቅሳ የሊዝ አዋጁን በተመለከተ ያቀረቡትን "መግለጫና ማብራሪያ" አዳምጠህ ከሆነ፣ "እግዜር ውሸት ተናግሮ ከመቀላመድ፣ከመቀበጣጠርና ከመንተባተብ አውጣኝ" የሚያሰኝ ሆኖ አግኝቼዋለሁ:: እውነት ለመናገር አንድ ቃል ይበቃል፣ ሸፍጥን ለመሸፈን ግን አዋጅ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የአፈፃፀም መመሪያ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ የአፈፃፀም ማኑዋል ወዘተ. ያስፈልጋል::

የአዲስ አበባ ሕዝብ ሆይ አሁንም እደግመዋለሁ፤መሬትህን አታስነካ! የራስህን ሕይወት፣ሚስትህን፣ልጆችህን፣መሬትህንና ንብረትህን ከዘረፋና ከንጥቂያ ለማዳን የምትፈፅመው ያልሞት ባይ ተጋዳይነት ገድል ስምህ በጀግኖች ታሪክ ውስጥ በወርቅ ቀለም እንዲፃፍ ያደርገዋል! ሚያዝያ 30ን እና ግንቦት 7ን /1997/ ደግመን ሌላ ታሪክ እንሥራ! ከኢህአዴግ ጐሣዊ፣ወታደራዊ አምባገነን አገዛዝ ሙሉ በሙሉ ነፃ እስክንወጣ ድረስ እነ አንዱዓለም አራጌን፣እስክንድር ነጋን፣በቀለ ገርባን፣ርዕዮት ዓለሙን፣ናትናኤል መኮንን እና ሌሎችበርካታ ለዴሞክራሲ፣ለፍትሕ እና ለአንድነት ሲሉ በወህኒ ቤት የሚማቅቁትን ወንድሞቻችንና እህቶቻችንን ሁልጊዜ ከኅሊናችን እንዳይጠፉ እናድርግ:: ስንደሰትም ሆነ ስናዝን እናስታውሳቸው:: እኛ ነፃ ስንወጣ እነሱም ነፃ ይወጣሉ:: ነፃ የምንወጣው ሳንፈራ ለሰብዓዊና ለዴሞክራሲያዊ መብቶቻችን ስንታገል ብቻ ነው! ስለዚህ የአዲስ አበባ ሕዝብ ሆይ መሬትህን አታስነካ!

# የዜጎች የንብረት ባለቤትነት መብት ይከበር ! !

## ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ (መድረክ) የተሰጠ መግለጫ

በአንድ አገር ውስጥ የሚኖሩ ዜጎች የባለአገርነት ስሜት እንዲኖራቸው የሚወጡ አዋጆች፣ መመሪያዎችና ድንጋጌዎች ሁሉ አብዛኛውን የሕብረተሰብ ክፍል ስምምነት ያገኙ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ መንግሥት ሕዝቡ የሚተዳደርበትን የትኛውንም አይነት ሕግ ሲያወጣ ማዕከል ማድረግ ያለበት የዜግነት መብትን ለማስጠበቅ፣ለማጎናጸፍ እንጂ አንገት የሚያስደፉ የሚያሸማቅቁ፣የሚያስፈራሩ አፋኝና ባጠቃላይ በመብት ገፈፋ ላይ የተመረኮዙ መሆን አይኖርባቸውም፡፡ የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣው አዋጅ ቁጥር 721/2004 ዓ.ም በማን አለብኝነት የዜጎችን ንብረት የማፍራት፣የመሸጥ፣ የመለወጥ እና የመጠቀም መሠረታዊ መብቱን በሕግ ሽፋን የገፈፈ አዋጅ ነው፡፡ በኢህአዴግ የሚመራው መንግሥት በሥልጣን በቆየባቸው 20 ዓመታት ሲያደርግ እንደነበረው ሁሉ ዛሬም የሚወጡ ህጎች ከፖለቲካዊ ጠቀሜታና የሥልጣን ዕድሜ ከማራዘም አንፃር ብቻ ታይተው በሕዝብ ላይ የሚጫኑ ናቸው፡፡

የሊዝ አዋጅ አወጣጥና የአፀዳደቁን ሂደት ብንመለከት ፈፅሞ የተለመደውን አሰራር የተከተለ አይደለም፡፡ የዚህ አዋጅ አፀዳደቅና አቀራረብ ሁለት መሠረታዊ ግድፈቶች ይታዩበታል፡-

1ኛ. በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀፅ 3 "የኢትዮጵያ ብሄሮች ብሄረሰቦች እና ሕዝቦች ሉአላዊነታቸው የሚገለፀው በዚህ ሕገ-መንግሥት መሠረት በሚመርጣቸው ተወካዮቻቸውና በቀጥታ በሚያደርጉት ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ ይሆናል፡፡" ይላል፡፡ ይሁን እንጂ በአዲሱ የሊዝ አዋጅ መሬትን በመሰለ መሠረታዊ ጉዳይ ላይ የሉአላዊ ሥልጣን ባለቤት የሆነውና በቀጥታ ጉዳዩ የሚመለከተው ሕዝብ ጉዳዩ ቀርቦለት በነፃነትና በግልፅነት እንዲወያይበት አልተደረገም፡፡

2ኛ. ኢህአዴግ በፓርላማው የወጣው የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ስነ-ምግባር ደምብና አሰራር እንኳን እንደሚገልፀው ከስብሰባው 48 ሰዓት በፊት የአንድ አዋጅ ረቂቅ ለም/ቤቱ አባል መድረስ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ የፓርላማ አባሉ በዚህ 48 ሰዓት ውስጥ ረቂቅ አዋጁን መርምሮና ባለሞያዎችን አማክሮ ይቀርባል፡፡ ረቂቅ አዋጁም በፓርላማው ከታየ በኋላ ወደሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ ይመራል፡፡ ኮሚቴውም ባለሞያ ጋብዞና አማክሮ ለሕዝብና ለሚዲያው ክፍት አድርጎ ያወያያል፤ሃሳቡን አዳብሮ በድጋሚ ለፓርላማ ያቀርባል፡፡ ፓርላማው ሲፈልግ ያፀድቀዋል፡፡ ሳይፈልግ ውድቅ ያደርገዋል፡፡ ግልፅ የሆነው አሰራር ይህ ሆኖ ሳለ ለራሱ ከመሰለውና ለፖለቲካ ፍጃታ ይጠቅመኛል ካለ እንኳን የሥነ ምግባር ደምብና አሰራር ቀርቶ ሕገ-መንግሥት የሚጥሰው የኢህአዴግ መንግሥት ትልቁን የዜጎች መብት የሚመለከተውን የሊዝ አዋጅ ለፓርላማ አባላት ማታ 12፡00 አድሎ ጧት 3 ሰዓት አዋጅ ሆኖ እንዲፀድቅ አድርጓል፡፡

እዚህ ላይ አንዳንድ ጉዳዮችን ወደ ኋላ መለስ ብሎ መዳሰስ ጠቃሚ ነው ብለን እናምናለን፡፡ በብዙ ጉዳዮች በኢህአዴግ መንግሥት በወንጀለኝነት የሚጠቀሰው ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ እንኳን የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን የመንግሥት ንብረት ለማድረግ ባወጣው አዋጅ ቁጥር 47/67 ምዕራፍ ሁለት አንቀፅ 1 "አንድ ቤተሰብ ወይም ግለሰብ ለመኖሪያ ቤት መስሪያ የሚያውለው እስከ 500 ካሬ ሜትር የሚደርስ የከተማ ቦታ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በይዞታ ሊሰጠው ይችላል፡፡ ባለይዞታው ሲሞት የሟች ሚስት ወይም ባል ወይም ልጆች በቦታው ተተክተው የመጠቀም መብት ይኖራቸዋል፡፡" ይላል፡፡ ለም/ቤት ወይም ድርጅት በሚቀርበው አቤቱታ መሠረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደሚሰጥ በዚሁ መዕራፍ አንቀፅ 2 እና 3 ይገልፃል፡፡ በዚሁ አዋጅ ምዕራፍ 3 እና 12 የከተማ ቤት ስለማስተላለፍ በሚለው ሥር "አንድ ቤተሰብ ግለሰብ ወይም ድርጅት በከተማ ቤቱ የመጠቀም ወይም ይህንኑ ቤት የማውረስ የመሸጥ ወይም የመለወጥ መብት አለው፡፡" ይላል፡፡

ይህንን አዋጅ ስንመለከት የአገሪቱን የከተማ ነዋሪዎች ከግለሰብ ጭሰኝነት ነፃ ያወጣ የከተማ ቦታን የመሸጥ የመለወጥና የባለቤትነት ክብር እንዲጎናፀፉ ያስቻለ ነው ማለት ይቻላል፡፡ አንድ አዋጅ ትክክለኛ አዋጅ ነው፤ሕዝባዊ ነው፤ሊባል የሚችለው ብዙሃኑን ሕዝብ ሲያስደስት ነው፡፡ ኢህአዴግ በየጊዜው የሚያወጣቸው አዋጆች ግን ገዢዎችን የሚጠቅም ሕዝብና ሀገርን የሚጎዳ ዜጎችን አንገት የሚያስደፉ መብትና ጥቅምን የሚጋፉ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ሰሞኑን የወጣውን አዋጅ 721/2004 ዓ.ም የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣ አዋጅን ብንመለከት የሚያሳየን ይህንኑ ነው፡፡ የዚሁ አዋጅ ክፍል ሁለት አንቀፅ 6 ነባር ይዞታዎች ወደ ሊዝ ስሪት ስለሚቀየሩበት ሁኔታ ከተራ ቁጥር 1-7 ተዘርዝሮ ተቀምጧል፡፡ የኢህአዴግ ሹመኞች "የነባር ይዞታዎችን አይመለከትም፡፡ ዝርዝር መመሪያ አልወጣም፡፡ ተረጋጉ" እያሉ በሕዝብ ላይ ውዥንብር ይፈጥራሉ፡፡ ነባር ይዞታዎችን አይመለከትም ቢሉም ሲሸጥ ሲለወጥ፣ሊዝ እንደሚገባ አዋጁ በግልፅ አዋጁ ደንግጓል፡፡ አንድ ሰው ነባር ይዞታን ሲገዛ ከባለንብረቱ ከሚከፍለው ክፍያ በተጨማሪ ለመንግሥት ያንኑ ቦታ የሊዝ ዋጋ ይከፍልበታል፡፡ ይህ አሰራር ብዙ ምርምር የማይጠይቅና ንብረት በማስተላለፍ ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ለማንም ግልፅ ነው፡፡ የነባር ይዞታው ባለቤት ቦታውን ሸጦ ሌላ አነስተኛ ቦታ ገዝቼ በተረፈችኝ ገንዘብ ሕይወቴን ልምራ ቢል የሚገዛው በሊዝ ነው፡፡ ነባር ይዞታዎች ከሊዝ የሚያመልጡት እንዴት ነው? ይዞታው ሳይሸጥ ሳይለወጥ የንብረት ዋጋ ሳይኖረው እንደ ጉልቻ በመቀመጡ ብቻ ከሊዝ አመለጠ ማለት ነውን?

አዋጁ የሕዝብን የአገሩ ባለቤትነት የሚነካ ነው፡፡ የሊዙ ጥሩነት "ነባር ይዞታዎችን ይነካል አይነካም" በሚለው አይለካም፡፡ የዜጋን ሁሉ ተስፋ ያጨለመ ነው፡፡ አዋጁ የአገሪቱን ሕዝብ ከይዞታ ባለቤትነት አሽቀንጥሮ ጥሎ መንግሥትን የመሬት ባለቤት የሚያደርግ ነው፡፡ አዋጁ አምባገነኖች በማን አለብኝነት የሚያወጡት አዋጅ ነው፡፡ ሕገ-መንግሥቱ "መሬት የሕዝብና የመንግሥት ነው" ቢልም ኢህአደግ ግን በራሱ ጠቅልሎ ሕዝብን ጭሰኛ አድርጎታል፡፡ ንብረት የማፍራት ሕገ-መንግሥታዊ መብቱን ነጠቆታል፡፡ በዚህም ሕዝብ አቋሙን በግልፅ አሳውቋል፡፡ ሕዝብ ከአዋጁ መውጣት በኋላ ለይስሙላ በተካሄዱ ስብሰባዎች ላይ በአዋጁ መውጣት ቁጣውን ገልጿል፡፡ ሕዝብ ትክክለኛ አቋም ወስዷል፡፡ ሕዝብ ሊደመጥ ይገባል፡፡ ሕዝብ መከበር አለበት፡፡ የሕዝብን እምነትና ፍላጎት በጡንቻ እየጨፈለቁ የሕዝብን ጩኸት እንደ ቁራ ጩኸት እየቆጠሩ መጓዝ ለማንም አይጠቅምም፡፡ ሕዝብ የማስጠንቀቂያ ደውሉን አሰምቷል፡፡ ሕዝብ የመደመጥ መብት አለው፡፡ በኢህአዴግ የሚመራው መንግሥት በተቆጣጠራቸው የሚዲያ ተቋማት የመሰለውን፣የሚፈልገውን በሕዝብ ስም እያስተላለፈ የሚያካሂደው ፕሮፓጋንዳ ለራሱም፣ለሕዝቡም፣ለአገርም እንደማይጠቅም አውቆ ሊያስብበት ይገባል፡፡

በአዋጁ ዙሪያ በመንግሥት ባለሥልጣናትና ካድሬዎች የሚሰጠው መግለጫና ከሕዝብ ለሚቀርበው ጥያቄ የሚሰጡት መልሶች የፌዝ መሆናቸው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክን (መድረክ) ያስገረመው ጉዳይ ነው፡፡ ይህም ነባር ይዞታህ እስከትሸጠውና እስከትለውጠው ድረስ ሊዝ አይገባም ማለት "ዶሮን ሲያታልሏት በመጫኛ ጣሏት" አይነት መሆኑ ነው፡፡ እነዚህ አካላት እንዳብራሩት "ነባር ይዞታዎች ወደ ሊዝ ስርዓት የሚቀየሩበት ሁኔታ ዝርዝር ጥናት ተደርጎ በ4 ዓመት ጊዜ ውስጥ ርምጃ ሊወሰድ እንደሚችል ነው፡፡" (አዲስ ዘመን ጥቅምት 22/2004 ዓ.ም) ከባለሥልጣናቱ ማብራሪያዎች ለመረዳት እንደተቻለው አዋጁ ከጥናት በፊት ቀድሞ የመጣ እንደመሆኑ የኢህአዴግ ሥርዓት የሕዝብን መብት ቤተ ሙከራ ማድረጉ አገዛዙና ሥርዓቱ የዜጎችን ጥቅምና ክብር ማዕከል ያላደረገ መሆኑን ሕዝባችን ይገነዘበዋል፡፡ በመድረክ ዕምነት ደግሞ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ተገቢው ጥናት መካሄድ ነበረበት እንላለን፡፡

ስለሆነም በገጠር ነዋሪው አርሶ አደር የይዞታው ባለቤት መሆን እንዳለበትና የከተማ ነዋሪውም የመኖሪያ ቤት የሰራበት መሬት ባለቤትነት እንደሚያረጋግጥ መድረክ በፖለቲካ ፕሮግራሙ ያሰፈረውን እውን ለማድረግ በተያያዘው ትግሉ እንደሚቀጥል እየገለፅን መላው ሕዝባችንም መብቱን የሚጋፉ አዋጆችንና ድርጊቶችን ለመቃወም በምናደርገው እንቅስቃሴ ውስጥ ከጎናችን እንዲቆም ሀገራዊ ጥሪችንን እናቀርባለን፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ (መድረክ)
ጥር 17 ቀን 2004 ዓ.ም
አዲስ አበባ

---

# አገርን ከውድቀት መታደግ የወቅቱ አንኳር ጥያቄ ነው

## አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) የህዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ

አገርና ዜግነት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ናቸው፡፡ አገር ያለ ዜጋ ዜግነትም ያለ አገር ከቶ አይታሰቡም፡፡ ካለፉት 60 እና 70 ዓመታት ጀምሮ በመካከለኛው ምሥራቅ የፍልስጤምና የእሥራኤል የከረረ ግጭት ለዓለም ሥጋት እስከ መሆን የደረሰውና ዛሬም መፍትሄ ያልተገኘለት በአገር የህልውና ጥያቄ ጉዳይ ነው፤ ሰው ያለ አገር ሰው ያለዜግነት ምሉዕ አይደለምና፡፡

ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ስንነሳ ኢትዮጵያዊነት ከደምና ከአጥንታችን ጋር የተዋሃደ ስለመሆኑ የማይሰማው ሰው የሚኖር አይመስለንም ፡፡ ኢትዮጵያዊነታችን የብዙ ሺህ ዓመታት ታሪክ ያለው ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ እንኳን ከአርባ ጊዜ በላይ በስም መጠቀሷ የታሪካችንን ጥንታዊነት በውል የሚያሳይ ነው፤ የዘመኑ መሪዎቻችን ይህንን ክደው የ100 ዓመት ታሪክ ሊለጥፉባት ቢሞክሩም የጥንት አባቶቻችን ይህችን አገር ከፍፁም ህልውናዋ ጋር ለኛ ለማውረስ ባካሄዱት የዘመናት ቅብብሎሽ የከፈሉትን ውድ ዋጋ ለአፍታ እንኳን መዘንጋት የለብንም፡፡ የአገራችንን ክብሯን ጠብቀን ለቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፍ ይጠበቅብናል፤ የትውልድ ሂደት እንደ ሰንሰለነት ነውና፡፡

ከሦስት ሺህ ዓመታት በላይ በህልውናዋ ፀንታ የቆየችውን ይህችን አገር የዛሬዎቹ የኢህአዴግ ካድሬዎች ሲሸራርፏትና ለባዕዳን አሳልፈው ሲሸጧት እጃችንን አጣምረን ዳር ቆመን ልንመለከተው አይጋባም፡፡ ኢህአዴግ የህልውናው እስትንፋስ አድርጎ በሚቆጥረው ህገ መንግሥት አንቀጽ 39 ላይ የሰፈረውን ሀሳብ ለማሳካትና ከኤርትራ መገንጠል በኋላ ቀሪውን የኢትዮጵያ ግዛት በብሄረሰብ ሸንሽኖ ለመነጣጠል ያደረገው ሙከራ በ1997 ዓ.ም ምርጫ ወቅት መራጩ ህዝብ ባሳየው ፍጹም ኢትዮጵያዊነት ሳይሳካለት ቀርቷል፡፡ አቶ መለስ ስልጣን እንደጨበጡ የባንዲራችንን ታሪካዊነትና ኢትዮጵያዊ ቅርስነት በማንቋሸሽ ከተራ የዱቄት መቋጠሪያ ጨርቅ እንደማይለይ አድርገው መናገራቸው አገሪቱ እንደ አገር በልበሙሉነት እንዳትቀጥል ገና ከማለዳው የወጠኑት ስልት መሆኑን መረዳት አያዳግትም፡፡

ከምርጫ 97 በኋላ ራሱን በመንግስትነት ሰይሞ ቤተመንግሥት የከተመው ኢህአዴግ የህዝብን ድምፅ ነፃና ፍትሐዊ ባልሆነ ምርጫ በ99.6 በመቶ ተመርጫለሁ ብሎ ሥልጣን መያዙ ዓለም የሚያውቀው ነው፡፡ ኢህአዴግ አምባገነናዊ ባህሪው ከዓመት ዓመት እየጨመረ መጥቷል፡፡ በዘር ከፋፍሎ የኢትዮጵያን አንድነት ለማዳከም የቀየሰው ስትራቴጂ የወጠነው ሴራ ባለመሳካቱ የአገሪቱን ለም መሬት እየቆረሰና እየሸነሸነ በበቆሎ ዋጋ ለባዕዳን መቸርቸር ከጀመረ ሰነባብቷል፡፡ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ውድ የኢትዮጵያ ልጆች በፈንጅ ላይ እየተረማመዱ ሕይወታቸውን ገብረው ከሻዕቢያ ያስመለሱትን የትግራይ ለም መሬት በሚስጥር ለሻዕቢያ ለመስጠት መስማማቱን አገር ያወቀው ፀሐይ የሞቀው ጉዳይ ነው፡፡ ይሄ አልበቃ ብሎት ከጎንደርና ከጋምቤላ ሰፋፊ መሬቶችን የሱዳን ግዛት ነው በሚል ቆርሶ የሰጠና በዚህም ሣቢያ የአገሬን መሬት አላስነካም ያለው ኢትዮጵያዊ ላለመልቀቅ እስከዛሬ አሻፈረኝ እንዳለ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ዳግም በኢንቬስትመንት ሰበብ የሰሜኑ ኢትዮጵያ ህዝብ የሚያርሰው መሬት ጠቦት በድህነት እየዳከረ ባለበት ሁኔታ ለሳዑዲ አረቢያና ለህንድ ሀብታሞች ከ50 እስከ 90 ዓመታት በሚቆይ የሊዝ ይዞታ በርካሽ ገንዘብ መቸብቸብን ተያይዞታል፡፡ በንቀትና በትዕቢት የተሞላው /ኢህአዴግ የአገሪቱ ምሁራን በወቅቱ የሰጡትን አስተያየት ሲያጣጥል ቢቆይም አለም አቀፍ ውግዘትንም እያስተናገደ ነው፡፡ የመሬት ወረራውን ተገቢ እንዳልሆነና አገርን በብርቱ እንደሚጎዳ የነገሩትን በንቀት ንግግር እያጣጣለው ይገኛል፡፡

ውድ ኢትዮጵያውያን እውን አገራችሁን ትወዳላችሁ? ኢትዮጵያ ቤታችሁ፣ ገመናችሁ፣ ትዳራችሁ፣ ህልውናችሁ እንደሆነች ይሰማችኋልን? እስቲ ፍልስጤማውያንን ተመልከቷቸው፡፡ በማያባራ የደም መፋሰስ ውስጥ የገቡት የአገር ጉዳይ የማንነት ጥያቄ ስለሆነባቸው ነው፡፡ ኢህአዴግ እኛን ከመናቁ የተነሣ የአገሪቱን መሬት እየቆረሰ ለባዕዳን ሲያድል ዝምታችን ምን የሚሉት ነው? "ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ" እንዲሉ ሆነና ዝምታችንን ከፍርሃት ስለቆጠረው ከአያት ከቅድመ አያት የወረሰውን ይዞታችንን ሊቀማን የእያንዳንዳችንን በር እያንኳኳ ነው፡፡

ላለፉት ግማሽ ምዕተ አመት በአምባገነን መሪዎች አስከፊ አገዛዝ የተማረሩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች አገራቸውን ጥለው በመሰደድ በባዕድ አገሮች ለባይተዋርነት ኑሮ ቢዳረጉም መቼም ቢሆን ኢትዮጵያዊነታቸውን ለአፍታ ያህል እንኳን አይዘነጉትም፡፡

ውድ ኢትዮጵያውያን በነዚህ ሦስት እና አራት ዓመታት ውስጥ የኑሮ ውድነቱና የህዝቡ ድህነት መላ ካልተበጀለት አገሪቱ አስፈሪ የሆነ የመበታተን አደጋ ሊያጋጥማት እንደሚችል ኢህአዴግ ራሱ በህዳር 2004 ዓ.ም ለተማሪዎችና ለመምህራን ውይይት ባዘጋጀው ሰነድ (ጥራዝ) ላይ በግልፅ አስቀምጦታል፡፡ ኢህአዴግ የአገዛዝ ዘመኑን ለማራዘም ሲል የአገሪቱን ህልውና እየናደ መሆኑን ልብ ልንል ይገባል፡፡ እምዬ ኢትዮጵያን ከመበታተን ለመታደግና ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውንና በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድነቷን ጠብቆ ለማቆየት መነሳት የሚገባን አሁን መሆኑን ተገንዝበን በፅናት ልንታገል ይገባል፡፡

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)የህዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ
ጥር 21 ቀን 2004 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)

**አዲስ በወጣው የሊዝ አዋጅ ላይ የውይይት መድረክ ለእሁድ ጥር 20 ቀን 2004 ዓ.ም መጥራቱ ይታወቃል። ሆኖም ከአፍሪካ ሕብረት የመሪዎች ስብሰባ ጋር በተያያዘ ምክንያት ወደ እሁድ ጥር 27 ቀን 2004 ዓ.ም መተላለፉን እየገለፅን በውይይቱ ላይ እንዲገኙ በአክብሮት ተጋብዘዋል።**

## በውይይት መድረኩ ላይ

**የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉ እና ኢ/ር ዘለቀ ረዲ ጽሑፍ ያቀርባሉ።**
**የስብሰባው ቦታ፡- ኢየሩሳሌም ሆቴል**
**የስብሰባው ቀን፡- እሁድ ጥር 27 ቀን 2004 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡00 /ሰዓት/ ጀምሮ**

**ለለውጥ በጽናት እንታገላለን!!**
**የሕዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ**

የኢትዮጵያ ሕዝብን የሥልጣን ባለቤት ለማድረግ በሚደረገው ትግል የግልዎን ድርሻ መወጣት ይፈልጋሉ?
እንግዲያውስ ለዚህ አላማ በፅናት ለሚታገለው አንደነት ፓርቲን በሞራል፣ በሀሳብና በገንዘብ ይርዱ።

አንደነትን በገንዘብ መርዳት ለምትፈልጉ፡
አንደነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ
የሂሳብ ቁጥር፡- 510
ንብ ባንክ፡ ዑራኤል ቅርንጫፍ ገቢ ያድርጉ።

ድረ-ገፅ: www.andinet.org
E-mail: andinet@andinet.org
or udjparty@gmail.com
Tel. 0111226288